

"በምዕራባውያኑ ድርጊት ዋጋ ብንከፍልም፤ ትግላችን በራሱ አፍሪካውያንን ያነቃል'

- አቶ ሽፈራው ወልደሚካኤል
የቀድሞ የፍትህ ሚኒስትር

ገጽ 6

የክፋትና ምቀኝነት ቅንብር- **የህጻናትን** ሕይወት እስከማጥፋት

ገጽ 10


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 042 ጥቅምት 12 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# «ለአሸባሪው ትህነግ ተጨማሪ እድል መስጠት በትግራይ ሕዝብ ላይ ሌላ የመከራ ዓመታትን መጨመር ነው»

- አቶ ምዑዝ ገብረህይወት
የሰብአዊ መብት ተሟጋች

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ለአሸባሪው ትህነግ ተጨማሪ እድል መስጠት የቡድኑን ህልውና በማስቀጠል በትግራይ ሕዝብ ላይ ተጨማሪ የመከራ ዓመታትን መጨመር በመሆኑ የቡድኑ ህልውና እንዲያበቃ ማድረግ ይገባል ሲሉ አቶ ምዑዝ ገብረህይወት ተናገሩ።

የሠላም አምባሳደር፣ የሰብዓዊ መብትና የመልካም አስተዳደር ተሟጋች የሆኑት አቶ ምዑዝ ገብረህይወት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አንዳንድ ምዕራባውያን ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ለትግራይ ሕዝብ ተቆርቋሪ መስለው ይታያሉ። ነገር ግን ትግራይ ነፃ የሚሆነው ከአሸባሪው ሕወሓት ነጻ ሲወጣ በመሆኑ ለዚህ ትልቁን ሃላፊነት መውሰድ ያለበት ራሱ የትግራይ ሕዝብ እና የፌዴራል መንግሥቱ ነው ብለዋል።

በኢትዮጵያ አሻንጉሊት የሆነ መንግሥት እንዲፈጠር ፍላጎት ያላቸው አንዳንድ የውጭ አካላት የአገርን ሉዓላዊነት ከሚንድ ተግባር መቆጠብ እንዳለባቸውም አቶ ምዑዝ ገልጸዋል።

አቶ ምዑዝ እንደገለጹት፤ እንደ አንድ ሉዓላዊት አገር የትግራይ ሕዝብ ነጻነት የሚረጋገጠው በኢትዮጵያ መንግሥት እንጂ በሌላ በማንም አይደለም።

«ለአሸባሪው ትህነግ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ



# ቢሮው በሦስት ወራት ከ18 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ሰበሰበ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከ 18 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ መሰብሰቡን አስታወቀ።

የቢሮው ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ ተፈራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ቢሮው ባለፉት ሦስት ወራት

ቢሮው በሦስት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ብሔራዊ ባንክ የወሰዳቸው እርምጃዎች በበጎ የሚታዩ ናቸው

ዘላለም ግዛው


አዲስ አበባ፡- የጦርነት ኢኮኖሚ ውስጥ የሚገኘውን የአገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታ ለመታደግ ብሔራዊ ባንክ የወሰዳቸው እና እየወሰዳቸው የሚገኙ እርምጃዎች በበጎነት እንደሚታዩ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዛፉ እየሱስ ወርቅ ዛፉ ገለጹ።

አቶ ዛፉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በብሔራዊ ባንክ በኩል እየተወሰዱ የሚገኙት እርምጃዎች በበጎ የሚታዩ ናቸው። በመንግሥት በኩል በሕገ ወጥ የገንዘብ ክምችት እና ምንዛሪ ላይ እንዲሁም በፍራንኮ ቫሉታ ላይ የተወሰዱት እርምጃዎች በበጎ የሚወሰዱ እንደሆኑም ጠቅሰዋል።

በመንግሥት በኩል የዋጋ ንረትን ለማረጋጋት፤ ያለምንም የውጭ ምንዛሬ ፍቃድ (ፍራንኮ ቫሉታ) በጉምሩክ በኩል በቀጥታ እንዲገቡ የተፈቀደውን ውሳኔ ያለአግባብ ጥቅም ላይ የሚያውሉ አካላት ተገቢ አለመሆኑን የገለጹት አቶ ዛፉ፤ ሌሎች ቀዳዳዎች ሊኖሩ ስለሚችሉም መንግሥት በዚህ ረገድ ክትትል እንዲያደርግ መክረዋል።

እየተባባሰ የመጣውን የዋጋ ግሽበት እና የኑሮ

ብሔራዊ ባንክ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሴ

አቶ ዛፉ እየሱስ ወርቅ ዛፉ


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

DERBA CEMENT



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ



eccs

የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ

ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.

የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ



Mob. 0911 225057/ 0989 343434

አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት



MP ማልዲቭስ ማስታወቂያ እና ህትመት

ለሁሉም የማስታወቂያ እና ህትመት ፍላጎትዎ ከተደራጀ ወርክሾፕ እና ዘመናዊ ማሽኖች ጋር

- 'CNC' መቁረጫ እና ኢንግሬቪንግ ማሽን
  ፎም ቦርድ፣አሉሚኒየም፣ኤም ዲ ፍ . . .
- 'Laser' መቁረጫ እና ኢንግሬቪንግ ማሽን
  ማይካ፣ ቆዳ፣ጨርቅ . . .
- 'UV flat bed printer' ለስጦታ እቃዎች
  እስክርቢቶ፣ ፍላሽ ዲስክ፣አጀንዳ . . .
- የቲሸርት እና ጨርቅ ላይ ዲጂታል ህትመት
- ዲጂታል ህትመት ማሽን
  ሮል አፕ፣ ስቲከር፣ አንፀባራቂ፣ትራንስፓረንት . . .
- የ 'Heat press' ማሽኖች
  ኮፍያ፣ማግ፣ሠሀን . . .

እንዲሁም የኤግዚቢሽን ስታንድ እና የመድረክ ግንባታ ስራዎች

ፈጣን እና ጥራት ያለው ስራ

+251 911 253 076 / +251 984 872 919

maldivespromotion@gmail.com

ሾላ ፣ ወደ እንግሊዝ ኤምባሲ በሚወስደው ዋና መንገድ



EFDA

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን

ETHIOPIAN FOOD & DRUG AUTHORITY

በነፃ የስልክ መስመር 8482 ዘወትር በስራ ሰአት ከሰኞ እስከ አርብ በመደወል

- በምግብ ጥራት ደህንነት
- በመድኃኒት ጥራት፤ ደህንነትና ፈዋሽነት
- በመድኃኒት አግባባዊ አጠቃቀም
- ትምባሆ እና አልኮል

- ምግብ፤
- መድኃኒት
- ትምባሆ
- አልኮልን

የሚመለከቱ ጥያቄዎችን እና ጥቆማዎችን ይቀበላል መረጃዎችን ይሰጣል

አፈጻጸሙን ም ይከታተላል

በህገወጥ የምግብ፣ የመድኃኒት፣በህክምና መሳሪያ፣ የጤና ግብአቶች ንግድና ዝውውር ላይ በመጠቆም የበኩልዎን ይወጡ::

ወቅታዊና እውነተኛ የጤና ግብዓት ቁጥጥር መረጃ ለማግኘት ተጨማሪ ያንብቡ

የቴሌግራም ቻናል https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority

የፌስቡክ ገጽ https://www.facebook.com/Ethiopian-Food-and-Drug-Authority-EFDA-854974084615919/

አላይን ለማመልከት http://www.eris.efda.gov.et/

የኢትዮጵያ ምግብ መድኃኒት ባለስልጣን



አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ

ADAMA STEEL FACTORY

ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር





0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

## የ2014 ዓ.ም ብሔራዊ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በስኬት ተጠናቀቀ

ገጽ 3



አቶ ስለሺ ለማ

# ማዕከሉ 114 ሚሊዮን ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ማግኘቱን አስታወቀ

**ፍቃዱ ዴረሳ**

አዲስ አበባ፡- በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከል በ2014 በጀት ዓመት አንድ 114 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የኤክስፖርት ገቢ ማስገኘቱን አስታወቀ።

በአምራች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የምግብና መጠጥ ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ማዕከል የ2014 ዓ.ም አፈጻጸምና የ2015 በጀት ዓመት የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ውይይትና የተሻለ አፈፃጸም ላሳዩ አምራች ተቋማት እውቅና ሰጥቷል።

በዚህ ወቅት የጨርቃጨርቅ፣ ቆዳና ምግብ ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ስለሺ ለማ እንዳስታወቁት በማዕከሉ የተሰማሩ አምራቾች የማምረት አቅማቸውን በ2014 በጀት ዓመት 67 በመቶ ለማድረስ እንዲሁም ከኤክስፖርት የሚገኘውን ገቢ ወደ 110 ሚሊዮን ዶላር ለማድረስ እንዲሁም የተመረጡ እስትራቴጂክ ተኪ ምርቶችን ደግሞ 50 በመቶ በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት አቅዶ ሲንቀሳቀስ መቆየቱን ገልጸዋል።

በዚህም በበጀት ዓመቱ 69 ሺህ ቶን ምርት ወደ ውጪ በመላክ ከ114 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ የኤክስፖርት ምርት ገቢ መገኘቱን አስታውቀዋል። በተመረጡ እስትራቴጂክ ተኪ ምርቶች የሀገር ውስጥ ምርትን 57 በመቶ ማድረስ መቻሉንም ተናግረዋል።

በ2015 በጀት ዓመትም የኤክስፖርት ተኪ ምርትን በሚያሳድጉ ጉዳዮች ዙርያ ከባለሀብቶችና ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በቅንጅትና በትብብር የሚሰራ መሆኑን የተናገሩት አቶ ስለሺ፤ በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች ውጤታማ ድጋፍና ክትትል በማድረግ በገበያ ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል በትጋትና በቁርጠኝነት መስራትና መደገፍ ይጠይቃል ብለዋል።

በ2014 በጀት ዓመት የታዩ መልካም አፈፃጸሞች ለዚህ በጀት ዓመት መልካም መነሻ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሀሰን መሀመድ ተናግረዋል። በተያዘው በጀት ዓመት በዘርፉ የተሻለ አፈፃፀም ለማስመዝገብ በቅንጅትና በትብብር መስራት ተገቢ እንደሆነና ለለውጥም ይህን አሰራር በተገቢው ገቢራዊ ማድረግ ተገቢ ነው ብለዋል። በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለወደፊት ማምረት የምትፈልጉ ባለሀብቶች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አስፈላጊውን ትብብር የሚያደርግ መሆኑን ተናግረዋል።

የተሻለ ሀገርና የኢኮኖሚ እድገት እንዲኖር ከተፈለገ የግሉን ዘርፍ ማህበራት ሚና በማጎልት መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረት እንዲጠቀሙ ማድረግ ይገባል ያሉት አቶ ስለሺ፣ ማህበራቱም የተሰጣቸውን ትኩረት በተገቢው በመጠቀም ምርቶቻቸውን በጥራት፣ በብዛትና በፍጥነት በማምረት ሀገር የምትፈልገውን የውጭ ምንዛሬ እንዲያስገኙ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በመርሃ ግብሩ ለሴት ባለሀብቶች፣ ለተኪ አምራቾች፣ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች፣ ለዘርፍ ማህበራት፣ ለልማት አጋር አካላት፣ ለኤክስፖርት አድራጊዎችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሽልማትና እውቅና ተሰጥቷል።

# በአሸባሪው ትህነግ የወደሙ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማቶችን አገልግሎት ለማስጀመር እየተሠራ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- በአሸባሪው ትህነግ የወደሙ የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማቶችን በመጠገን አገልግሎት ለማስጀመር በጥናት ላይ የተመሰረተ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ገለጸ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ሞገስ መኮንን እንዳሉት፤ አሸባሪው ትህነግ በኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ላይ በፈጸመው ጥቃት ሳቢያ አንዳንድ የትግራይና የአማራ አካባቢዎች እስካሁን የኤሌክትሪክ ኃይል እያገኙ አይደለም። በተለይ ከአላማጣ እና ከሽሬ ሰብስቴሽን የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያገኙ አካባቢዎች ለረጅም ጊዜ አገልግሎቱን ማግኘት አልቻሉም።

ከአላማጣ ሰብስቴሽን የሚወጣውን ኃይል የሚጠቀሙ የላሊበላ፣ የሰቆጣና አብዛኛዎቹ የዋግኽምራ ዞን ወረዳዎች የኤሌክትሪክ ኃይል እያገኙ አይደለም ያሉት አቶ ሞገስ፤ እንዲሁም በወልቃይትና ሁመራ ያሉ አካባቢዎችም እንዲሁ እስካሁን የኤሌክትሪክ ኃይል አለማግኘታቸውን ተናግረዋል።

ሆኖም የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ባለሙያዎች ካለፈው ማክሰኞ ጀምሮ ወደ እነዚህ ስፍራዎች እንዲሄዱ በማድረግ የደረሰው ጉዳት ላይ ጥናት በማድረግ ላይ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ወደ ስፍራው ያቀናው የባለሙያ ቡድን የደረሰውን ጉዳት በማጥናት በሚያቀርበው ሪፖርት ላይ የተመረኮዘ የጥገና ስራ እንደሚጀመር ተናግረዋል።

የጥገና ስራውን ለማከናወን የጥናቱን ሪፖርት መጠበቅ የግድ አስፈላጊ መሆኑን የገለጹት የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተሩ ፤ ባለሙያዎቹ እስካሁን እስከ ቆቦ ያለውን መስመር ጥናት ጨርሰዋል ብለዋል።

ከዚህ ቀደም በነበረው ሂደት እስከ ቆቦ ያለው መስመር የጥገና ስራ ተሰርቶ የተጠናቀቀ ቢሆንም በአሸባሪው ሕወሓት መልሶ ጉዳት ስለደረሰበት ዳግም ማጥናት ማስፈለጉን አመልክተዋል።

ከወልዲያ አልውሃ ከሚባለው አካባቢ ጀምሮ እስከ አላማጣ ድረስ ሰፊ ሥራ የሚጠይቅ የኤሌክትሪክ መስመር ጥገና መኖሩን መገንዘብ ተችሏል ብለዋል።

በሑመራና በአላማጣ መስመር አሁን ላይ ምን ያህል ጉዳት እንደደረሰ ባለሙያዎች ጥናት እያደረጉ መሆኑን ገልጸው፤ ጥገናውን የሚያከናውን ቡድን መዘጋጀቱንም ተናግረዋል።

ይህ ቡድን የሚጠብቀው የጥናቱን ውጤትና ትዕዛዝ ብቻ መሆኑን ገልጸው፤ የተቋረጠውን የኤሌክትሪክ ኃይል ወደነበረበት ለመመለስ በቂ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን አመልክተዋል።

ይሁን እንጂ በአንዳንድ አካባቢዎች የኤሌክትሪክ ኃይል መስመሮች ከዋና መንገድ ርቀው በተራራና ሸለቆ አካባቢ እንደመገኘታቸው ከፈንጂ ያልጸዱ አካባቢዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ ከሀገር መከለከያ ሠራዊት የደህንነት ማረጋገጫ ሲሰጥበት ስራው እንደሚጀመር ጠቁመዋል።

ከዚህ ቀደም በሽሬ በኩል የወልቃይት መስመርን ለማገናኘት የተጀመረው ስራ 40 ኪሎ ሜትር ሲቀረው በአሸባሪው ወያኔ ዳግም በተቀሰቀሰ ጦርነት ሥራው መቋረጡን ማስታወሳቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

መንግሥት የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦትንና መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማስቀጠል ከሰሞኑ መግለጫ ማውጣቱ ይታወሳል።

መግለጫውን ተከትሎ የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦትና መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማስጀመር መንግሥት በቁርጠኝነት እየሠራ መሆኑን ለሰብዓዊ ድጋፍ የተቋቋመው ኮሚቴ ማሳወቁም ይታወቃል።

# የኢትዮ-ኬንያ የኃይል ማስተላለፊያ መስመር ኃይል ማስተላለፍ ሊጀምር ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የኢትዮ- ኬንያ ባለ 500 ኪሎ ቮልት የከፍተኛ ኃይል ማስተላለፊያ መስመር በቀጣዮቹ ሁለት ሳምንታት ኃይል ማስተላለፍ እንደሚጀምር የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ገለጸ። ሕብረተሰቡ ከኃይል ማስተላለፊያ መስመር ተሸካሚ የብረት ምሰሶዎች ንክኪ እንዲርቅም ተጠይቋል።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የማስተላለፊያ መስመሮችና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ኮንስትራክሽን ዘርፍ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ክብሮም ካህሳይ ከወላይታ ዞን አስተዳዳሪና የመምሪያ ኃላፊዎች ጋር ውይይት ሲያካሄዱ እንደገለጹት፤ የኢትዮ-ኬንያ የኃይል ትስስር ለኢኮኖሚ ያለው ፋይዳ የላቀ ነው። በተመሳሳይ በጋሞ ዞን በኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት ላይ የሚፈፀመው ስርቆት እየቀነሰ ቢመጣም አሁንም ክትትል የሚያስፈልገው ስለመሆኑ ለአመራሮቹ ተገልጾላቸዋል።

በቀጣይም በዞኑ መሰረተ ልማቱ በሚያልፍባቸው አካባቢዎች ምንም ዓይነት ስርቆት እንዳይከሰት ለሕብረተሰቡ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እንዲሰራ፣ የፀጥታ አካላትም ተንቀሳቅሰው እንዲጠብቁና ሕብረተሰቡ በይዞታው ላይ የተተከሉትን ምሰሶዎች እንዲጠብቅ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እንዲሰራ ጥያቄ ቀርቦ መግባባት ላይ መደረሱን ተገልጿል።

በጋሞ ዞን ምዕራብ አባያ ወረዳ 18 ቤቶች ካሳ ተከፍሏቸው አለመነሳታቸው በውይይቱ ላይ ተጠቅሷል። ሕብረተሰቡም መስመሩ ኃይል ያልተለቀቀበት መስሎት በመዘናጋት ጉዳት እንዳይደርስበት በሕዝብ መድረክ፣ በማሕበራዊ ሚዲያና ለነዋሪዎች ተደራሽ በሆኑ ዋና ዋና ሚዲያዎች ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እንዲሰራ መግባባት ላይ ተደርሷል።

በተያያዘ ዜና በፕሮጀክቱ ሥራ መጀመር ዙሪያ ከኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ጽህፈት ቤት የስራ ኃላፊዎች ጋር ተመሳሳይ ውይይት መደረጉን ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

# ታማኝ ግብር ከፋዮች ቅድሚያ አገልግሎት የሚያገኙበት ሥርዓት ተግባራዊ ሊደረግ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ለታማኝ ግብር ከፋዮች በተለይም ዕውቅና እና ሽልማት ላገኙ ግብር ከፋዮች ሀገሪቱ ለዜጎች የምትሰጣቸውን አገልግሎቶች ቅድሚያ እንዲያገኙ የሚያደርግ ሥርዓት በአጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ እንደሚደረግ ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ገለጹ።

ግብር በመሰወር እና በማጭበርበር፣ በኮንትሮባንድ እና በሌሎችም የሌብነት ዘርፎች ላይ የተሰማሩ ጥቂት ሕገወጦችም በሀገሪቱ ሕግ መሰረት እንደሚጠየቁ ፕሬዝዳንቷ ተናግረዋል።

የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ እንደገለጹት፤ ሕግን አክብረው የሚጠበቅባቸውን ግዴታ በመወጣት ላይ ያሉ በተለይም በተለያየ ደረጃ ዕውቅና የተሰጣቸው ግብር ከፋዮችን ሀገሪቷ ለዜጎቿ የምትሰጣቸውን አገልግሎቶች ቅድሚያ እንዲያገኙ እንደሚደረግ መንግሥት ከዚህ ቀደም ቃል ገብቷል።

በመሆኑም መንግሥት ቀደም ብሎ ቃል በገባው መሰረት ለታማኝ ግብር ከፋዮች ሀገሪቷ ለዜጎቿ ከምትሰጣቸው አገልግሎቶች ቅድሚያ እንዲያገኙ ለማስቻል ቅድመ ሁኔታዎች እየተመቻቹ ሲሆን ቅድሚያ የመስጠት ሥርዓቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ይደረጋል ሲሉ ገልጸዋል።

ለዜጎች ከሚሰጡ አገልግሎቶች ግብር ከፋዮች ቅድሚያ መሰጠታቸው ለታማኝ ግብር ከፋዮች ሀገር የምትሰጣቸውና የሚገባቸው ክብር መግለጫ ይሆናልም ሲሉ አክለዋል።

ከሁሉም በላይ አሁናዊ ሀገራዊ እና አካባቢያዊ ሁኔታ በአንድ በኩል የሀገሪቱን የገቢ አቅም እንዲያድግ የሚያስገድድ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሀገሪቱን ሰላም ለማስጠበቅ እና የተጀመሩ ልማቶችን ዕውን ለማድረግ ገቢ ከፍተኛ ሚና አለው ብለዋል።

መንግሥት ከዜጎቹ ተገቢውን ግብር በተገቢው ወቅት ካላገኘ ለልማትና ለሰላም የሚያስፈልገውን ገቢ ለማግኘት የሀገራትንና የልማት አጋሮችን በር ማንኳኳት



ግዴታ ይሆናል ሲሉም አብራርተዋል።

በመሆኑም ከአላስፈላጊ ጥገኝነት እና ወለድ እና ሌሎች ጫናዎችን ለመቀነስ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ሀገርን ከጥገኝነት ለማላቀቅ ከሀገር ውስጥ የሚገኘውን ገቢ ማጠናከር የመጀመሪያ እና የትብብር ማዕከል ሊሆን እንደሚገባ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል የታማኝ ግብር ከፋዮችን አርአያ ያልተከተሉ እና ግብርን በመስረቅ የተሰለፉት ከመጥፎ መንገዳቸው እንዲመለሱ እንደሚደረግ እና ይኸው መንገድ ያዋጣናል ብለው የሚቀጥሉ ካሉ ደግሞ የጤነኛ ግብር ከፋዮችን መብትና ግዴታ እኩልነት ለማስጠበቅ እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ጠቁመዋል። ኢትዮጵያ እንዲህ ዓይነት ጥፋቶችን ልታርምባቸው የምትችላቸው ሕጎች እንዳሏት እና ተፈፃሚ ልታደርገው እንደመትችል መዘንጋት የለበትምም ሲሉ አክለዋል።

የሌብነት አማራጭ አዋጭ አለመሆኑን ከወዲሁ በመገንዘብ ሁሉም ወደ ትክክለኛው መስመር በመግባት የሚጠበቅበትን ልማታዊ አስተዋፅዖ እንዲያደርግ ያሳሰቡት ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ፤ በሕግ የሚጠበቀውን ሳይከፍሉ የሀገር መሰረተ ልማትን ለመጠቀም መሞከር ከከፈለው እንደመዝረፍ እንደሚቆጠርም አብራርተዋል።

ከማንኛውም ሌብነት እና ሙስና የፀዳ የመንግሥት አመራር፣ መዋቅር እና ሕብረተሰብ እንዲኖረን በጋራ መሥራት ይኖርብናል ያሉት ፕሬዝዳንቷ፤ ባለፈው በጀት ዓመት በገቢ አስተዳደሩ የተሞከረውን ሙስናና ሌብነትን የማጋለጥ በጎ ተግባር በተያዘው ዓመት ተጠናክሮና ጨምሮ መታየት ይኖርበታል ሲሉም አሳስበዋል።

# «ሰላምን ያስቀደመው የፕሬዚዳቷ ዓመታዊ ንግግር የመንግሥትን የሰላም ቁርጠኝነት ያሳያል»

*- ሰለሞን ተፈራ*

**በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር**

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ ፡- ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ በ6ኛው ሕዝብ ተወካዮች እና ፌዴሬሽን ምክር ቤት 2ኛ ዓመት የጋራ የሥራ ዘመን ያቀረቡት መክፈቻ ንግግር ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት የሕግ ማስከበር ስራ እንደሚሰራ አቅጣጫ ማስቀመጣቸው መንግሥት ሰላምን ለማስፈን በቁርጠኝነት እየሰራ መሆኑን የመላክታል ሲሉ በአምቦ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ ምሁሩ ገለጹ።

መምህር ሰሎሞን ተፈራ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ፕሬዚዳንቷ በንግግራቸው ለሰላም መስፈን ቅድሚያ መስጠታቸው መንግሥት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝት በአግባቡ ያሳየ ነው።

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ በዲፕሎማሲ፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ችግሮች እየተስተዋሉ ነው። ግብርናን በማዘመን ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እና ለመሰል ጉዳዮች በተለይ በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያለው ጦርነት እንቅፋት ሆኗል። በመሆኑም መንግሥት ለነዚህ ችግሮች ቅድሚያ በመስጠት ለመፍታት መንቀሳቀሱ ችግሩን ለመፍታት ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያል።

ፕሬዚዳንቷ ከተቀመጡት አቅጣጫዎች መካከል ችግሮችን በምክክር ለመፍታት እንደ ሀገር ተቋቁሞ ስራ ላይ የሚገኘው ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዘላቂ ሰላም ለማስፈን ትልቁ መሳሪያ ተደርጎ በትኩረት



እየተሰራበት መሆኑን እንደማሳያ አንስተዋል።

እንደ መምህር ሰለሞን ገለጻ፤ ከሕወሓት ጋር ያሉ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት መንግሥት በተደጋጋሚ ቁርጠኝነትን ሲገልጽ ቆይቷል። የፕሬዚዳንቷ ንግግር ያለ ምርጫ ቦርድ እውቅና ራሱን “የትግራይ ክልል መንግሥት” እያለ የሚጠራው አሸባሪ ቡድን በቀረቡለት አማራጮት መፍትሔ ሃሳቦች የማይገዛ ከሆነ በእርምጃ ሕገ መንግሥቱን የማስከበር ፅንሰ ሃሳብ ያካተተ ንግግር ነው ብለዋል።

በሰላማዊ መንገድ መፍትሄ ማስገኘት የሁለቱም አካላት ድምር ውጤት በመሆኑ የመንግሥት ሰላም ፈላጊነት ብቻውን ሰላም ለማምጣት እንደማያስችል የጠቆሙት መምህሩ፤ ሕወሓት ከጠብ አጫሪነት ተግባሩ ተለቆ ፊቱን ወደሰላም መመለስ እንዳበትም አሳስበዋል።

በሰላማዊ መንገዶች ችግሮችን የመፍታት አማራጮች አሸባሪው ቡድን የማይቀበል ከሆነ መንግሥት የዜጎቹን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ ደህንነትና የግዛት አንድነት ለማረጋገጥ እርምጃ የመውሰድ ሕገ መንግሥታዊና ሞራላዊ ግዴታ እንዳለበትም አቶ ሰለሞን ገልጸዋል። በተጀመረው መሰረት በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ፌዴራል ተቋማትና ዜጎች ደንነት ለመጠበቅ እርምጃውን መቀጠል አለበት ሲሉም ተናግረዋል።

በተመሳሳይም መንግሥት በፕሬዚዳንቷ የተቀመጡ አቅጣጫዎች መሬት ላይ ውጤታማ ለማድረግ አስፈላጊውን ፖለቲካዊ እርምጃዎችን መውሰድ እንዳለበት አብራርተዋል። ስራ አስፈጻሚዎቹን ጨምሮ ከላይ እስከ ታች ያሉትን በመፈተሽ ብቁ አመራሮችን በመመደብና ቅርብ ክትትል በማድረግ በፕሬዚዳንቷ የተቀመጠሳን አቅጣጫ እውን ለማድረግ መሰራት አለበት ብለዋል።

በሀገሪቱ ውስጥ የሚታዩ ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከፖለቲካዊ አለመግባባቶች እንደሚመነጩ ጠቅሰው ግብርና ዘርፉ በማዘመን ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር ሰላምን ሊያሰፍኑ በሚችሉ ጉዳዮች ዙሪያ በትኩረት ሊሰራበት እንደሚገባ አሳስበዋል። በተመሳሳይም የሚኒስትሮች ምክርቤት የአስፈጻሚ አካላት አፈጻጸምን በቅርበት በመከታተልና በመገምገም የተቀመጠውን አቅጣጫ ውጤታማ ለማድረግ የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንዳለበት ገልጸዋል።

# በዲሲ የሚገኙ ዳያስፖራዎች የመንግሥትን አቋም በመደገፍ ነገ ሰላማዊ ሰልፍ ያካሂዳሉ

**አስቴር ኤልያስ**

አዲስ አበባ፡- በአሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች በነገው ዕለት ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት በነጩ ቤተ መንግሥት ፊት ለፊት የኢትዮጵያን መንግሥት በመደገፍ ሰላማዊ ሰልፍ እንደሚያካሂዱ በዋሽንግተን ዲሲ ነዋሪው አቶ ነጋሲ በየነ ገለጹ።

በዋሽንግተን ዲሲ ነዋሪ የሆኑት አቶ ነጋሲ በየነ ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት የስልክ ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት፤ ኢትዮጵያውያን ከአያቶቻችን የተማርነው ለማንም መንበርከክን ሳይሆን የትኛውንም ጠላት ማንበርከክን ነው። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ላይ እየደረሰ ያለውን ጫና በመቃወም በዲሲ የሚገኙ ዳያስፖራዎች በነገው ዕለት ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ በነጩ ቤተመንግሥት ፊት ለፊት ለኢትዮጵያ ጠበቃ ሆኖ ለመቆም ተዘጋጅተዋል።

አቶ ነጋሲ፣ ልጆቻችን ለውትድርና ሕይወታቸውን እየሰጡ ነው። እኛ በውጭ አገር ያለነው ዳያስፖራዎች ጊዜያችንንና ገንዘባችንን ለመስጠት ማቅማማት አይጠበቅብንም ሲሉ ጠቅሰው፤ በዕለተ እሁድ ለሚካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ሁሉም እንዲገኝ ጥሪ ተደርጓል ብለዋል። በነጩ ቤተመንግሥት ፊትለፊት የሚደረግ ሰላማዊ ሰልፍ በተለያዩ አካላት በኢትዮጵያ ላይ እየደረሰ ያለው ጫና እንዲቆም መልዕክት የሚተላለፍበት ነው ሲሉ ጠቁመው፤ ቀጣይነት እንዳለውም አመልክተዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ ከዚህ ጎን ለጎን ሌላ የሚደረገው የአሜሪካን ሴናተሮችና የኮንግረስ አባላትን በመቅረብ ለኢትዮጵያ ጥቅም እንዲቆሙ እናድርግ በሚል ጉዳይ ላይም እየተሰራበት ነው። ይህ ቢያንስ በአሜሪካ ካሉት 50 ያህል እስቴቶች ውስጥ ኢትዮጵያውያን በብዛት አሉበት በሚባሉት በ21 ስቴቶች ላይ እየተሰራበት ይገኛል። በተለይ በሚካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያኑ እነዚህ አካላት ከኢትዮጵያና ከኤርትራ ጎን የማይቆሙ ከሆነ በምርጫ ወቅት ድምጽ የማይሰጧቸው እንደሆነም እወቁ በሚል መልዕክት ይተላለፋል ተብሎም ይጠበቃል።

አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በአሜሪካ በሚደረገው የምርጫ ጊዜ ድምጹን ለመስጠት አይወጣም፤ ከወጣም በኋላ ብዙዎቹ ማንን መምረጥ እንዳለባቸው አያውቁም ያሉት አቶ ነጋሲ፣ በመሆኑም ይህ አይነቱን አካሄድ እንዳይኖር ከወዲሁ ኢትዮጵያውያኑን እያነቃቃናቸው እንገኛለን ብለዋል።

ለሚካሄደው ምርጫ የእኛ የኢትዮጵያውያኑ ድምጽ ያስፈልጋል ያሉት አቶ ነጋሲ፣ በቨርጂኒያም ሆነ በሜሪላንድ በዛ አግባብ እየሰራን ነው ብለዋል። አያቶቻችን ከእነዚህ አንዳንድ ምዕራባውያን ጋር ተጋፍጠው ያሸነፉት የደም መስዋዕትነት ከፍለው ነው። እኛ ደግሞ ጊዜያችንንና ገንዘባችንን መስዋዕት አድርገን ኢትዮጵያን ብንታደግ ለኢትዮጵያ ያንስባታል እንጂ አይበዛባትም ሲሉ አስረድተዋል።

ሚዲያዎቻቸው እያደረጉ ያለውን ተንኮል እኛ ኢትዮጵያውያን ላይ እስኪደርስ ድረስ አላወቅናቸውም ነበር። ስለዚህም የእነርሱ ጣልቃ ገብነት ለእኛ ከማሰብ የመነጨ አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ለምሳሌ አሸባሪውን ሕወሓት ሲደግፉ ለትግራይ ሕዝብ ስለሚያስቡለት አይደለም። የቅርብ ጊዜ ትውስታችን የሆነችውን አፍጋኒስታንን ብናይ ለሃያ ዓመት ቆይተውባት የወጡት ዶግ አመድ አድርገዋት ነው። ስለዚህም እንቅስቃሴያቸው ሁሉ ከራሳቸው ጥቅም ጋር የተሳሰረ እንጂ ሌላውን ለማገዝ የሚደረግ ባለመሆኑ ሁሉም ከኢትዮጵያ ጎን ሊቆም ይገባል ሲሉ ተናግረዋል። ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያ እንቁም ሲሉም ጥሪ አቅርበዋል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ደስ ያሰኘን ነገር ቢኖር በስንዴ ራሳችንን ችለን ለውጭ ገበያ እናቀርባለን የተባለው ጉዳይ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ እየተሰራ ያለው ስራ ይበል የሚያሰኝ ነው። ይህ ስራ የኢትዮጵያ እጅ እንዳይጠመዘዝ የሚያደርግ ስራ ስለሆነ ለዚህ ስራው መንግሥት ድጋፍ ያስፈልገዋል። በመንግሥት በኩል የጎደለ ነገር ካለ ደግሞ እንዲታረም ማድረግ ነው እንጂ አገርን አሳልፎ መስጠት አግባብ አይደለም።

# የ2014 ዓ.ም ብሔራዊ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በስኬት ተጠናቀቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በተለያዩ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋምት ሲሰጥ የነበረው የ2014 ዓ.ም ብሔራዊ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በስኬት መጠናቀቁን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

የመንግሥት ኮሙኒኬኝን አገልግሎት ትናንትና ባወጣው መግለጫ በፈተናው አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ተማሪዎችና ፈታኞች እንደተሳተፉበት ገልጿል።

እንደ መግለጫው ከሆነ፤ የኢትዮጵያ ዕድገትና ብልጽግና የሚረጋገጠው የሥነ ምግባር እና የዕውቀት ጥራት ባለው የሰው ኃይል በመሆኑ ፖሊሲና አሠራሮች በዚሁ ልክ ተቀምረዋል። ይሄ ጅምር በጥልቀት በተጠና የትምህርት ፍኖተ ካርታ ሥራ ተተግብሮ ታይቷል። አጓጊ በሆነው በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ ተራምዷል።

የትምህርት መሪዎች፣ መምህራንና ወላጆች በታላቅ ቅንጅት በመሥራት ላይ ናቸው። የዚህ የለውጥ ሥራ አካል የሆነው ተማሪዎችን በሐቅ እና በሳይንሳዊ መንገድ የመመዘን ሥራ ታላቅ እመርታ አሳይቷል ሲል አገልግሎቱ አስታውቋል።

የዚሁ ለውጥ አካል የሆነው የ2014 ዓ.ም የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተናም የጥረቶቹ ተከታይ ሆኖ በታላቅ ስኬት መጠናቀቁን አገልግሎቱ ገልጿል።

በቀደመው የማኅበራዊ ሳይንስ የፈተና አሰጣጥ ላይ የታዩ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች ተገምግመው በተፈጥሮ ሳይንስ ፈተና ወቅት የተሠራው ሥራ እጅግ አመርቂ ሆኗል ሲል አገልግሎቱ በመግለጫው ጠቁሟል።

የፈተና አሰጣጡ ስኬት በሌሎችም ሀገር አቀፍ ምዘናዎች ሊተገበሩ የሚችሉ የተሻሉ አሠራሮችን አስተምሮ ማለፉን የገለጸው አገልግሎቱ፤ በሁሉም ደረጃ ያሉ ተማሪዎች በራሳቸው ሥራ ብቻ ተማምነው መቆም እንደሚኖርባቸው እንዳስተማረ አስታውቋል።

እንደ መግለጫው ማብራሪያ፤ በትምህርትም ሆነ በሕይወት፣ በሥራም ሆነ በኃላፊነት መስኮች የአጭበርባሪነት በር እየተዘጋ የሚሄድ መሆኑን ማረጋገጫ ሰጥቷል። በአንፃሩም በመጪዋ ኢትዮጵያ በራስ ጥረት እና ላብ መተማመን ብቻ ዋጋ የሚያገኝ መሆኑን አስረግጧል።

ፈተናው ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ተማሪዎችን እና መምህራንን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ፣ ለመመገብ፣ ለማሳደር፣ ጤና ለመጠበቅና ጸጥታን ለማስጠበቅ መቻሉ በሀገራችን የተገነባውን አቅምም ያሳያል ሲል አገልግሎቱ ገልጿል።

ፈተናዎቹ በየሚሰጡበት አካባቢ ያለው ሕዝብ ለመፈተን የሄዱትን መምህራን በፍቅር የተቀበለበት፣ ባሕል ወጉን ያካፈለበት፣ የቱሪስት መስሕቦቹን ያስጎበኘበት መንገድ የሀገራችንን ሕዝቦች ወንድም እህታማማችነት ማጠናከሩንም አስረድቷል።

በዚህ ታሪካዊ ስራ ስኬት ከዝግጅት ጀምሮ እስከፍፃሜው አስተዋፅኦ ያደረጉትን ሁሉ መንግሥት ምስጋና ያቀርባል ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ገልጿል።

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

# «ለአሸባሪው ትህነግ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ኢትዮጵያን ማተራመስ የሚፈልጉ የውጭ አካላት አሁንም የሽብር ቡድኑን በመደገፍ ጩኸት እያሰሙ እንዳለ የገለጹት አቶ ምዑዝ፤ ይህ የአገርን ሉዓላዊነት የሚያፈርስና ተቀባይነት የሌለው አካሄድ እንደሆነ ተናግረዋል። ኢትዮጵያ ራሷን የቻለች ሉላዊት አገር እንጂ በባዕዳን ፍላጎት ላይ ተመስርታ የምትመራ አይደለችም ነው ያሉት።

አቶ ምዑዝ አገሪቷ ሕጋዊ በሆነ መንገድ በተመረጠ መንግሥት እየተመራች እንዳለች ጠቅሰው፤ የአገሪቷ አንድ አካል የሆነችው ትግራይም ነጻነቷ የሚረጋገጠው በመንግሥት ብቻ እንደሆነ ጠቁመዋል። ይህንን የሚገዳደር የውጭ ሃይል ፍላጎት የአንድን አገር ሉዓላዊ ክብር የሚጻረር እንደሆነ አመላክተዋል።

የሽብር ቡድኑ ኃይሎች ባደረጉት ወረራ ሰው ሲያርዱ፣ አዛውንት ሲደፍሩ፣ የንጹሃንን ንብረት አውድመው ሲያፈናቅሉ፣ ለሕዝቡ የሚላከውን ሰብዓዊ እርዳታ ለተዋጊ ሃይላቸው ሲያውሉት፣ የትግራይን ሕዝብ አስገድደው እንዲወጋ ሲያደርጉ፣ የጭካኔ በትራቸውን ነጻ እናወጣሃለን ባሉት የትግራይ ህዝብ ላይ ሲያሳርፉ ዝምታን በመምረጥ፤ የሽብር ቡድኑ ሽንፈት እንደሚደርስበት ሲያውቁ ማዕቀብ ለመጣል የሚሯሯጡ አካላት ቀጠናውን በማተራመስ ፍላጎታቸውን ለማሳካት እንደሆነ አቶ ምዑዝ ተናግረዋል።

ምንም እንኳን ለሠላም ሰላማዊ ውይይት ወሳኝ ቢሆንም አሸባሪው ሕወሓት ግን በታሪኩ ሰላም ወዳድ ቡድን ባለመሆኑ የመንግሥት ራሱን የመከላከል እርምጃ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል። “ትግራይ የኢትዮጵያ አካል እንደመሆኗ ለችግሮቿ ደራሽ ኢትዮጵያውያን ናቸው። በትግራይ ጉዳይ የሚያገባውም የኢትዮጵያ መንግሥት ነው” ሲሉ ገልጸዋል።

የሽብር ቡድኑ በሰማይም ሆነ በየብስ ሲላክ የነበረውን እርዳታ ከድሃው ጉሮሮ እየነጠቀ ለተዋጊዎቹ ቀለብ ሲያውል እንደነበር በመግለጽ፤ ይህንን ግፍ ሕዝቡ መቼውንም የማይረሳው እንደሆነ ጠቅሰዋል። በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ መንግሥት ለሕዝቡ የተሳለጠ እርዳታ እንዲደርስ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ የሚደነቅ መሆኑንም ጠቁመዋል። ለቡድኑ ተጨማሪ እድል መስጠት ሌላ 50 የመከራ ዓመታትን መጨመር በመሆኑ፤ ሕዝቡ ሠራዊቱን በመደገፍ የሽብር ቡድኑ እስከመጨረሻ ተፋልሞ ከመንግሥት ጋር በመሆን ነጻነቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል ሲሉም አቶ ምዑዝ አስገንዝበዋል።

መከላከያ ሠራዊቱ የሚወነጀል ሳይሆን ከራሱ ኮቾሮ ላይ እየቀነሰ በመስጠት ለዜጎቹ አለኝታ እንደሆነ በደረሰባቸው አካባቢዎች እያሳየ ያለው የበጎነት ሥራው ህያው ምስክር መሆኑም ተናግረዋል።

# ብሔራዊ ባንክ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ውድነትን ለማረጋጋት የሰሜኑን ጦርነት መቋጫ ማበጀት ይገባል ያሉት አቶ ዛፉ፤ ለሰላም መስፈን ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባዋል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የማክሮ ኢኮኖሚ ፈተናዎች ገጥሚታል። ይህንን ችግር በመገንዘብ መንግሥት እየሰራበት ይገኛል፤ ሆኖም ለመፍትሄው የተጀመሩ ጥረቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ሲሉም ምክረሃሳብ ለግሰዋል።

በአገሪቱ ለሚስተዋለው የኢኮኖሚ ችግር ሃላፊነቱ የመንግሥት ብቻ አድርጎ መመልከት ትልቅ ስህተት ነው ያሉት አቶ ዛፉ፣ መንግሥት፤ ድርጅቶች በአንጻራዊ ሰላም ሁኔታ ስራቸውን እንዲሰሩ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

የኑሮ ውድነቱ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉና አነስተኛ ገቢ ያላቸውን በከፍተኛ ደረጃ ቢያጠቃም፣ የመንግሥትና የግል ዘርፉ ሰራተኞችንም ስለሚጎዳ ለመንግሥት ብቻ ሊተው አይገባም ብለዋል።

አቅርቦትን ከፍ ማድረግ በአንድ ሌሊት የሚሆን ጉዳይ አይደለም። ምርት ጊዜ የሚፈጅ፣ ሂደትን አልፎ የሚዘጋጅ ነው።

መንግሥት የወጭ ባጀቱን ያህል የውስጥ ገቢን ሊሰበስብ ይገባል። በአገር ውስጥ የውጭ ምንዛሬ አቅም ላይ የሚስተዋለውን መመናመን ማስተካከል እንደሚገባውም ጠቁመዋል።

በሕገወጥ መንገድ የሚካሄዱ የውጭ አገር ምንዛሬ እና ክምችትን፣ የወርቅ ዝውውርና ክምችት፣ የሐሰተኛ የብር ኖቶች ሕትመትን ለመቆጣጠር ሕገወጥ ድርጊቶችን ለጠቆመም ብሄራዊ ባንክ ማበረታቻ አስቀምጧል። ፍራንኮ ቫሉታን በሕገ ወጥ መንገድ ተግባር ላይ በሚያውሉ ግለሰቦች ላይም የእርምት እርምጃ እንደሚወሰድ ማሳሰቡም ይታወሳል።

# ቢሮው በሦስት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

17 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ አቅዶ ከ18 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ በመሰብሰብ የእቅዱ 106 ነጥብ 8 በመቶ በላይ ማሳካት ችሏል፡፡

አፈጻጸሙ ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ33 ነጥብ 7 በመቶ መጨመሩን አስታውሰው፤ በበጀት ዓመቱ ለመሰብሰብ ከታቀደው አጠቃላይ ገቢ የ26 ነጥብ 5 በመቶ የሚሸፍን መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

ገቢ ግብርን ለማስፋት አዳዲስ የገቢ አማራጮችን ለመጠቀምና የማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ አፈጻጸሙን ለማሻሻል እየተሠራ መሆኑን አመልክተው፤ ባንኮች ውል ሲዋዋሉ የውሉን አንድ በመቶ ለከተማ አስተዳደሩ እንዲገባ ማድረግ የተቻለ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር የሚገባውን ከውልና ማስረጃ አገልግሎት የሚገኘውን የከተማዋን ገቢ ወደ ከተማ አስተዳደሩ እንዲመለስ ጥረት እየተደረገ እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

በተጨማሪም የፓርኪንግ አገልግሎት እና ከንግድ ተሽከርካሪ ሽያጭ በሚሰበሰብ ገቢ ተመን ላይ ማሻሻያ ተደርጓል ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ ከቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት ሽያጭ ሊገኝ የሚገባውን ገቢ ማግኘት እንዲቻልም ወቅታዊ የገበያ ዋጋን መሠረት ያደረገ የግብር አከፋፈል ሥርዓት ተፈጻሚ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡

ግብርን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ አሳውቆ መክፈል መቻሉና ግብር ከፋዮች ባሉበት ሆነው በባንክ በቴሌ ብር ግብራቸውን መክፈል መቻላቸው፤ አዳዲስ የገቢ አማራጮችን አሟጦ ለመጠቀም የተደረገው ጥረት የገቢ መጠኑ እንዲያድግ ካስቻሉ ምክንያቶች መካከል መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የቢሮውን አገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን የተሠሩ ሥራዎችም በግብር ከፋዩና በፈጻሚ መካከል ያለውን ግንኙነት መቀነስም በመቻሉ ሥስነምግባር ጉድለትን ማሻሻል ማስቻሉንም አመልክተዋል፡፡

ቢሮው አገልግሎት አሰጣጡን ለደንበኞች ምቹ ለማድረግ ግብር ከፋዩ የሚስተናገድባቸውን ቢሮዎች ለማሻሻል የሚያስችሉ ተግባራት እየተከናወኑ ነው ያሉት አቶ ሙሉጌታ፤ የግብር ከፋዩን ጊዜ፣ ጉልበትና ገንዘብ ለመቆጠብ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂ ውጤቶችን መተግበር፣ ደንበኞች ጥቆማ ለመስጠት ወይም ማብራሪያ ለመጠየቅ ሲፈልጉ በ7075 የድምጽና አጭር የጽሑፍ መልእክት መቀበያ ማዘጋጀትና ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶችን ግብር ማስታወቂያ በከፋዮች የስም ፊደል ቅደም ተከትል እንዲሆን ማድረግ ከተወሰዱት እርምጃዎች መካከል የሚጠቀሱ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡

የቢሮው የገቢ አሰባሰብ ከእቅድ አንጻር አበረታች ውጤት የተመዘገበበት መሆኑን ያመለከቱት ቢሮ ኃላፊው፤ በየደረጃው ያለው አመራር አገራችን ካለችበት ተጨባጭ ሁኔታ አንጻርና ከተማ አስተዳደሩ ያለድጎማ በጀት ለሕብረተሰቡ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት ከፍተኛ የበጀት ፍላጎት መኖሩን በመረዳት ለውጤታማነቱ የበኩሉን ጥረት እንዲያደርግ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# አገልግል

የቅዳሜ መጽሄት



‹‹መቀመጥ ይገድላል››

ገጽ 8

የቡራዩ የልዩ ተሰጥኦ ማበልፀጊያ- ክህሎትን የመሻት ግብ

ገጽ 14



‹‹በምዕራባውያኑ ድርጊት ዋጋ ብንከፍልም፤ ትግላችን በራሱ አፍሪካውያንን ያነቃል››

- አቶ ሽፈራው ወልደሚካኤል
የቀድሞ የፍትህ ሚኒስትር

ገጽ 6



በእሾህ የተከበበችው አበባ

ገጽ 18

## በውስጥ ገጾች


ኢትዮጵያን የተሸከሙ ወርቃማ ትከሻዎች ገጽ 9

ቅንዓት ሲመቻቸው ገጽ 12


ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## “በምዕራባውያኑ ድርጊት ዋጋ ብንከፍልም፤ ትግላችን በራሱ አፍሪካውያንን ያነቃል”

- አቶ ሽፈራው ወልደሚካኤል
የቀድሞ የፍትህ ሚኒስትር

ማህሌት አብዱል


ፎቶ፡ በገበበ ገብሬ

የተወለዱት ከአዲስ አበባ 50 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሰንዳፋ ከተማ አቅራቢያ በምትገኘው በረህ ወረዳ ውስጥ ነው። የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደብረብርሃ ከተማ በሚገኙት አፄ ዘረ-ያቆብና ሃይለማርያም ማሞ በተባሉ ትምህርት ቤቶች ተከታትለዋል። በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርሲቲ ገብተውም በህግ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ በደርግ ስርዓተ መንግስት በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ በህግ መምሪያ ምክትል በመሆን ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ጊዜ ከሰሩ በኋላ ነፃ የትምህርት እድል አግኝተው በመሄድ በአሜሪካ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ በህግ የማስተርስ ዲግሪያቸውን ያዙ። በተጨማሪም ሊስተርን በሚባል ሌላው ዩኒቨርሲቲ በኦርጋናይዜሽናል ሊደርሺፕ ሁለተኛውን የማስተርስ ዲግሪያቸውን ሰርተዋል።

እንግዳችን በትምህርት ላይ ሳሉ የመንግስት ለውጥ ቢመጣም በቀጥታ ወደ አገራቸው በመመለስ በኮሎኔል ፍስሃ ይመራ በነበረው የጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ውስጥ የህግ መምሪያ ኃላፊ ሆነው ተመደቡ። ሁሉንም የደርግ ህጎች ለ17 ዓመታት በማርቀቅና በማዘጋጀት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ ሲሆን የማዕከላዊ ፕላን ወይም ዘመቻ መምሪያ የሕግ ክፍል ኃላፊነትንም ደርበው በመስራት ያበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ እንደሆነ ይጠቀሳል። የአሸባሪው ትህነግ መንግስት በትረ-ስልጣኑን ከተረከበ በኋላም ለስልጠና ከሄዱበት እንግሊዝ በአዲሱ መንግስት ተጠርተው የፍትህ ሚኒስትር ሆነው ለአንድ ዓመት ያህል አገልግለዋል። ሆኖም ቃል በተገባላቸው መሰረት በነፃነት የሚሰሩበት ምህዳር ባለመኖሩ በገዛ ፍቃዳቸው ስልጣናቸውን ለቀቁ።

የራሳቸውን ቢሮ ከፍተው ለሚድሮክና ለመሰል ትልልቅ ኩባንያዎች የህግ አማካሪ ሆነው ለረጅም ዓመት የሰሩት እኚሁ ሰው በኋላም የማማከር ስራቸውን እርግፍ አድርገው በመተው በበጎ አድራጎት ላይ ከሚሰራ “ኮምፓሽን” ከተባለ ድርጅት ጋር በመሆን የበርካታ ወላጅ አልባ ህፃናትን ህይወት የመታደጉ ስራ ላይ ሙሉ ለሙሉ ትኩረታቸውን አደረጉ። በኢትዮጵያም አልፈው በኬኒያ፣ ታንዛኒያ፣ ቶጎ፣ ቡርኪናፋሶና መሰል የአፍሪካ አገራት ላይ የህፃናት መርጃ ተቋማትን በማቋቋም ለአህጉሪቱ ጭምር የራሳቸውን አስተዋፅኦ ያበረከቱ ሰው መሆናቸውን ይጠቀሳል። እኛም በተለያየ እውቀትና ሙያ በየደረጃው አገራቸውን ያገለገሉትን የቀድሞ የፍትህ ሚኒስትር አቶ ሽፈራው ወልደሚካኤልን የዛሬው €€የዘመን እንግዳ« አድርገን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በደርግ መንግስት ለምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርነት ታጭተው እንደነበር ሰምተናል፤ እስቲ ስለዚህ አጋጣሚ ያስታውሱንና ውይይታችንን እንጀምር?**

**አቶ ሽፈራው፡-** ልክ ነው፤ ግን ይህ የሆነው የደርግ መንግስት ሊወድቅ ሲል ነው። በወቅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ እንደሚመጣ አስቀድሞም ታውቆ ስለነበር አገሪቱን በተለያየ የስራ መስክ የሚያዘጋጁ ሰዎች ተመርጠው ነበር። ይህ ደግሞ የተደረገው በውጭ ኃይሎችና በመንግስት ነው። ብቻ እንዴት እንደሆነ ባላውቅም እኔን ጨምሮ ስድስት ሰዎች ተመለመልንና እንግሊዝ አገር ለስልጠና ተላክን። እንዳልኩሽ ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ስለሚመጣ መሰረታዊ የመዋቅር ዝግጅት ለማድረግ ታስቦ ነው። በዚያ መሰረት በህጉ ዘርፍ እኔ ነበርኩኝ የተመረጥኩት። በነገራችን ላይ ስልጠናው የሚሰጠው የዓለም ባንክ ነበር።

አስቀድሜ እንዳነሳሁልሽ ደርግ እንደሚወድቅ ራሳቸው የደርግ ሰዎች ተገንዝበው ስለነበር ሰው ማደራጀት ጀምረው ነበር። አዲስ መንግስት ሊቋቋም ሲያስቡ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እንድሆን በአቶ ፋሲካ በኩል ጥያቄ ቀርቦልኝ ነበር። በመሰረቱ እስከአሁን ድረስ ይህንን ሚስጥር እኔ ለማንም አልተናገርኩም ። በቅርቡ የአቶ ፋሲካ መፅሐፍ ሲመረቅ መድረክ ላይ ነው የተነገረው። ግን እኔ ፈቃደኛ አልነበርኩም፤ ምክንያቱም የማልሰራበትን ቦታ መያዝ አልፈልግም። ብዙ ጊዜ እንዳውም ፖለቲካ ውስጥ መግባትም ስለማልፈልግ የፖለቲካ ድርጅቶች እንድኖር አይፈልጉም ነበር። ግን ዋናው ሰውዬ (ኮሮኔል መንግስቱ ሃይለማርያም) ባልታወቀ ምክንያት ይወዱኝ ነበር። ሁልጊዜ ይህንን ሰውዬ አትንኩት እያሉ ይከራከሩልኝ ነበር። በዚህ ምክንያት እንደሌሎቹ ታስሬም ሆነ ጉዳት ደርሶብኝ አያውቅም። እኔ ለስልጠና እንግሊዝ ሳለሁ ግን የደርግ መንግስት ወደቀ።

**አዲስ ዘመን፡- በኢህአዲግ መንግስት የፍትህ ሚኒስትር ሆነው ተሹመው ነበር፤ ይህስ እንዴት ነበር የሆነው?**

**አቶ ሽፈራው፡-** የደርግ መንግስት እንደወደቀ ወዲያውኑ ደግሞ እዛው እንግሊዝ ሆኜ የሽግግር መንግስቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው አቶ ታምራት ላይኔ ደውሎ ‹‹በህገ-መንግስት የሚረዳን ሰው ስለምንፈልግ እርዳን›› አለኝ። እኔ ግን የእኔን ጓዶች በሙሉ ገድላችሁ፤ አስራችሁ፤ አባራችሁ እያለ እኔንም ከእነሱ ጋር ልትቀላቅለኝ ስለሚሆን አልመጣም አልኩት። እሱም ‹‹ግዴለም እኛ ስለእርሶ በደንብ እናውቃለንና መጥተው እንዲያግዙን እንፈልጋለን፤ የፍትህ ሚኒስቴር እንዲሆኑም መርጠኖዎታል›› አለኝ። እኔ ግን ነገሩ ጥሩ ነው፣ ሆኖም ስሜን ነው ወይስ ሙያዬን ነው የምትፈልጉት? ብዬ ጥያቄ አቀረብኩለት። በመሰረቱ እኔ ደርግም ስድስት ቦታዎች ላይ ሚኒስትር እንድሆን ጠይቆኝ ነበር። እኔ ግን ፖለቲካ ውስጥ መግባት ስለማልፈልግ አሻፈረኝ ነው ያልኩት። ለእኔ ስልጣን አዲስ አለመሆኑን፣ በስሜ ለመነገድ ከሆነ እንደማልመጣ በነፃነት የሚያሰሩኝ ከሆነ ልመጣ እችላለሁ ብዬ ነገርኳቸው። እንዳውም እዚህ ስመጣ በፅሁፍ ተደራድሬ ነው የመጣሁት።

የሚገርምሽ ወዲያውኑ ከኢትዮጵያ ኢምባሲ ማርቼዲስ ተልኮ ነው የተቀበሉኝ። እናም በስምምነታችን መሰረት ለአንድ አመት ያህል በነፃነት የፍትህ ሚኒስትር ሆኜ ብሰራም እየቆየ ሲሄድ ሊያሰሩኝ ባለመቻላቸው በፈቃዴ ለቅቄ ወጣሁ። አስቀድሜ የለመንኳቸው ፍትህን ከሰጣችሁኝ እኔ ልስራው፤ ሳጠፋ ቅጡኝ በሚል ነው። በዚያ ተስማምተን ነበር የመጣሁት፤ ግን እንዳሰብኩት አልሆነም፤ ፈፅሞ ሊያሰሩኝ አልቻሉም። በነገራችን ላይ እኔ በድህነት ነው ያደኩት። ድህነት ፎቅና ምድር ቤት ሰርቶብኝ ስለኖርኩኝ ስልጣን ባጣ ምን እሆናለሁ ብዬ አልፈራም። እውነቴን ነው የምልሽ መራብን አውቃለሁ፤ መቸገርንም እንዲሁ። ለእኔ ምንም አይደንቀኝም፤ ውስጤ ግን ቆራጥ ነው።

ለነገሩ እንደፈለኩኝ ማገልገል ካልቻልኩኝ ስልጣን ላይ መቆየቱ ለእኔ ትርጉም የለውም። ስልጣን እንሰጥሃለን ስላሉኝ ብቻ በማላምንበት ነገር ልሰራ አልችልም። ለዚህም ነው ስራዬን በገዛ ፍቃዴ ለቅቄ ለቀናት ቤቴ ቁጭ ነው ያልኩት። ከዚያ በኋላ ግን የጥብቅና ፈቃድ ቤቴ ድረስ ተላከልኝና የህግ ቢሮ ከፍቼ በህግ አማካሪነት ቀጠልኩኝ። ለአላሙዲን ድርጅት ለሆነው ሚድሮክ ኩባንያና ገብረየስ ቤኛ ለተባለ ባለሃብት የህግ አማካሪ ሆኜ ሰርቻለሁ። የሚገርምሽ በዚያ ወቅት በመንግስት ቤት በወር አገኝ የነበረውን በቀን አገኝ ነበር። ስለዚህ ስልጣን በመልቀቄ ያጣሁትም፤ የሚቆጨኝም ነገር የለም።

ደግሞም የኢትዮጵያ ዋና ችግር ኢኮኖሚ ነው ብዬ አላምንም። ለነመለስም ያልኳቸው ይህንኑ ነው። ዋናው ችግር የግለሰብና የህዝብ የፍትህና የመብት ጥያቄ እንደሆነ ነው የማምነው። ለዚህ ነው አስተዋፅኦ አበረክት ይሆናል ብዬ ኃላፊነት የተቀበልኩት። እንዳለመታደል ሆኖእነሱ ይዘውት የመጡትን ዓላማ ስለነበር የሚተገብሩት አልተቻለም። በነገራችን ላይ ለእነሱ ስልጣን ስል እኔነቴን አልሸቅጥም ብዬ ስወጣም ከኢህዴግ ምንም አይነት መግለጫ ሳልሰጥና ወደ ውጭ ሳልሸሽ የቆየሁት። ብዙ ጊዜ ሰዎች ውጭ ሄደው በሚዲያ መግለጫ ይሰጣሉ። እኔ ግን አላደረኩትም።

**አዲስ ዘመን፡- በማህበራዊና በበጎ አድራጎት ስራዎትም ይታወቃሉ፤ እስቲ ስለዚህ ስራዎት በጥቂቱ ያጫውቱን?**

**አቶ ሽፈራው፡-** በህግ ማማከሩ ስራ ላይ ሳለሁ አንድ ደንበኛዬ ከአሜሪካ ይመጣና እዚህ ×ገር የድሃ ድሃ የሆኑ ልጆችን መርዳት ስለምፈልጉ ለእነሱ የህግ አማካሪ እንድሆን ጠየቀኝ። ኮምፓሽን ኢንተርናሽናል የተባለው ይሄው ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ በርካታ ህፃናትን ነው የሚረዳው። እኔ ደግሞ እንዳልኩሽ በድህነት ያደኩኝ በመሆኔ ሃሳቡን ወደድኩትና አብሬያቸው መስራት ጀመርኩኝ። በኢትዮጵያ ውስጥ ድርጅቱን በማቋቋም ሂደት ውስጥ የተሳተፍኩኝ ሲሆን በዚህ ምክንያት የጥብቅናውን ስራ እርግፍ አድርጌ ተውኩት። ያ ሲሆን ደግሞ ገቢዬ በ21 በመቶ ቀነሰ። ግን የምፈልገው ስራ በማግኘቴ ደስተኛ ሆንኩኝ። በመሰረቱ በሂደት ገቢዬም አደገ፤ ቤትም አስቀድሜ ሰርቼ ስለነበር ምንም አልተቸገርኩም።

እንዳውም ወደ ተለያዩ የአፍሪካ አገራት ልከውኝ በህይወቴ ትልቅ የምለውን ስራ ነው የሰራሁት። ታንዛኒያና ኬኒያ ላይ ተቀምጠን ታዛኒያ፣ ጋና፣ ቡርኪናፋሶ፣ ቶጎና ሌሎች አገራት ላይ በመዘዋወር የህፃናት መርጃ ማዕከል አቋቋምኩኝና የህፃናት ጉዳይ ማማከር ስራ እሰራ ነበር። የሚመለከተው አካላት በሙሉ በልጆች ጉዳይ ላይ ትኩረት እንዲሰጡ በመላው አፍሪካ ሰፊ ንቅናቄ ነው ያደረግነው። በነገራችን ላይ በልጅ ውስጥ ልጅን ብቻ ከማየት የበለጠ ስህተት የለም ብዬ ነው የማስበው፤ ልጅን ልጅ አድርጎ የሚያስቀር እይታ እርግማን ነው። ስለዚህ በዚህ ስራ በቆየሁባቸው ዓመታት መንግስታትም ሆነ የሚመለከታቸው አካላት ለልጆች የሚገባቸውን ክብርና ስፍራ እንዲሰጡ ነው ብዙ ጥረት ያደረኩት።

**አዲስ ዘመን፡- በአገሪቱ አሁን ላይ ያለው ህገ-መንግስት ለሚከሰቱ ብሔር ተኮር ግጭቶችና ችግሮች እንደ አንድ መንስኤ ይጠቀሳል። እርሶ በሶስቱ መንግስት ህግ ስርዓት ውስጥ እንዳለፈ ሰው በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ?**

**አቶ ሽፈራው፡-** እኔ በመሰረቱ ብሔርተኝነት ወይም ዘረኝነት የሚባለውን ነገር አሸባሪው ትህንግ ፈጠረው ብዬ አላምንም፤ ይልቁኑ ቤንዚን ነው ያርከፈከፈበት። ምክንያቱም ስሜቱ ነበረ፤ የነበረው ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ነው። በተለይ አንዱ ብሔር ከፍ በማድረግ ሌላውን ዝቅ የማድረጉ ነገር ከአዕምሮ ስፋት አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተፈጠረ ነው። እኔ ለምሳሌ በአባቴ ኦሮሞ ነኝ፤ በእናቴ አማራ ነኝ፤ በዚያ ወቅት ይደረግ የነበረውን ነገር ጠንቅቄ አውቃለሁ። በተጨማሪም እኔ በአባቴ የባላባት ልጅ ስለነበርኩ ሰፊ መሬት ነበረን፤ ከብቶቻችን ተቆጥረው የማያልቁ ነበሩ፤ ግን ደጃች ውቤ የሚባሉ ሰው መጥተው በአንድ ቀን መሬታችንን ወሰዱት። ይህንን ያነሳሁልሽ ቀድሞም ቢሆን የመደብ ልዩነት ያመጣውን ችግር እንድትገነዘቢልኝ ነው።

በሌላ በኩል በልጅነቴ የእናቴ አገር ሄጄ ሳድግ በሌላኛው ብሔር ላይ የሚነሱት አንዳንዶቹ ንግግሮች ጨርቅ የሚያስጥሉ ናቸው። እኔ በመሰረቱ በኢትዮጵያውነቴ የማምን ሰው ነኝ። ግን አንዱ በሌላው ላይ የበላይ ልሁን ብሎ የሚያደርገውን ነገር ድሮም ቢሆን አየው ነበር። ይሄ ድንቁርና የሚባለውን ቃል አልወደውም እንጂ አዕምሮ ያለመስፋት ያመጣው ችግር ነው። እነ መለስ ይህንን ስሜት አልፈጠሩትም፤ እንዲገንና ለራሳቸው ዓላማ ሰውን የማባያ ጉልበት ሰጡት እንጂ!። ይህ የብሔርተኝነት ጉዳይ ከስር ከመረመርሽው በአጠቃላይ ሴጣናዊ ሃሳብ የያዘ ነው። ያንን ያመጡት እነሱ ሌላውን በማጣላት ስልጣን ለማቆየት ሲሉ ነው።

### ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

ደግሞም እንዳየነው በኢኮኖሚም ሆነ በፖለቲካ የበላይ ሆነው የቆዩት በዚህ ዘዴ ነው። ግን እኛ ውስጥ የነበረን ነገር አቀጣጠሉት እንጂ አልፈለሰፉትም የሚለውን ነገር እንድታሰምሪበት እፈልጋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ህገ-መንግስቱ በእርግጥ የመብት ጥያቄዎችን ቢመልስም በተጨባጭ መሬት ላይ ተግባራዊ ሆኗል ብለው የማያምኑ ሰዎች አሉ። የእርሶ ሃሳብ ምንድን ነው?**


**አቶ ሽፈራው፡-** በነገራችን ላይ ሶስተኛ ዓለም የምንባለው አገራት አንዱ ምልክታችን በተፃፈውና በሚተገበረው ህግ መካከል ያለው ፍቺ የተለያየ መሆኑ ነው። ይህንን አይነት ችግር የሚታየው በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም፤ በአብዛኛው የሶስተኛ ዓለም አገራት የህግ አፈፃፀም ሁኔታ ይሄ ነው። ህገ-መንግስት መፃፍ አያስቸግርም፤ እንደጨሌ ጌጥ ከዚህም ከዚያም ወስዶ መፃፍ ይቻላል። በመሰረቱ በንጉሱም ጊዜ በተለይ የተሻሻለው ህገ-መንግስት በእርግጥ ህይወት ብናለብሰው ኖሮ ጥሩ የሚባል ነበር፤ ይህ ሲባል የሚሻሻል ነገር አልነበረም ማለቴ አይደለም። ደግሞም በዛሬ አዕምሮ ትላንትን መፈረጅ ጥፋት ይመስለኛል። በደርግም ጊዜ በነገራችን ላይ ህገ-መንግስቱን እኛው ነን የሰራነው። የማንስማማባቸው የህግ አንቀፆች ነበሩ፤ እኔ በግሌ የማልስማማባቸውን አንቀፆች በፅሁፍ አቅርቤ ነበር። ያ ህገ-መንግስት እንዳለ እንኳን ቢተረጎም ኖሮ በአግባቡ መጥፎ አልነበረም። በጥቅሉ ህገ-መንግስቶቹን ብቻ መፈረጅ ለእኔ ይከብደኛል፤ ምክያቱም የተፃፉትን እንኳን በአግባቡ መተግበር ባለመቻላችን ነው። ዋናው ነገር ህይወት መስጠቱ ላይ ነው።

እኔ ህግን እንደመኪና ከመነዳሪ (ጎማ) ነው የማየው። የመኪና ከመነዳሪ አየር ከሌለው ራሱንም አይችልም፤ አየር ከተነፋበት አውሮፕላን እንኳን ሊያሳርፍ ይችላል። ምክንያቱም የአየሩ ጥንካሬ ነው የከመንዳሪው ወይም የጎማው ጥንካሬ። ምንማለት ፈልጌ መሰለሽ፤ መንግስት፤ ህዝቡም ሆነ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ልክ እንደጎማው ለህጉ አየር ቢሆኑት አሁን የምናየው ችግር ባልተፈጠረ ነበር። እርግጥ ነው፤ ይህንን የምልሽ እንደህግ ሰው ሆኜ ሳይሆን እንደማንኛውም ሰው ከሚሰማኝ ስሜት ተነስቼ ነው። እንደተባለው አሁን ያለው ህገ-መንግስት የሚያከራክሩ አንቀፆች አሉት፤ በተለይ አንቀፅ 39 በሁሉም ሰው እንደሚብጠለጠል ይታወቃል፤ እኔም አልወደውም። ግን ዋናው ችግር እሱ ሳይሆን ሲጀመር ህጉ የተፃፈው ለአሜሪካ፤ ምዕራባውያኑንና ዓለም ባንክን ለማስደሰት ነው። ስለዚህ ለሌላ የተፃፈ ህግ እርስ በርስ ቢያባላን ሊገርመን አይገባም። ምክንያቱም አላማው ይህ ስለነበር ነው።

በመሰረቱ እነሱ የፈለጉትን ሁሉ ሲጫንብን ጭነቱን ለማራገፍ የሚችል ህዝብ አልፈጠርንም። የራሱን እድል በራሱ የሚወስን ትውልድ አላፈራንም። ስለዚህ በህገ-መንግስት ላይ ትችት ከማቅረብ ይልቅ አተገባበራችንን ብንፈትሽ የተሻለ ይመስለኛል። ምክንያቱም ችግሩ ወረቀቱ አይደለም። ለምሳሌ ከወጡ ከ100 ዓመታት በላይ የሆናቸው የሌላ አገር ህገ-መንግስቶች አሉ፤ እነዚህ አገራት አሁንም ለዛሬ እንደሚመች አድርገው ነው ተፈፃሚ የሚያደርጉት። ይህንን የሚደርገው ደግሞ የዛሬው ሰው ነው። ህግን ህያውና አስፈላጊ የሚያደርገው ሰው ነው። ለዚህ የሚሆን ወይም ይህንን መተግበር የሚያስችል ሰውም ሆነ ተቋማት አልፈጠርንም። እኛ ሳንዘጋጅ የሌሎችን ወስደን ለመተግበር በምናደርገው ጥረት ውስጥ ነው ችግር እየተፈጠረ ያለው። ልክ እንደ እግረኛ መሻገሪያ መንገድ ህጉንም አላከበርነው፤ ምክያቱም የአዕምሮ ዝግጅት የሌለን በመሆኑ ነው። እኔ እንዳውም ስለህገ-መንግስት ይህንን ያህል መሟገት ቅንጦት ይመስለኛል።

**አዲስ ዘመን፤- ግን እኮ በዚህ ህገ-መንግስት ምክንያት ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲከናወን እንደነበር ይታወሳል፤ ይህንን እንዴት እንደቅንጦት እናየዋለን?**

**አቶ ሽፈራው፡-** በነገራችን ላይ የኢትዮጵያ ሁኔታ ዋጋ ቢያስከፍልም ሁልጊዜ እየተሻሻለ ነው የመጣው። በንጉሱ ጊዜ የነበሩ መሰረታዊ የህግ ክፍተቶች በደርግ ጊዜ ተለውጠዋል። ለምሳሌ የአርሶ አደሩ የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ ተመልሷል፤ ንብረት የማፍራት መብት ደግሞ በኢህአዴግ ዘመን ተመልሷል። ባለፉት 27 ዓመታት የመጣውን ለውጥ መካድ አይቻልም። በአጠቃላይ በየጊዜው እየተሻሻሉ የመጡ ነገሮች አሉ። በተለይ በኢህአዴግ ዘመን ህዝቡ መብቱን ሲያውቅ አይኑ ተከፈተ፤ ለምን? ብሎ መጠየቅ ጀመረ። ይህ ደግሞ መልሶ ለአሸባሪው ሕወሓት መንግስት ችግር ሆነ። ልክ እንደእነሱ ሁሉ ሌላውም ህዝብ ከአገሪቱ ሃብት የመጠቀም መብት



ጥያቄ አቀረበ። ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞቹም ይታሰሩ የነበሩት የሚደረገውን ነገር ስለሚያጋልጡ ነው።

በተጨማሪም ኢኮኖሚውንም ሆነ ፖለቲካውን በሙሉ እኛ ብቻ እንቆጣጠር ማለታቸው ነው በህዝብ ዘንድ ቅሬታ የፈጠረው። በመሰረቱ እነሱ መብትን በህገ-መንግስቱ እንዲካተት ያደረጉት አምነውበት አይመስለኝም። አስቀድሜ እንዳልኩሽ በራሱ ህግን ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችል ዝግጁነት አልነበረም። ለአዲሱ ትውልድ የሚመጥንና ጥያቄውን ለመመለስ የሚስችል ስርዓትም ሆነ አካል መፍጠር አልተቻለም። በድሮው አዕምሮና ሁኔታ ላይ ነበር አዲስ ሃሳብ ለመጨመር ትግል ይደረግ የነበረው። ከዚህ አንፃር ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ስለአዕምሮ ለውጥ ብዙ ይናገራል፤ ጭንቅላት ላይ ለመስራትም እየሞከረ ነው ያለው፤ ምንያህል እንደተሳካለት ባላውቅም ግን ይሞክራል። እንደዚህ አይነት ጥረት ባለፉት ሶስት መንግስታት አላየሁም። ዶክተር አብይ ግን በሰው አዕምሮ ላይ መስራት እንደሚገባ ያምናል፤ ይናገራል፤ ፅፏልም። የትኛው መሪ ነው ታዲያ ይህንን ያደረገው?። ኢህአዴግ ዋና ትኩረቱ ምዕራባውያን መንግስታት ማስደሰት ነበር። ለእነሱ ደስ የሚላቸውን የደርግና እዚህ ደግሞ የፈለገውን ይሰራል፤ ያ ነው እንግዲህ ተቃርኖው የነበረው። እንዳልሽው የሰብአዊ መብት ጥሰቱ በሽበሽ ሆኖ ነበር።

**አዲስ ዘመን፡-የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የምዕራቡ ዓለም አገራት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ገብተው የሚያደርጉትን ጫና እንዴት ይመለከቱታል?**

**አቶ ሽፈራው፡-** የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በአጠቃላይ የፖለቲካ ውጤት እንደሆነ አውቃለሁ። በምዕራባውያኑ የሚመራው ይህ ድርጅት አንዲት እናት ጡቷን የገዛ ልጇን እንዳታጠባ ከልክሎ ለሌሎች ልጆች እንድታጠባ የሚያስገድድ ድርጅት ነው። በአባይ ውሃ ላይ ያደረጉት ይህንን ነው። በነገራችን ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘ ‹‹ትውልድም እንደአባይ›› የሚል ፊልም አሰርቻለሁ። እናም ምዕራባውያኑም ሆነ ተመድ ውስጥ ያሉ አገራት ይህንን ያህል የደነቀረ ህሊና ያላቸው ናቸው። ምዕራብውያኑ በተመድ ውስጥ የራሳቸውን ሰዎች በመሰግሰግ የሚፈልጉትን ጉዳይ ብቻ እንዲፈፀም ሲያደርጉ ኖረዋል። በመሰረቱ ድርጅቱ ‹‹የተባበሩት መንግስታት›› ይባል እንጂ ከስም ውጭ የሌለ ተቋም ነው። ይቅርታ አድርጊልኝና ምዕራባውያኑ ድርጅቱን ደፍረውታል፤ አዋርደውታል። ስለዚህ በእነሱ ህሊና የሚንቀሳቀስ ስለሆነ ጥሩ ነገርም ቢያመጡ እኔ ጥሩ ነው ብዬ ለመቀበል እቸገራለሁ። ምክንያቱም ሁልጊዜም ከጥሩ ስራቸው በስተጀርባ ሌላ ፍላጎትና ተንኮል በመኖሩ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በአፍሪካ ህብረት በኩል ከአሸባሪው ትህነግ ጋር የሚደረገው የሰላም ንግግርስ ምን ያህል ውጤታማ ይሆናል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ሽፈራው፡-** በአፍሪካ ህብረት በኩል መነጋገር የኢትዮጵያ መንግስትም አቋም ነው። እነሱ ይህንን ያሉት ተገደው እንጂ ፈልገው ነው ብዬ አላምንም። ምዕራባውያኑ በአፍሪካ ህብረት በኩል የሚደረገውን ድርድር የተቀበሉት ምርጫ ስላጡ ነው። ቀድሞም ቢሆን የእነሱ እቅድ ይህ አልነበረም። በተለይ እንግሊዝ የምትባል አገር ድሮም ቢሆን ኢትዮጵያ እንዳታድግና በሃብቷ እንዳትጠቀም ያልማሰችው ጉድጓድ የለም። የአባይ ወንዝ እንዳንጠቀምበት ከማድረግ ጀምሮ የቀለበት መንገዱም እንዳይጠናቀቅ ብዙ ጥረት አድርጋ እንደነበር ይታወቃል። እንደሚታወቀው ቀለበት መንገዱ መግጠም ያልተቻለው በእንግሊዝ አሻጥር ምክንያት ነው። አሁንም ቢሆን የአዲስ አበባ አብዛኛውን መሬት ያየዘችው እንግሊዝ ነች። የኢትዮጵያ ካርታ በዚህ መልኩ እንዲሰራ ያደረጉትም እነሱ ናቸው።

በነገራችን ላይ ቅኝ ግዛት እኮ ከሌሎቹ የአፍሪካ ሃገራት በላይ ክፋቱ አግጥጦ የሚታየው እኛ ላይ ነው። ምክንያቱም አልሸነፍ ባይነታችንን ቀድመው ስለሚያውቁ በቻሉት ሁኔታና አጋጣሚ እኛን ከመጉዳት ተኝተው የማያድሩ በመሆናቸው ነው። ምዕራባውያኑ ስለሰብአዊ መብት ለመናገር የሞራል ብቃት የላቸውም። ዩክሬን ውስጥ ከራሺያ ጋር ከሚያዋጓቸው ሰዎች መካከል አልቃይዳዎች አሉበት። የአሜሪካ ህዝብና መንግስት ገንዘብ ከፍሎ ነው የሚያዋጋው። ይህንን ታዲያ እያየን የሰብአዊ መብትን ያከብራሉ፤ ስለሰብአዊ መብት ይጨነቃሉ ተብሎ አይታመንም። በአጠቃላይ እነሱ ለሚያወጡት ሪፖርት ምንም ትኩረት አልሰጠውም።

በመሰረቱ የሰላም ውይይቱ ውጤታማ ስለመሆኑ ጥርጥር አለኝ፤ ይህንን የምልሽ በአሸባሪው ትህነግ በኩል ብቻ ሳይሆን የምዕራባውያኑ ብዙ እጅ ስላለበት ነው። በተለይ አሜሪካኖች ጉዳዩን ሙጭጭ አድርገው የያዙት በመሆኑ ከስኬት ይደርሳል ብዬ አላምንም። ይህም ቢሆን ግን በእኛ ላይ የሚደረገው ተፅዕኖና በብዙ መከራ ውስጥ ብንሆንም ለቀረው የአፍሪካ ህዝብ የምዕራባውያን ማንነትን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። እኛ ዋጋ ብንከፍልም፤ ትግላችን በራሱ ሌሎችን አፍሪካውያንን ያነቃል። ሰው እንወዳለን ቢሉም፤ እነሱ ሰብአዊ መብት ከራሳቸው ውጪ አያውቁም።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ደግሞ እስቲ ከፃፋዋቸው አራት መፅሐፍቶች መካከል የተወሰኑትን ይዘት ያብራሩልን?**

**አቶ ሽፈራው፡-** በቅርቡ ከፃፉኩት መካከል አንደኛው ‹‹ የሰው ተመኑ ስንት ነው? ›› የተሰኘ ሲሆን ይህንን መፅሃፍ ልፅፍ የቻልኩት ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በአገራችን እየሆነ ባለው ነገር መተኛት ስላቃተኝ ነው። ሰው እንዴት እንደአፈር በአካፋ ይወረወራል? እርጉዝ ሴት እንዴት ነው ከኖረችበት አካባቢ የምትባረረው፤ የምትታረደው?። ሰው እንዴት ተዘቅዝቆ ይሰቀላል? የሚል ጥያቄ ሁልጊዜ ይመላለስብኝ ነበር። ስለዚህ ሁለት ሃሳቦች ወደልቤ መጥተው አነቁኝ። ለኢትዮጵያ ህዝብ ሰው ምን እንደሆነ የራሴን አስተዋፅኦ ላበርክት ብዬ ነው። ሆኖም መፅሐፉ ገና ገበያ ላይ አላወጣሁትም፤ ምክንያቱም በብዛት እንዲሰራጭ ስለምፈልግና ለዚህ ደግሞ የመገናኛ ብዙሃን ድጋፍ ስለሚያሻኝ ነው። በነገራችን ላይ የሽያጩን ገቢ ሙሉ ለሙሉ የሚውለው ለበጎ አድራጎት ነው።

ወደ ጥያቄሽ ስመለስ ይህንን መፅሃፍ መፃፍ የጀመርኩት የኢትዮጵያ ህዝብ አማኝ ስለሆነ ሰው በፈጣሪ እይታ ምን ይመስላል ከሚል ነው። መፅሃፉ በአብዛኛው አራት ሃሳቦች ነው ያሉት አንደኛው ሰው በእግዚአብሔር እይታ ምን ይመስላል?፤ እግዚአብሔር ሁሉን ከፈጠረ በኋላ ሰውን የፈጠረው ለሰው ልጅ ያለውን ክብር ነው የሚያሳየው። ምክንያቱም እኛ ልክ የክብር እንግዳ እንደምንቀበል ነው ሁሉን ለሰው ልጆች ምቹ አድርጎ ሲጨርስ የፈጠረን። ያ ነው ለሰው ልጅ ያለው ቦታ። ሌላኛው የመፅአፉ ክፍል ሰው በሰው እይታ ምን እንደሚመስል ነው የሚተነትነው። ሰው በዓለም ጦርነት፤ በመደብ ትግል፤ በሃይማኖት ምክንያት እንዴት እንደተጨራረሰ ያሳያል፤ ሰው በሰው እይታ ዥንጉርጉር መሆኑን ይገልፃል። አሁን ደግሞ ብሶ ብሶ በዘር መከፋፈል ጀመረ። ኢትዮጵያ ውስጥ ተበደልን የሚሉ ሰዎች ጉልበት ሲያገኙ በዳይ ሆነዋል፤ ስለዚህ ሁሉም ጥፋተኛ ነው የሚል ሲሆን ከመካሰስ ይልቅ የፊቱን ረስተን ለወደፊቱ ጥሩ እንስራ የሚል ነው።

ሶስተኛው ደግሞ የዓለም አቀፍ ህብረተሰብ ይህንን እብደት አይቶ ልዩ ልዩ ህጎችን አወጣ፤ አራተኛው ክፍል ከመቃብር የገማ ነገር እያመጣን ዛሬ በፈካው አበባ ላይ አናፍስ የሚል ነው። ጥፋት የምንለውን እንዘርዝር፤ ጀግና እንሁን። ጀግንነት ማለት ደግሞ ‹‹ተበድዬ ነበር ይቅርታ አደርጋለሁ››፤ ‹‹በድዬ ነበር ይቅርታ እጠይቃለሁ›› ማለት መቻል ነው። እንማማር፤ ይህንን የሚያሳይ ሃውልት በየክልሉ ይተከል፤ በየትምህርት ቤቱ ወደፊት ላለመካሰስ ቃል ገብተን አርማ እናስቀምጥ። ያለፈው ትላንት ዛሬን አይጠቅምም የሚል ድምዳሜ ነው ያለው።

ሁለተኛው መፅሃፍም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው፤ ርዕሱ “የግለሰብ ሚና” ሲሆን ክፋትን ለመቃወም ፤ መልካምን ለመደገፍ አስተዋፅኦ ማድረግ እችላለሁ፤ እኔ ቁም ነገር ነኝ የሚል ሃሳብ ነው ያለው። እኔ ልዩነት ማድረግ እችላለሁ ብዬ በራሴ አምናለሁ። ይህንንም ስፅፍ መፅሃፍ ቅዱስን ጨምሮ ማዘር ትሬዛንና ዶክተር አብይን እንደምሳሌ ተጠቅሜያለሁ። ዶክተር አብይ የቆሸሸችውን አዲስ አበባን ውብ አድርጓታል፤ ይህ የሚያሳየው አንድ ሰው ብቻውን ለውጥ ማምጣት እንደሚችል ነው። በአጠቃላይ ይህ መፅሀፍ አርአያ የሆኑ ሰዎችን እንደምሳሌ በማንሳት አሁን ያለው ትውልድ የተፈጠረው በዓላማ መሆኑን ተረድቶ ለዓላማው መኖርና ለውጥ ለማምጣት እንዲጨክን የሚያበረታታ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እርሶ በማህበራዊ አገልግሎት ብዙ የሰሩ እንደመሆኑ ለትውልዱ ያሉት ራዕይ ምንድን እንደሆነ ይግለፁልንና ውይይታችንን በዚሁ እናብቃ?**

**አቶ ሽፈራው፡-** አስቀድሜ እንዳነሱት ሰው ልጁን ‹‹አንቱ›› ካላለና ካላከበረ ራሱ ‹‹አንተ›› እና ‹‹አንቺ›› ተብሎ ነው የሚያልፈው። እኛ ልጅን ስናከብር እኛ አንቱ መባላችን ገሃድ ይሆናል። ልጅን ስናሳድግ ገና ከማህፀን ጀምሮ የተከበረ፤ ቁምነገር መሆኑን እየነገርነው ልናሳድገው ይገባል። እኔ እንዳውም የኢትዮጵያ ዋና ችግር ትውልድ ላይ መስራት ያለመሰራቱ ነው ብዬ ነው የማምነው። በተለይ ደግሞ ህፃናት ላይ አልሰራንም። የኢትዮጵያ ንጋት የሚሆነው የኢትዮጵያ ወላጆች ልጆቻቸውን አንቱ ማለት ሲጀምሩ ነው። ትውልድን ‹‹አንቱ ››ያላለ ህብረተሰብ ‹‹አንቱ›› ሳይባል ነው የሚያልፈው፤ አይለወጥም።

ስለዚህ የልጆች ነገር ትልቅ ስፍራ ሊሰጠው ይገባል፤ እናከብራቸው፤ ለቁም ነገር ከጡት መጥባት ጀምሮ እናዘጋጃቸው። ምክንያቱም ሰው የዘራውን ያንኑ ያጭዳልና ነው። በፍቅርና በአክብሮት ያደገ ልጅ ሌላውን ማክበርና መውደድ አይቸገርም። አሁን የምናየው የማንነት ግጭት አይፈጠርም ነበር። የኢትዮጵያ እናቶች ስለሰው ልጅ እኩልነት እየነገሩ ልጆቻቸውን ቢያሳድጉ ኖሮ ትውልዱ በማንነቱ ምክንያት አይጣላም ነበር። መጀመሪያውኑ ጥላቻን ማረፊያ ነው የምናሳጣው። በነገራችን ላይ እኔ ይህንን በማሰብ ነው ሰንዳፉ ላይ የልጆች እድገትና ስልጠና ምርምር ማዕከል የከፈትኩት። በዚህ ማዕከል ላይ ወላጆች፤ የመንግስት ባስልጣናት፤ መምህራን ሄደው ይሰለጥናሉ። ይሁንና አሁን ላይ አመራር በተለወጠ ቁጥር ማዕከሉን ለመውሰድ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሙኛል፤ አሁንም ቢሆን ስራውን ይሰራል። ግን ጉልበቴ ስራው ከማስፋት ይልቅ ቦታውን ለማፅናት መሆኑ ያሳዝነኛል። መስራት ያለብኝን ሳልሰራ የማዕከሉን ህልውና ለማቆየት ሆኗል።

**አዲስ ዘመን፡- ስነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉና በአንባቢዎቼ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ሽፈራው፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

## “መቀመጥ ይገድላል”

እፀገነት አክሊሉ

ለረዥም ሰዓት መቀመጥ ህይወትን አደጋ ላይ እንደሚጥል ምን ያህል ተገንዝበን ይሆን? አዎ ረዥም ሰዓት መቀመጥ በሰው ልጆች ላይ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልፃሉ::

የካናዳው ዘ ዋሽንግተን ፖስት ድረ ገጽ አንድን ጥናት መነሻ አድርጎ እንዳስነበበው በቀን ውስጥ ለ11 ሰዓታት የሚቀመጡ ሰዎች የመሞት እድላቸው በ40 በመቶ ከፍ ይላል:: ይህም ከምንሰራው የሥራ ባህሪ ጋር በተያያዘ ሊከሰት የሚችል መሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል::

**ብዙ መቀመጥ እንዴት ነው ስጉዳት የሚያጋልጠው?**

ዘ ዋሽንግተን ፖስት ያወጣው ፅሁፍ እንዳሰፈረው ለረጅም ሰዓት መቀመጥ እጅግ በርካታ የጤና ችግሮች እንዲከሰቱ ምክንያት ይሆናል:: በዚህም ጡንቻዎቻችን አነስተኛ ስብ ብቻ እንዲያቃጥሉና የደም ዝውውሩ የተፋዘዘ እንዲሆን ያደርጋል:: አሲዳማ ስብ በልባችን ላይ እንዲከማች በማድረግም ለልብ ህመም ያጋልጣል::

የጀርባ አጥንት፣ የዳሌ ጡንቻዎች እንዳይፍታቱ በማድረግ በቀላሉ እንዳንቀሳቀስ ሁሉ ሊዳርገን የሚችልበት እድል ሰፊ ነው::

ለረዥም ሰዓት መቀመጥ በእግር ላይ የተቀላጠፈ የደም ዝውውር እንዳይኖር፣ አጥንቶቻችን ጥንካሬ እንዳይኖራቸው በማድረግ፣ አእምሮ እንዲፈዝ፣ የአንገት ፣ የትከሻና የጀርባ ህመም እንዲከሰት በማድረግ በኩልም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበርክታል::

ተጣጣፊ የጀርባ አጥንት እንዳይኖርና የዲስክ መንሸራተት እንዲከሰትም በማድረግ ረገድ ተጽእኖው በቀላሉ የሚታይ አይደለም::

በመሆኑም ከአምስት እስከ ስምንት ዓመታት ለረዥም ሰዓታት በመቀመጥ ጊዜያቸውን ያሳለፉ ሰዎች በቀን ከአንድ ሰዓት በታች ብቻ ከሚቀመጡ ሰዎች ጋር ሲነፃፀሩ 61 በመቶ የመሞት እድላቸው ሰፋ ያለ ነው::

ለተራዘመ ጊዜ መቀመጥ ወደ ሰውነታችን የገባው ምግብ በተገቢው መንገድ አገልግሎት ላይ እንዳይውል ያደርጋል:: እንቅስቃሴ ሲኖር የሰውነታችን ህዋሳት ምግቡን ለኃይል ምንጭነት እንደሚጠቀሙበት ይሆናል። ረጅም ሰዓት በመቀመጥ ውስጥ ግን እንቅስቃሴ ስለማይኖር በተለያዩ የሰውነታችን ክፍሎች ላይ አላስፈላጊ የሆኑ የስብ ክምችቶች እንዲፈጠር ምክንያት ይሆናል:: ይህም ወደ አላስፈላጊ ክብደት መጨመር ያመራል::

በዚህም ምክንያት የሰውነት ህዋሳት ከምግብ የሚገኙ ስኳር እና ቅባት የመሳሰሉ ንጥረ ነገሮችን እንደ ኃይል ምንጭነት የመጠቀም አቅማቸው እየቀነሰ፤ ሰውነታችን በደም ውስጥ ያለውን የስኳር መጠን የመቆጣጠር አቅሙን እያጣ፤ የስብ ክምችታችንም በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ይሄዳል:: ስለዚህ ለሁለተኛው አይነት የስኳር ህመምና ለደም ግፊት የመጋለጥ እድላችን ይሰፋል:: የደም መተላለፊያ ቱቦዎቹ እየጠበቡ ሲመጡ ደግሞ የደም ግፊቱ እንደሚከሰት ይሆናል::

አብዝቶ መቀመጥ ለክብደት መጨመር በሚያበረክተው አስተዋጽኦ ምክንያት ከክብደት መጨመር ጋር ተያይዞ ለሚከሰቱ በርካታ የጤና ችግሮችም መጋለጥ ይኖራል::

ለረዥም ጊዜ ስንቀመጥ ክብደታችን በተወሰኑ የሰውነት ክፍሎቻችን ላይ ብቻ ስለሚያርፍ ያልተስተካከለ የሰውነት ቅርጽ፣ የጀርባና የአከርካሪ አጥንት መጉበጥ፣ የትከሻ መዛነፍ እንደዚሁም የአንገት መጣመም ሊከሰትብን ይችላል::

እነዚህ ሁሉ ችግሮች የሚያሳዩት ብዙ በተቀመጥን ቁጥር የእድሜያችንን ፍፃሜ እያቀረብን መሆኑን ነው:: ስለዚህ ችግሩን ለመቀነስ የሚቻልበትን መንገድ መፈለግ ይገባል::




በሌላ በኩልም በተለይ በአሁኑ ወቅት በተራዘመ መቀመጥ ምክንያት ሰዎች ለአከርካሪ አጥንት ችግርና ለወገብ ህመም በሰፊው እየተጋለጡ መሆኑ ይነገራል። እነዚህን ሁኔታዎች ለመቀየር ደግሞ አንድ ሰው በሳምንት ያላማቋረጥ ለ 150 ደቂቃዎች ያህል የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ እንዳለበትም ባለሙያዎች እየመከሩ ነው:: በቀን መመገብ ያለብንን 800 ግራም የተመጣጠኑ ምግቦችና አንድ ነጥብ አምስት ሊትር ውሀ መውሰድም መዘንጋት የለበትም::

ሌላው በተለይም በአከርካሪ አጥንታችን ላይ የሚከሰተውን ችግር ለመቀነስ የምንቀመጥበትን ወንበር ምቹ ማድረግ፣ ቀጥ ብሎ መቀመጥ፣ የመሳሳብ ስፖርቶችን ማዘውተር፣ በእግር ጉዞ ማድረግ፣ በስራ ቦታም ቆመንና እየተጓዝን መስራት የምንችላቸው ስራዎች ሲኖሩ መንቀሳቀስ፣ የዮጋ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን ያግዛሉ::

መቀመጥ ይገድላል ብለን ለመነሳታችን ምክንያት የሆነን ደግሞ ባሳለፍነው ሳምንት የተከበረው ዓለም አቀፍ የአከርካሪ አጥንት ቀን ነው። እለቱ “እያንዳንዱ አከርካሪ አጥንት ዋጋ አለው” በሚል መሪ ቃል የተከበረ ሲሆን በተለይም አሁን አሁን በሰዎች ላይ እየተከሰተ ያለው የአከርካሪ አጥንትና የወገብ በሽታ እያሳደረ ያለው ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ችግር ሰፊ ከመሆኑም በላይ ብዙዎች እየተሰቃዩበት ያለ መሆኑን አመላክቷል።

እለቱ መከበር የጀመረው እኤአ በ2008 ሲሆን ዕለቱ በሚከበርበት ጊዜም ሰዎች ስለ አከርካሪ አጥንታቸው ግንዛቤ እንዲኖራቸው እንዲሁም ከአከርካሪ አጥንት ችግር የሚያድኑት እንዴት ነው? የሚለውን ለማስረዳት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ለማስፋት ስለመሆኑም በበዓሉ ላይ ተገልጿል።

ዓለምአቀፉንየአከርካሪቀንአስመልክቶ“ስፓይን ሄልዝ ኢንሼቲቭ ኢትዮጵያ “ ከተለያዩ ተባባሪ አካላት ጋር ባዘጋጀው ዝግጅት ላይ እንደተገለጸው ድርጅቱ በተለይም የአከርካሪ አጥንት ጉዳት ላይ ጤና ሚኒስቴርን ጨምሮ የሴቶች ና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሁም ትምህርት ሚኒስቴርን በማሳተፍና ከእነሱም እውቅና በማግኘት በተለያዩ ትምህርት ቤቶች በመገኘት ልጆች ስለ አከርካሪ አጥንታቸው ጤንነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው በተቻለ መጠንም አከርካሪ አጥንታቸውን የሚንከባከቡበትን መንገድ በመጠቆም እየሰራም ስለመሆኑ የድርጅቱ ተወካይ ወይዘሮ ቢኒያም ግርማ በበዓሉ ላይ ተናግረዋል።

ተማሪዎች ጋር በመሄድ ቀላል የሆኑ ስፖርቶችን እንዲሰሩ አተነፋፈሳቸውን አቀማመጣቸው እንዲከታተሉ የማድረግ ስራ እንሰራለን ያሉት ወይዘሮ ቢኒያም ከመገናኛ ብዙሃን ጋርም በመሆን ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ስለ አከርካሪ አጥንቱ በቂ ግንዛቤን እንዲጨብጥ የማድረግ ስራ እንደሚሰራም አመላክተዋል።

በአከርካሪ አጥንታቸው ላይ ጫና የሚፈጥር ስራን የሚሰሩ ለምሳሌ መካኒኮች፣ በኮንስትራክሽን ስራ ላይ የሚሰማሩ ሰዎች በቀላሉ የአከርካሪ አጥንታቸው ሊጎዳ ስለሚችልና የእነሱ መጎዳት ደግሞ በቤተሰባቸው አልፍ ሲልም በአገር ለይ የሚያደርሰው ኢኮኖሚያዊ ጫና በቀላሉ የሚታይ ስላይደለ ግንዛቤያቸውን የማስፋት ራሳቸውን የሚጠብቁበትን መንገድ የማመቻቸት ስራም እንሰራለን ይላሉ።

ቀኑን ብቻ በማሰብ መዋል የለብንም ያሉት ወይዘሮ ቢኒያም ድርጅቱም አከርካሪ አጥንት ላይ ሲሰራ እንደመቆየቱ በተያዘው ዓመትም እለቱን ከማሰብ በተጨማሪ “ቀጥ በሉ” በሚል መሪ ቃል የተለያዩ ትምህርቶችን እየሰጠ ነው።

እንደ ወይዘሮ ቢኒያም ገለጻ “ቀጥ በሉ” የሚለው መሪ ቃል የተመረጠው የትኛውም ሰው በያለበት ሆኖ ሲሰማው ወይም ሲያነበው ስለ አቀማመጡ እያደረገ ያለውን ነገር ቆም ብሎ እንዲያስብ አልፎም ስለ አከርካሪ አጥንቶች ግንዛቤ እንዲኖር እንዲሁም አስፈላጊውን ጥንቃቄ ወዲያው እንዲወስዱ ለማድረግ ነው።

በዘርፉ ረጅም ዓመት የሰሩት ካይሮፕራክተር ዶክተር ሰላም አክሊሉ እንደሚሉትም የአከርካሪ አጥንት የመላው የሰውነታችን ጤንነት ምሰሶ ነው፤ በመሆኑም አንድ ሰው ሙሉ ጤነኛ ነኝ ለማለት የሚችለው መጀመሪያ የአከርካሪ አጥንቶቹ አቀማመጥ ትክክለኛ ሲሆኑ ነው። ይህም ሲባል የአንድ ሰው የነርቭ ስርዓት ያለው ከራስ ቅሉ አንስቶ በህብለ ሰረሰርና በአከርካሪ አጥንት መካከል ስለሚያልፍ የሰውነታችን ጤንነት ሙሉ ሊሆን የሚችለው የአከርካሪ አጥንታችን ደህናና አቀማመጡም ትክክል ሲሆን ነው።

ኢትዮጵያውያን በአከርካሪ አጥንታችን ላይ ያለን ግንዛቤ በጣም አናሳ ነው፤ ድሮ ሲጋራ ማጨስ ገዳይ ነው በሚባልበት መጠን መቀመጥ ይገላል እየተባልን ነው፤ ነገር ግን ይህንን ብዙ ሰው አያውቅም የሚሉት ዶክተር ሰላም ይህ ማለት ደግሞ ሰው ተቀምጦ በሚውልበት ጊዜ ከመቀመጥም በላይ ደግሞ አንገት ደፍቶ ስልክና ኮምፒውተር ላይ ሲቆይ የነርቭ ስርዓቱ ላይ ላቅ ያለ እክልን እያመጣ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፤ እክል ብቻም ሳይሆን ደግሞ የአተነፋፈስ፣ የጨጓራ መፍጨትና የአንጀት ስራ የልብ ምት ድረስ የሚደርስ ችግርን እንደሚያስከትልበትም ማወቅ ያስፈልጋል።

እንደ ዶክተር ሰላም ገለጻ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ሊያውቀው የሚገባው ነገር ቀኑን ሙሉ ስልክ ላይ አቀርቅሮ መዋል ገዳይ መሆኑን ነው። ይህንን በምሳሌ ባስረዳ “ አንድ ሰው ቀጥ ብሎ በቆመ ወይም በተቀመጠ ሰዓት ጭንቅላቱ ብቻ 6 ኪሎ ግራም አካባቢ ይመዝናል፤ አንገቱን 45 ዲግሪ ባጠፈ መጠን ደግሞ የጭንቅላቱ ክብደት አምስት እጥፍ ይሆናል፤ ይህ ክብደት ደግሞ በአንገቱ እንዲሁም በህብለ ሰረሰሩ ላይ በማረፍ ጫና ይፈጥራል፤ “ በመሆኑም ይህንን ተረድቶ ገዳይ የሆነውን መቀመጥን አለማብዛት መቀመጥ ካስፈለገም ቀጥ ብሎ በመቀመጥ ጤናን መጠበቅና ሞትን መቀነስ እንደሚገባም ያስረዳሉ።

በሌለ በኩልም ችግሩ የተከሰተባቸው አብዛኞቹ ሰዎች ከህመማቸው ጋር ነው የሚቀመጡት የሚሉት ዶክተር ሰላም ምናልባት ከተማ አካባቢ ያሉ ሰዎች ለዚያው ጥቂቱ ግንዛቤው ኖሯቸው ወደ ህክምና ተቋም ሊሄዱ ይችላሉ፤ ነገር ግን ከፍ ያለ የስራ ጫና የሚበዛባቸውና ስለ አከርካሪ አጥንት ጤንነት ግንዛቤ የሌላቸው የገጠር ሰዎች፣ በአነስተኛ መጠን የኮንስትራክሽን ስራ የሚሰሩ ሁሉ ከህመሙ ጋር ሊቀመጥ ይገደዳሉ፤ በመሆኑም የግንዛቤውን ደረጃ ማስፋት የባለሙያዎች እንዲሁም የመገናኛ ብዙሀን ስራ ሊሆን ይገባል ይላሉ።

በጤና ጣቢያዎቻችንና ትልልቅ የህክምና ተቋማት በጣም ብዙ ሰዎችን መርዳት የሚችሉበት ሁኔታ መፈጠር አለበት የሚሉት ዶክተር ሰላም ለዚህ ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የጤና ባለሙያዎችን ማብቃት ያስፈልጋል፤ በተጨማሪም ልጆቻችንን የሚያስተምሩ የስፖርት መምህራን ትልቅ ግብዓት ናቸው፤ በመሆኑም ልጆችን ሲያስተምሩ የአካላቸውን አቀማመጥ፣ የትከሻቸውን፣ የጀርባቸውን መዛነፍ አለው ወይ የለውም የሚለውን ቢያዩልን በቶሎ መፍትሔ ይገኛል ችግሩንም በዛም ልክ መቀነስ ይቻላል ባይ ናቸው።

“የአከርካሪ አጥንት የጤንነታችን መሰረት መሆኑን እንገንዘብ፤ እቃ ስናነሳ፣ ተሸክመን ስንሄድ፣ መምህራን ልጆች በትምህርት ቤት አቀማመጣቸው ምን መምሰል አለበት? የሚሸከሙት ቦርሳ መጠኑ ምን ያህል ሊሆን ይገባል? የሚለውን እባካችሁ ተከታተሉልን፣ መገናኛ ብዙሃን የተጠናከረ ስራን ስሩልን “ በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ 1 ቢሊየን ሰዎች በአከርካሪ አጥንት ችግር ይሰቃያል። ከሌላው ዓለም በይበልጥ አፍሪካ ዝቅ ሲል ደግሞ እንደ እኛ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች አራት እጥፍ ነው ችግሩ የሚታይባቸው።

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

# ኢትዮጵያን የተሸከሙ ወርቃማ ትከሻዎች

በዚህ ጋዜጣ የጥቅምት 5 ቀን 2015 ዓ.ም እትም “የኢትዮጵያን ስም የተሸከሙ የሙያ ማኅበራት” በሚል ርዕስ በተግባራቸው ግዝፈት ሳይሆን በስማቸው ብቻ “የኢትዮጵያ...” የሚል ቅጽል እያከሉ ያለ ፍሬ ኮስምነው የሚገኙ በርካታ “ብሔራዊ ማኅበራት” ከሚያንኅላጅጁበት እንቅልፍ እንዲባንኑ መቀስቀሳችን ይታወሳል። ለምን ከገባንበት ጥልቅ ድባቴ “አወካችሁን” እንደማይሉ ተስፋ በማድረግ ጭምር።

ሃሳባችንን ዘለግ በማድረግም አላግባብ የተሸከሙትን ግዙፍ የኢትዮጵን ስም አንድም በአግባቡ ተጠቅመውበት ለሀገር የሚበጅ ፍሬ እንዲያፈሩ፤ አለበለዚያም አላቅማቸው “እንኮኮ” ብለው ፊጥ ካሉበት “የኢትዮጵያ ስም” ጫንቃ ላይ እንዲወርዱ ጠንከር ያለ የወዳጅነት ሃሳብ ለመሰንዘርም ተዳፍረናል።

ለማዋዣነት እንዲረዳም የፈረንሳዩ ገናና መሪ ናፖሊዮን ቦናፓርቴ በጦር ሜዳ ዐውደ ውጊያ ላይ በነበረበት አንድ ወቅት ፈሪ ወታደሩ ሲሸሽ አስተውሎት ካስጠራው በኋላ፤ “ስምህ ማነው?” ብሎ እንደጠየቀው፤ ወታደሩም “ናፖሊዮን” እባላለሁ ብሎ ሲመልስለት “ወይ እንደ እኔ እንደ ናፖሊዮን ጀግና ሁን፤ አለበለዚያ ስሜን መልስልኝ” አለ መባሉን ጭምር ጠቅሰናል።

ናፖሊዮንን በምሳሌነት የጠቀስነው ኢትዮጵያም ጨከን ብላ ስሟን አላግባብ የተሸከሙትን የሙያ ማኅበራት “ወይ ስሜን መልሱ፤ አለበለዚያም የስሜን ክብር ያህል አገልግሉኝ!” ብላ “በብሔራዊ ማኅበርነት” መንበሩን የያዙትን ቡድኖች እንድትገስጻቸው ጭምር ምክር ሃሳብ አቅርበንላታል። የዛሬው ርዕስ ጉዳያችን ከላይኛው የመንደርደሪያ ሃሳብ ጋር ተቀራራቢ ቢመስልም በይዘቱ ጠነን እና ጠጠር የሚል የመሚገቻ ፍሬ ነገሮች የተንዠረገጉበት መሆኑን አስረግጠን ማስታወስ እንደወዳለን።

**ዝክረ አትላስ፤**

ከሀገራችን ተጠቃሽ ገጣሚያን መካከል አንዱ የሆነው ብዕረኛ የቀመራቸውን ጥቂት ስንኞች በመዋስና በግጥሙ ውስጥ ስለተጠቀሰው አንድ “ገጸ ባሕርይ” ጥቂት መዘከሪያ ሃሳብ ፈነጣጥቀን ወደ ሞጋቹ ርዕሰ ጉዳያችን እናቀናለን።

**“አትላስ የግሪኩ፣ አትላስ ‘የተረቱ’ ምድርን ስላዘለ፣**
**ሲዘከር ጉብዝናው፣ ሲወደስ መጠሪያው ጽኑ እየተባለ።**
**“የእኔ ስስ ትከሻ ምን ተብሎ ይጠራ፣**
**ተሸክሞ የሚኖር ምድርን ከአትላስ ጋራ።”**

በእነዚህ ስንኞች ውስጥ የተጠቀሰው “አትላስ” ጥንታዊ ግሪኮች የፈጠሩት የአፈ ታሪክ ውላጅ ነው። ከአማልክቱ መካከል አንዱ እንደነበርና በሰራው ስህተት ምክንያት ከፍ ባሉት አለቆቹ አማልክት ውሳኔ ፍጻሜ በሌለው ዘለዓለም፤ ዓለምን ከነግሳንግሷ ተሸክሞ እንዲኖር ፍርድ እንደተላለፈበት አሳዛኙ ተረክ ዝርዝሩን ይነግረናል።

ዛሬም ድረስ “አትላስ” በፍርደኛነቱ እንደቀጠለና “ዓለም” በጫንቃው ላይ ተቀምጣ እንደምትንፈላስ የሚያሳዩ በርካታ ሐውልቶች በአቴንስ አደባባዮችና በበርካታ ሀገራት ተገሽረው ማስተዋል እንግዳ አይደለም። በጂኦግራፊ ትምህርት ደጋግመን ስሙን የምንጠራው የዓለም ካርታ “አትላስ” ተብሎ የተሰየመውም የዚህ ምስኪን ተሸናፊ የግሪክ “አምላክ” ፍርደኛ ታሪክ መነሻ ሆኖ መሆኑን ልብ ይሏል። ለማንኛውም ወደ ዋናው ርእሰ ጉዳያችን እንዝለቅ።

**ባለወርቃማ ትከሻዎች፤**

ኢትዮጵያ በሉዓላዊ ክብሯ፣ በሞገስና በነፃነቷ “እመቤት ሆይ!” እየተባለች ተከብራና ተወዳ እንድትኖር ምክንያት የሆኑት ያለፉትና ዛሬም በሕይወት ያሉት ብሩካን ልጆቿ ናቸው። “ልጆቿ” ስንል ሁሉንም ማለታችን አይደለም። አንዳንዶች ልጅ ሳይሆኑ ግብርም ስምም የሌላቸው “የእንግዴ ልጅ” የሚባሉ ዓይነቶች ናቸው።

> **አ**በሳላቸው አንድም የጅብ፣ አንድም የቅልጥም ሰባሪ ጆፌ አሞራ ዓይነት ነበር። የላይ ላዩን ሥጋ ብቻ ሳይሆን የአጥንቷ ውስጥ መቅኒም አልቀራቸውም። ይህ ማለት የዘረፋ መረባቸው የተዘረጋው ከተራ ኪዮስክ እስከ የከርሰ ምድር ሀብት ድረስ መዝለቁን ለማሳየት ነው

የእናት ሆድ ዝንጉርጉር እንዲሉ ከዜጎች መካከል አንዳንዶች ለመጻፍ (ለታሪክ ክብር የበቁ ማለት ነው)፣ አንዳንዶችም ለወናፍ (ለአልባሌ) ተግባር የተፈጠሩ መሆናቸውን ልብ ይሏል። ይህንን አገላለጽ የተዋስነው፡- “‹የዋህ በግ› ሁለት ወልዳ አንዱን ለመጻፍ አንዱን ለወናፍ” የሚለው ሀገራዊ ብሂል ትዝ ቢለን ነው።

ኢትዮጵያን አስከብረውና እያስከበሩልን ያሉት ተወዳሽ ልጆቿ ዋነኛው መለያቸው ሀገራቸውን በትከሻቸው ላይ ተሸክመው ለመኖር ራሳቸውን ሙሉ ለሙሉ አሳልፍ መስጠታቸው ነው። እንደነዚህ ዓይነት ልጆቿ እምነታቸው ከራስ ያለፈ፣ በወገን ፍቅር ልባቸው የነደደ፣ የዜግነት ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ሹመትም ሆነ ሽልማት የማይጠብቁ፣ ጎሽታም ሆነ እሶሶ የማይጠይቁ የተግባር ሰዎች ናቸው። የክፉ ቀን አለኝታ የሆኑት እነዚህ የሀገር ጌጦች፤ ቀዳሚው ህልማቸውና ርዕያቸው የሀገራቸው ከፍታና የሕዝባቸው እፎይታ ነው።

የሚነጉደው እድሜያቸውና የምድር ጉዟቸውን ሲያጠናቅቁ የሚያሸልበው ሥጋቸውና ትዳራቸው እያጓጓቸውና እያሳሳቸው “ከራስ በላይ ነፋስ” በማለት አያላዝኑም። ልባቸውን አሳብጠውና ስሜታቸውን አስብተውም “ከእኔ ወዲያ ላሳር” እያሉ አይፏልሉም። ሀገራቸውን በወርቃማ ትከሻቸው ላይ ተሸክመው የሚያከብሯት አማላይ ጉርስም ሆነ ውርስ ስለሚፈልጉ አይደለም። ተግባራቸው እንጂ ስማቸው እንዲጮኽና አዋጅ እንዲለፍፍም አይፈልጉም። ሃሳቡን በተጨባጭ ማሳያ እናኅላምሰው።

ሀገርን ለመታደግ ከግፈኛው ወራሪ ኃይል ከአሸባሪ ሕወሓት ጋር እየተፋለሙ ያሉትን አናብስት የጥምር ጦሩን ጀግኖቻችንንና በተለየ “ንስር ዐይኑ” ለሉዓላዊነታችን ክብር በተጠንቀቅ ዘብ የቆመልንን የመከላከያ ሠራዊታችንን ለአንድ አፍታ በዐይነ ህሊናችን አቅርበን እናስተውላቸው። ደምና ላባቸውን፣ ዕድሜያቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ለመስዋዕትነት አቅርበው ጠላትን እየጣሉ የሚወድቁት ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ሳይሆን ኢትዮጵያን ላለማስደፈር የገቡትን የቃል ኪዳን መሃላ የሙጥኝ ብለው ስለሚጠብቁ ነው። ኪዳናቸውን በዝማሬ የሚገልጹትም፡-

**“አጥንቴም ይከስከስ፤ ደሜም ይፍሰስሳት፣**
**ይህቺን ሀገሬን ፍጹም አይደፍራትም ጠላት።”**

እያሉ ነው።

አንዱ በመስዋዕትነት ሲወድቅ ሌላው እየተቀባበለ ኢትዮጵያ አብራቸው እንዳትወድቅ ቀን ከሌት የሚፋለሙትም ከራሳቸው በላይ የሀገራቸው ክብር ነፍሳቸውንና ማንነታቸውን ጢም አድርጎ ስለሞላው ነው። እንዲያማ ባይሆን ኖሮ ሕወሓት የሰሜን ዕዝ ጀግኖችን በከዳበትና ሀገር መከራ ላይ በወደቀችበት ጊዜ “ኢትዮጵያን በጫንቃቸው ላይ ተሸክመው” ነፍሳቸውን ለውርርድ በማቅረብ መራር ዋጋ ባይከፍሉ ኖሮ ዛሬ “እምዬ” ምን ልትመስል እንደምትችል መገመቱ አይከብደም። ክብርና ሞገስ ለጀግናው መከላከያችን፣ ለፀጥታ ክፍሎችና ለሕዝባዊ ሠራዊቶቻችን ይድረስልን።

በወታደራዊ መስክ ብቻ ሳይሆን በሕዝብ አስተዳደር፣ በፖለቲካ አመራር፣ በግብርና፣ በትምህርት፣ በንግድና በኢንቨስትመንት፣ በሕግና በሰላም ማስከበር፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ በሚዲያውና በኪነ ጥበቡ መስክ ወዘተ. ወርቃማውን ጫንቃቸውን ዝቅ አድርገው ኢትዮጵያን በመሸከም ከፍ ላደረጓት ልጆቿ በሙሉ ክብርና ሞገስ ይሁንላቸው።

በሥርክ ጸሎታቸው/ዱአቸው እና በጾማቸው ሥጋቸውን እያረቁ በመቃተት ተንበርክከውና ዝቅ ብለው ኢትዮጵያን ወደ ፈጣሪ ዙፋን ለማቅረብ ሌት ተቀን ለሚቃትቱ የሃይማኖት አባቶች፣ መምህራንና ርህሩህ እናቶችና ዜጎች የኢትዮጵያ አምላክ ዘላለማዊ ክብር ያዋርሳቸው። ሀገራቸው በክብር ጸንታ የኖረችውና ዛሬም ተከብራ ያለቸው የእነርሱን ወርቃማ ጫንቃ መንበር አድርጋ ስለሆነ ኩራትም ክብርም ሊሰማቸው ይገባል።

**ኢትዮጵያ የተሸከመቻቸው ወበከንቱዎች፤**

“ጽድቁ ቀርቶ...” እንዲሉ ኢትዮጵያን መሸከሙ ቢቀር እንኳን በእርሷ ላይ ተንጠልጥለው የተጣቧት በመዥገር የሚመሰሉ የልጅ ጠላቶቿ አደብ ቢገዙ ባልከፋ ነበር። ቀደም ሲል ስንኞቹን የተዋስነው ገጣሚ ካሳተመው የመጽሐፉ ገጾች ውስጥ “የመጻተኛ ሀገር” በሚል ርዕስ በአራት ሀረጋት ቀምሮ ያቀረበልን አንድ ግጥም ከዚህ ንዑስ ርዕስ ጋር የሚኅዳኝ ስለመሰለን ደራሲው ባየበት ዕይታ ሳይሆን ይህ ጸሐፊ በገባው መልኩ እንደሚከተለው ለሃሳባችን ማኅልበቻነት ተጠቅመንበታል።

**“ሀገር ድንኳን ትሁን፤ ጠቅልዬ የማዝላት፣**
**ስገፋ እንድነቅላት፤ ስረጋ እንድተክላት።”**

ኢትዮጵያን ለማስከበር ሳይታክቱ ዋጋ እየከፈሉ ያሉ ልጆቿ የመኖራቸውን ያህል በአንጻሩም “ሆድ አደርነትን” መለያ በማድረግ ኅሊናቸውን ለክፋትና ለጥፋት እየቸረቸሩ ያሉ “የሀገር ጉዶች” መኖራቸውንም በብዙ መልኩ እያየንና እየታዘብን ነው። እንደነዚህ ዓይነት የቁም ሙቶች የሚኖሩት ለዜግነታቸው ክብር “ዘብ በመቆም” ሳይሆን በእኔነታቸው ታዛ ሥር ተጠልለውና አድበተው በሙት ኅሊናቸው እየተነፈሱ፣ በበድን ማንነታቸው እየተኩራሩና “እኔ ከሞትኩ...” አለች ከምትባለው እንስሳ ጋር አብረው እያፋሸኩ ነው።

ለእነርሱ የሚታያቸው ኢትዮጵያ የጀግኖች ልጆቿን ጫንቃ እንደ አእማድ አጽንታ በክብር መቆሟ ሳይሆን ሲቃዡ የሚያድሩት “የሰሜን ነፋስ” ካስማውን በቀላሉ ነቃቅሎ እንደሚያፈራርሰው ተራ ድንኳን ነው። ድንኳኑን የተሸከመው ደግሞ የእነርሱ ኅባጣ ወገብ እንደሆነ ሲፎክሩ መታየታቸው ሌላው መገለጫቸው ነው።

“ሲፋጅ በማንኪያ፤ ሲቀዘቅዝ በእጅ” እንዲሉ በውስጣቸው የሰረጸው ፍልስፍና ከላይ በሁለት ስንኝ ውስጥ የተጠቀሰው መልእክት ነው። ሀገር ስትረጋጋ ሊኖሩባት፤ “መከራ ሲገጥማት” ጥለው እብስ ሊሉ በቋፍ ላይ መሆናቸው የኅሊና ቢስነታቸው አድማስ ጥግ ነው።

የሀገርን መከራ ለጥቅማቸው፣ ክፉ ወቅትን ለመክበሪያቸው ለመጠቀም ሌት ሲቃዡ፣ ቀን ሲባትቱና ሲወራጩ የሚሉ ዜጎች ቁጥር በስታትስቲክ ቀመር ቢገለጽ መልካም በሆነ ነበር። እንደነዚህ ዓይነት ዜጎች ባህርያቸውም ሆነ ስልታቸው የረቀቀ ነው። ሀገር ለእነርሱ “የነፍስና የሥጋቸው መጦሪያ” እንጂ የክብር ጌጥና ውበት አይደለችም። በንሰሃ ለመመለስም ድፍን አእምሯቸው፣ የደነደነው ልባቸውና የማይረካው ፍላጎታቸው ልቅ ሆነው እንዲጋልቡ ብርታት ሆኗቸዋል።

ለዚህ እውነታ በጥሩ ማሳያነት የሚጠቀሱት ደግመን ደጋግመን እንደገለጽነው የሕወሓት መሪ ተብዬ “የቁም ሙቶች” ናቸው። እነዚህ ጥቂትና በጣት የሚቆጠሩት ግለሰቦች እንኳን ኢትዮጵያን በትከሻቸው ላይ ሊሸከሙ ቀርቶ “ጠረኗን” ሳይቀር ተጠይፈው የኖሩ ጉዶች ናቸው። በሥልጣን ላይ ተፈናጠው የኖሩበትን ዘመን ያገባደዱት እንደ መዥገር ኢትዮጵያ ላይ ተጣብቀው ግቷንና ደሟን እየመጠጡ ነበር። የሃያ ሰባቱ ዓመታት መከራ የሚገለጸው “ዘረፋ” በሚለው ቃል ሳይሆን የሀገሪቱን ሥጋና አጥንት እየጋጡ ነበር ማለቱ ይቀላል።

አበላላቸው አንድም የጅብ፣ አንድም የቅልጥም ሰባሪ ጆፌ አሞራ ዓይነት ነበር። የላይ ላዩን ሥጋ ብቻ ሳይሆን የአጥንቷ ውስጥ መቅኒም አልቀራቸውም። ይህ ማለት የዘረፋ መረባቸው የተዘረጋው ከተራ ኪዮስክ እስከ የከርሰ ምድር ሀብት ድረስ መዝለቁን ለማሳየት ነው። የዱር አውሬዎች እንኳን ያደኑትን የሚመገቡት ከራሳቸው የቡድን ሠራዊት ጋር በመጋራት ነው። ሕወሓት ይሉት የዘመናችን ሰብዓዊ ደም መጣጭ ቢያንስ ስሙን ተሸክሞ “የእኔ ብቻ” እያለ ለሚሸነግለው የተከበረው የትግራይ ሕዝብ አንዳች የበጎነት ተግባር ቢፈጽም ባልከፋ ነበር። የመሪዎቹ ዋና ግብ ሥጋቸውና ቤተሰባቸው ብቻ ስለሆነ ዘረፋው ለራስ ጓዳና ለራስ ወገን ብቻ ነበር።

ኢትዮጵያ አልተፈተነችም ማለት አይደለም። በውስጥ በእንግዴ ልጆቿ፣ በውጭ በታሪካዊ ጠላቶቿ ተጠቅታለች፣ ተጎድታለች ታማለች። ቢሆንም ግን የተሸከሟት ባለወርቃማ ትከሻ ልጆቿ ለጠላቶቿ መቅሰፍት፣ ለጥቃቷ አለኝታ፣ ለህመሟ ፈውስ ሆነው ስለተሸከሟት የተንገዳገደች ትምሰል እንጂ አትወድቅም፤ የዛለች ትምሰል እንጂ አትሰነካከልም። እናት ዓለም በተሸከሙት ልጆችሽ ጫንቃ ላይ ከፍ ብለሽ ግነኚ፣ ደምቀሽ አብሪ፣ በጠላቶች ፊት ድልን፣ በወደረኞች ፊት ሞገስን ይስጥሽ። ሰላም ይሁን!

ፖለቲካና ወቅታዊ

## ተናጋሪው ዶሴ

# የክፋትና ምቀኝነት ቅንብር- የህጻናትን ሕይወት እስከማጥፋት

አስመረት ብስራት



በገጠር አካባቢ የተወለዱት ህፃናት እያዩ የሚያድጉትና ከፍ ሲሉም የሚሰሩት ስራ ነው እረኝነት። በገጠር ሴትም ሆነ ወንድ እረኝነትን ሳይሞክር እና ቤተሰቡን ከብቶች በመጠበቅ ሳያገለግል የሚያድግ ልጅ አይኖርም። የእረኝነት ስራው የሚሰራው ደግሞ ከአካባቢያቸው ራቅ ባለ የሚጋጥ ሳርና ውሃ ባለበት ቦታ ነውና ከብቶቹን የሚጠብቁት እረኞች ስንቃቸውን ይዘው ከቤታቸው ራቅ ብለው ይሄዳሉ። በዚህ ወቅት ታዲያ የተለያዩ አደጋዎችም ሊያጋጥማቸው ይችላል። ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ። በጎርፍ መወሰድ በዱር እንስሳ መነከስና መበላት እንዲሁም በሰዎች መደባደብ አልፎ ተርፎም አድብቶ ለማጥቃት በመጣ ጠላት የመሞት አደጋዎችን ያስተናግዳሉ።

በዛሬው የ‹‹ዶሴ›› አምዳችን ላስነብብ የፈለኩት ስለ እረኝነት ሳይሆን በእረኝነት ላይ ሆነው በአሰቃቂ ሁኔታ ስለተገደሉ ህጻናትና የፍትህ ውሳኔ ይሆናል።

### ጎደኛሞች እረኞች

በጌዴኦ ዞን ኮቾሬ ወረዳ ደቦ ቀበሌ ነው የተወለዱት። ሕፃን ዘላለም ጀቦና ነፃነት ገብሬ ይባላሉ። ቤታቸው ጎን ለጎን በመሆኑ የጠበቀ ጉርብትና ካላቸው ቤተሰቦች ነው የተገኙት። ሕፃን ዘላለም ጀቦ ስድስት ዓመቷ ሲሆን ህፃን ነፃነት ገብሬ የሰባት ዓመት ልጅ ነበረች። እድሜያቸው አቻ በመሆኑ እና የቤተሰቦቻቸው የጠበቀ ጉርብትና ልጆቹ ተዋደው እና ተግባብተው የእህትማማች ያህል አብረው እንዲያደጉ አድርጓቸዋል።

ዘላለም የተወለደች ጊዜ የነፃነት እናት እንደ እናትም እንደ እህትም ሆና ነበር የዘላለምን እናት ያረሰቻት። እርስ በእርስ የሚደጋገፉት ጎረቤታሞች ፍቅር ልጆቹ ላይም ተጋብቶ ሲወጡም ሲገቡም አይለያዩም ነበር። ነፃነት በእድሜ ከፍ ብትልም እረኝነትን የጀመሩት ግን አብረው ነበር። ለእረኝነት ሲወጡ እናቶቻቸው የቋጠሩላቸውን ምግብ ይዘው ከትናንሽ አለንጋቸው ጋር በጎቻቸውን እየነዱ ይውላሉ። ሜዳው ላይ ጨዋታው ቡረቃውን ደስታቸው ወደር የለውም ነበር። በፍቅር የሚጨዋወቱ ህፃናት ከሚኖሩበት አካባቢ ብዙም ርቀው ስለማይሄዱ አደጋ ይደርስብናል ብለው አስበው አያውቁም ነበር። ሁልጊዜ ደስታና ጨዋታ የማይለያቸው እነዚህ ንፁህ ፍጡራን ላይስ ማን ክፉ ይደርስ ይሆናል ብሎ ያስባል? አያድርስ ነው እንጂ!

### ጎደኛሞቹ ገበሬዎች

አቶ ጀቦና ጎቼና አቶ ገበሬ ጎየቶ በጌዴኦ ዞን ኮቾሬ ወረዳ ደቦ ቀበሌ ነዋሪ ናቸው። የእነዚህ ጓደኛሞች ቤት አጠገብ ለአጠገብ ከመሆኑም ባሻገር ማሳቸውም ኩታ ገጠም በመሆኑ አብረው አርሰው ምርታቸውን አንድ ላይ ነበር የሚያስገቡት። ለገበያ እንኳን ሲወጡ የማይለያዩት ጓደኛሞች አንዱን ያለ አንዱ ማየት ይከብድ ነበር። የጎረቤታሞቹ ጥብቅ ቁርኝት ቤተሰቦቻቸውም አንድ ላይ የሚኖሩ ስለነበሩ አንድን ቤተሰብ ከአንዱ መለየት እጅግ ከባድ ነበር።

እነዚህን ጓደኛሞች አንድ ላይ ሰርተው የተሻለ ምርት በማግኘታቸው የሚቀኑባቸው ብዙዎች ነበሩ። በተለይም የእርሻ መሬታቸው በኩታ ገጠም የተሻለ የምርት ሂደትን በመከተላቸው ከመማር ይልቅ በቅናት መመልከትን ጀመሩ። ይባስ ብለው ዙሪያው ካለው መሬት የተሻለ ሆኖ የታያቸውን የእነዚህን ጠንካራ ገበሬዎች እርሻ ለመቀማት ዳር ዳር ይሉ ገቡ።

የእነሱን የቅናት ሀሳብም ሌሎች ላይ በማጋባት ስምንት የሚሆኑ ግብረ-አበሮችን አደራጁ። የሀሰት መስካሪዎችን አዘጋጁ። ቀጥለውም እናንተ የምታርሱት መሬት የእኛ እርስት ነው በማለት በአካባቢያቸው ባለ ፍርድ ቤት ከሰሷቸው። በህግና በስርዓት የሚመሩት ጓደኛሞቹ ገበሬዎች የይዞታ ማረጋገጫቸውን በማቅረብ መሬቱ የራሳቸው መሆኑን በማረጋገጥ ክርክሩን ረተው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ።

በዚህ እጅግ የተናደዱት መለሰ ሚጁ፣ ማቲዎስ አየለ፣ ገብረመድህን ሚጁ፣ ታምራት (ሽቶ) አሸናፊ፣ ታምራት ተስፋዬ፣ ባህሉ አየለ፣ ኢሳያስ ወርቁና ፍሬአየሁ አየለ በተባሉት ስምንት ሰዎች እነዚህን የሚዋደዱ ጎረቤታሞች የሚተነኩሱበት ነገር በየፊናቸው ማሰላሰል ጀመሩ።

### የጥፋት ምክክር

ስምንቱ ለጥፋት የተሰባሰቡት ጓደኛሞች ከእለታት አንድ ቀን ከገበያ ሲመለሱ ክፋትንና ምቀኝነትን በልባቸው እንዳረገዙ አንድ መጠጥ ቤት ተቀመጡ። አንዱ “ቤታቸውን በላያቸው ላይ እናንድደው....” ሲል ሀሳቡን ያቀርባል። ሌላው “እነሱ ጠንካሮች ስለሆኑ መልሰው ይተኩታል ሌላ ሀሳብ ....” በማለት ጓደኞቹን በጥያቄ አይን ይመለከታል። ሌለኛው “ለምን ማሳቸው ውስጥ ከብት አንነዳበትም.....?” ሲል ይጠይቃል። “ይህም አይሆንም ጎተራቸውን የሞላውን እህል እየበሉ ሊቆዩ ይችላሉ። ይልቅ ሌላ አንጀታቸውን ድብን የሚያደርግ ሀሳብ አለኝ” በማለት ሌላ ያለውን ሀሳቡን ለጓደኞቹ ያቀርባል።

ይህ ሀሳብ በስምንቱም የጥፋት ልኡካን ተቀባይነት ያገኘና እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው ለመመካከር ለሳምንት ቀጠሮ ይዘው ይለያያሉ። ሁሉም ላሰቡት እኩይ ተግባር ይጠቅመናል ያሉትን መሳሪያ በድብቅ ማሰናዳት ይቀጥላሉ።

### ቀን አያውቁ ህጻናት

ሁለቱ ጓደኛማቾች ህጻናት ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ በጎች በመጠበቅ ላይ ነበሩ። ጓደኞቻቸው ምሳቸውን ለመብላት ወደ ቤታቸው በመመለሳቸው የተነሳ ብቻቸውን ጥላ ስር ቁጭ ብለው ቅልልቦሽ እየተጫወቱ ነበር። ሲሸናነፉ በመንጫጫትና በመሯሯጥ ትንሽ ሲስቁ ይቆዩና ወደ ዛፍ ጥላ ስር ከለል ብለው ጨዋታቸውን ይቀጥላሉ። በስድስት ዓመቷ ሕፃን ዘላለም ጀቦና የሰባት ዓመቷን ነፃነት ገብሬ የተባሉ ሴት ሕፃናት ባላሰቡት ጊዜ ነበር ድንገት ስምንት ጎረቤቶቻቸው ወደእነሱ አቅጣጫ ሲመጡ የተመለከቱት።

ልጆቹ ቀና ብለው አየተው የሚያውቋቸው ሰዎች መሆናቸውን ሲያረጋግጡ ያለምንም ስጋት ወደ ጨዋታቸው ተመለሱ። አሁንም ሰዎቹ ወደእነሱ እየቀረቡ ነው። እነሱ ጋር ለመድረስ ትንሽ ርቀት ሲቀራቸው አራቱ በተለያየ አቅጣጫ ተበታትነው አራቱ ደግሞ ወደእነሱ እየቀረቡ ነበር። ልጆቹ በጨዋታ ልባቸው ጠፍቶ ስለነበር ምንም ተኩረት አልሰጧቸውም። እነዚያ የጥፋት መልዕክተኞች ግን አጠገባቸው እንደደረሱ ልጆቹ ድምፅ ሲያሰሙ ሊያጥፉቸው ይችላሉ ብለው ባዘጋጁት ቁሳቁስ በማፈንና ትንፋሽ በመሳጣት፤ በመቀጠልም በገመድ በማነቅ የህፃናቱን ሕይወት አጠፉ።

ልጆቹን ከገደሉ በኋላም እንደ በግ በየሜዳው ላይ ዘርርው ጥለዋቸው በመሄድ የክፋት ሀሳባቸውን ያጠናቅቃሉ። ያን ጊዜ ምሳቸውን በልተው የሚመለሱት የህፃናቱ ጓደኞች የሆነውን በሙሉ ተመልክተው ኖሮ ልክ ሰዎቹ ከአካባቢው ዞር ሲሉ ጠብቀው እርዳታ ፍለጋ መንደሩን በጩኸት አቀለጡት። ጩኸቱን የሰሙት የአካባቢው ነዋሪዎች በቦታው ሲደርሱ የተመለከቱትን ማመን አቃታቸው። ዳሩ ነፍስ የማያቁ ህፃናት ሕይወት እንዲህ ባለ ሰቅጣጭ ሁኔታ ጠፍቶ መመልከትን ያህል ልብ ሰባሪ ነገር ከወዴት ሊገኝ?።

የህፃናቱ ወላጆች በቦታው ሲደርሱ የተመለከቱትን ማመን አቃቷቸው፤ ሁኔታው ኩፉኛ አስደንጋጭና ፈፅሞ ያልጠረጠሩት ስለነበርም ስሜታቸውን መቆጣጠር ተስኗቸው ራሳቸውን ሳቱ። የሆነው ሁሉ ሆኖ ሰው ሲረጋጋ እርዳታ የጠየቁትን ህፃናት ስለጉዳዩ በመጠየቅ ጉዳዩን ይዘው ለህግ አካል አቀረቡ።

### የፖሊስ ምርመራ

ፖሊስ ጉዳዩን እንደሰማ ልጆቹ የተመለከቷቸውን አራት ገዳዮች ለመያዝ ይሰማራል። የልባቸውን ሰረተው ቤታቸው የተከተቱት ጓደኛሞች ከየቤታቸው ተለቅመው ይወጣሉ። ፖሊሶች ባደረጉት ምርመራ አራቱ ሰዎች ብቻ ገዳይ አለመሆናቸውንና ሌሎች ግብረ-አበሮች አብረዋቸው እንደነበሩ ይደርስበታል። እነዚህን ተባባሪ ወንጀለኞች ለመያዝ ባደርገው ጥረት የማህበረሰቡም ርብርብ ተጨምሮበት በቁጥጥር ስር ዋሉ።

ለህፃናቱ ሞት ምክንያት የሆነው ቅናት መሆኑን፤ በማይረባ በመሬት ግጭት የተነሳ የህፃናቱ ሕይወት መጥፋቱን ፖሊስ ይናገራል። የአይን ምስክሮችን፤ የህክምና ማስረጃን በመጠቀም የቴክኒክና የታክቲክ ምርመራ ሲያደረጉ ከቆዩ በኋላ ፖሊስ ምርመራውን ጨርሶ ወደ ዓቃቤ ህግ በመላክ ውሳኔውን እየተጠባበቀ ይገኛል።

### ውሳኔ

ዓቃቤ-ህግም ፖሊስ አጠናክሮ የላከለትን መረጃና ማስረጃ ተመልክቶ ተጠርጣሪዎቹን በከባድ የግድያ ወንጀል ክስ መሰረተባቸው።

ዓቃቤ ህግ ሐምሌ 6 ቀን 2013 ዓ.ም በጌዴኦ ዞን ኮቾሬ ወረዳ ደቦ ቀበሌ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ በጎች በመጠበቅ ላይ በነበሩት በስድስት ዓመቷ ሕፃን ዘላለም ጀቦና የሰባት ዓመቷን ነፃነት ገብሬ የተባሉ ሴት ሕፃናትን በአሰቃቂ ሁኔታ ግድያ በፈጸሙት ግለሰቦች ላይ ከባድ ቅጣት እንዲጣልባቸው ክሱን አቅርቧል።

የጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰው መግደል ወንጀል የተከሰሱት ስምንት ግለሰቦች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ቀን ቀጥሯል።

ሰው በመግደል ወንጀል ችሎት የቀረቡት ተከሳሾች ‹‹ድርጊቱን አልፈፀምንም›› በሚል የእምነት ክህደት ቃላቸውን የሰጡ በመሆኑ፤ ዓቃቤ ህግ ያሰባሰባቸውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች በማቅረብ ተከራክሯል። ተከሳሾችም መከላከያ ማስረጃ በማቅረብ ያሰሙ ቢሆንም፤ በዓቃቤ ህግ የቀረበውን የሰውና የሰነድ ማስረጃ ማስተባበል ባለመቻላቸው ፍርድ ቤቱ ተከሳሾቹን በተከሰሱበት አንቀፅ ሥር ‹‹ጥፋተኛ ናቸው›› በማለት ብይን ሰጠ።

ግራ ቀኙን ሲያከራክር የቆየው የጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀደም ሲል በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ቁ539/1/ሀ/ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ያሉ ተከሳሾችን በሞት እንዲቀጡ ወሰነ፤ ከ4ኛ እስከ 8ኛ ያሉ ተከሳሾችን ደግሞ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ቁ671/1/ሀ/ እያንዳንዳቸውን የስድስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ቢወስንም በቅጣቱ ላይ የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት አቅርበዋል።

የጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ የጣለባቸው መለሰ ሚጁ ፣ማቲዎስ አየለ፣ ገብረመድህን ሚጁ፣ ታምራት (ሽቶ) አሸናፊ፣ ታምራት ተስፋዬ፣ ባህሉ አየለ፣ ኢሳያስ ወርቁና ፍሬአየሁ አየለ በተባሉት ስምንት ተከሳሾች ላይ ነው። ተከሳሾቹ ሐምሌ 6 ቀን 2013 ዓ.ም በጌዴኦ ዞን ኮቾሬ ወረዳ ደቦ ቀበሌ ከቀኑ ስድስት ሰዓት ላይ በጎች በመጠበቅ ላይ በነበሩት በስድስት ዓመቷ ሕፃን ዘላለም ጀቦና የሰባት ዓመቷን ነፃነት ገብሬ የተባሉ ሴት ሕፃናትን በአሰቃቂ ሁኔታ ግድያ በፈጸሙት ግለሰቦች ላይ ነው።

የጌዴኦ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጥቅምት 4/2015 በዋለው ችሎት በመሰለ ሚጁና በገብረመድህን ሚጁ ላይ እያንዳንዳቸው በ25 ዓመት ማቲዎስ አየለ በ21 ዓመት ከ5ኛ እስከ ስምንተኛ ያሉ ተከሳሾችን ደግሞ በአምስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ አስተላልፏል። መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መዝገብ ቤት ተመልሷል፤ ይግባኝም መብት ነው ተብሏል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## ደመወዝ በወረፋ !

**ቦጋለ አበበ**

ሰልፍ መያዝና ወረፋ መጠበቅ የእለት ከእለት አንዱ ተግባራችን ከሆነ ቆይቷል። ቢያንስ በቀን አንዴ ለሆነ ነገር እንሰለፋለን ወይም ረጅም ሰዓት ወረፋ እንጠብቃለን። በተለይም በመዲናችን አዲስ አበባ የማንሰለፍበት ወይም ወረፋ የማንጠብቅበትን ጉዳይ አውጥተን አውርደን አናገኝም ቢባል አልተጋነነም። ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ፣ ስራ ለመግባትና ከስራ ወደ ቤት ለመሄድ ረጃጅም የታክሲ ሰልፎችን እግራችን እስኪቀጥን ቆመን መጠበቅ እንደ አንድ የስራ አካል ሆኖ ስለተለመደ ወደ ጎን እንተወው። ዳቦ ለመግዛት ሰልፍ፣ ወደ ተቋማት ጎራ ብሎ የፈለጉትን አገልግሎት ለማግኘት ወረፋ፣ የመብራትና ውሃ ክፍያ ለመፈጸምም እንደዛው። ብቻ ምን አለፋን አልተሰላም እንጂ በእለት ከእለት እንቅስቃሴያችን ለስራ ከምናውለው ሰዓት በሰልፍና በወረፋ የምናቃጥለው ሰዓት ጆሮን ጭው ሊያደርግ ይችላል።

በታክሲ፣ በዳቦ፣ በዘይትና ስኳር መሰለፍ የተለመደ ብርቅም ያልሆነ የሕይወታችን አንዱ አካል በመሆኑ ወደ ዋናው ጉዳይ እንግባ። የባንኮች ጉዳይ። እነ ታክሲና ዳቦስ አማራጭ ስለሌለን ተሰለፍን። እንደ አሸን እየፈሉ የሚገኙ ባንኮቻችን የገዛ ገንዘባችንን ለማንቀሳቀስ የሚያሰልፉንና ረጅም ሰዓት ወረፋ የሚያስጠብቁን ነገር ግን ያበሳጫል።

ባንኮች አካውንት ካልከፈታችሁ ብለው በየመንገዱ ብቻ አይደለም የሚያስቸግሩን። በየቢሮውም እየሄዱ ፍጹም ትህትናና ያገልጋይነት መንፈስ ተሞልተው ከሌለን ላይ ጭምር እንድንቆጥብ ማሳመን አይሳናቸውም። አገልግሎታቸውን ፈልገን ደጃቸው በጠናን ወቅት ግን የቀድሞ ትህትናቸው እምጥ ይግባ ስምጥ እነሱ ብቻ ናቸው የሚያውቁት።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባንኮችም እንደ ታክሲና ዳቦ ቤቶች ተገልጋዮችን ረጅም ሰልፍ ካላሰለፉ የአገልግሎት ሰጪነት ፍላጎታቸው አልከፈት እያለ ነው። ባንኮችን ከታክሲዎችና ዳቦ ቤቶች የሚለያቸው ሃብታም ድሃ፣ ወንድ ሴት ብለው ሳይለዩ ሁሉንም ለሰልፍና ወረፋ መዳረጋቸው ነው። ሃብታም ሲባል ግን ግዙፎቹን ከበርቴዎች እንዳልሆነ ግልጽ ነው። በግል ስራ የሚንቀሳቀሱ ነገር ግን በየእለቱ ከተቀጣሪ ሰራተኞች የተሻለ ገንዘብ የሚያንቀሳቅሱትን ለማለት ያህል ነው። መካከለኛ ገቢ ያላቸውን ማለት ሳይቀል አይቀርም። ከቤተሰቡ የተላከለትን ሁለት መቶ ብር ከሚያወጣ ተማሪ ጀምሮ የታሰሩ ረብጣ ብሮችን እስከሚያስገባ ነጋዴ ድረስ ሁሉም በባንኮቻችን ወረፋ ጠባቂ ነው።

በተለይም ባንኮች በሰልፍና ወረፋ ተጨናንቀው የታክሲ ተራ የሚመስሉበት የደመወዝና የበዓላት ወቅቶች ያላማረሩት ሰው የለም። በእርግጥ ባንኮች ሲባል ሁሉንም መኮነን እንዳይሆን ብዙዎቹ የግል ባንኮች ላይ ይህ ችግር ጎልቶ አይታይም። የመንግስት ባንኮች ግን እንኳን የደመወዝ ወቅት ወትሮውንም እንዳንገላቱን ነው። እንግልት መፈጠሩ ሳይሆን የሚፈጠርበት ምክንያት ደግሞ ከሁሉም አናዳጅ ነው። ከተገልጋዮች ብዛት አኳያ መጨናነቆች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ በቀናነት ልናስብ እንችላለን። ነገር ግን እንደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አይነት ብዙ የባንክ ቅርንጫፎች ያላቸው የፋይናንስ ተቋማት በርከት ያሉ የአገልግሎት መስጫ መስኮቶች ይዘው ለአገልግሎት ክፍት ሆነው የምናገኛቸው በጣት የሚቆጠሩትን ብቻ መሆኑ ልንወቅሳቸው ከበቂ በላይ ምክንያት ነው። እግር ጥሎን ወደ አንዱ ባንክ ቅርንጫፍ ጎራ ካልን አንዳንድ የባንክ ሰራተኞች አገልግሎት የሚሰጡበትን መስኮት ጥለው በሌላ ስራም ይሁን በግል ወሬ ተጠምደው ልናገኛቸው እንችላለን። ተገልጋይ ተሰልፎ እያዩ እንኳን አይሞቃቸውም አይበርዳቸውም።

ብዙ ጊዜ በደመወዝ መቀበያ ወቅት በተለይም የኤቲኤም ካርድ የማንጠቀም ወይም በካርድ ማውጣት ከሚፈቀደው የገንዘብ መጠን የበለጠ ለማውጣት የምንፈልግ ሰዎች በቡክ አገልግሎት ለማግኘት ጎራ እንላለን። ወረፋ መጠበቂያ ቁጥራችን ያረፈባት ብጫቂ ወረቀት ይዘን ረዘም ላለ ደቂቃ ጠብቀን አገልግሎት ወደምናገኝበት መስኮት እናመራለን። ከዚያም የባንክ ባለሙያዎች ደመወዝ በኤቲኤም ካርድ ለምን አታወጡም በሚል የራሳችንን ሳይሆን የእነሱን ገንዘብ እንዲሰጡን የጠየቅን በሚመስል ቁጣና ግልምጫ ሊመልሱን ይችላሉ። እሺ በካርድ መጠቀም ስልጣኔ ነው ብለን እንቀበል። ካርዱን የምንጠቀምባቸው የኤቲኤም ማሽኖች በየባንኮቹ ቅርጫፎች በብዛት ተገትረው አገልግሎት የሚሰጡት ግን እጅግ ጥቂቶቹ የመሆናቸው ጉዳይስ?። እንዲያውም በደመወዝ ወቅት አገልግሎት የሚሰጡ ማሽኖችን ከረጅም ሰልፍና ወረፋ ጋር በአቅራቢያችን ፈልገን ካገኘን እድለኛ ነን ማለት ነው። የኤቲኤም ማሽኖች እዚያው ባንኩ በር ላይ ቆመው ለረጅም ጊዜ ወይ አገልግሎት አይሰጥም ወይም ብር የለውም ወይ ደግሞ በጥገና ላይ ነው የሚሉት ነገር ይበልጥ ያበሳጫል። እዚያው የባንኩ ቅርንጫፎች ጋር የቆሙ ማሽኖች በሲስተምም ይሁን በሌላ ችግር ላይሰሩ ይችሉ ይሆናል። ግን ለረጅም ጊዜ እዚያው አጠገባቸው ቆመው መላ የሚፈጥርላቸው ጠፍቶ ደመወዛችንን ለመውሰድ ወረፋ ሲያስጠብቁን ማየት ግዴለሽነት እንጂ ሌላ ምን ይባላል።

የባንኮችን ብቻ ሃጢያት ማብዛት እንዳይሆንብን የእኛ ተጠቃሚዎችንም ችግር ማንሳት ተገቢ ነው። በተለይም ከኤቲኤም አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ብዙ ጊዜ አንድ ችግር አለብን። የያዝነውን የኤቲኤም ካርድ መጠቀም የምንፈልገው ካርዱን ካወጣንበት ባንክ ማሽን ብቻ ነው። አገልግሎት መስጠት የሚችሉ የሌሎች ባንኮች ማሽኖች አጠገባችን እያሉ ካርዱን ያወጣንበት ባንክ ማሽን ካልሆነ ብለን ረጅም ሰልፍ መጠበቅን የምንመርጠው ነገር አለ። አንዳንዶቻችን ይሄን የምናደርገው ካለማወቅ ነው። አንዳንዶቻችን ደግሞ ካርዱን የሰጠን ባንክ ማሽን ለአገልግሎት ከሚቆርጥብን ገንዘብ በላይ በሌላ ማሽን ስንጠቀም የሚቆርጥብንን ገንዘብ አስልተን ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከምንጠብቀው ወረፋና ሰልፍ አኳያ የያዝነውን ካርድ ባገኘነው ማሽን ብንጠቀም ልዩነቱ ያን ያህል የጎላ አይደለም። እዚህ ጋር ያለውም የሲስተም ችግር መዘንጋት የለበትም። እናም ባንኮች ሆይ ወደ ዘመናዊ(ዲጂታል) አሰራር ለመሸጋገር ከምታደርጉት ጥረት ጎን ለጎን ደንበኞቻችሁ በጥቃቅን ክፍተቶች የሚጉላሉበትን ነገርም አስቡበት።

# ዓለም አቀፍ



## የኮንጎ ጦር በኤም 23 አማፂያን ላይ አዲስ ጥቃት ከፈተ

የዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ጦር በኤም 23 አማፂያን አዲስ ጥቃት መክፈቱ።

በሰሜን ኪቩ በሩትሹሩ ግዛት ሐሙስ እለት እና ዓርብ ጠዋት በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ጦር እና በኤም 23 አማፂያን መካከል ውጊያ መደረጉን ቢቢሲ ዘግቧል።

በአካባቢው የሚሰራ አላይን ሚሮቫ የሚባለው ጋዜጠኛ በአካባቢው ከሳምንታት መረጋጋት በኋላ በተፈጠረው ውጊያ በርካታ ሰዎች ቀያቸውን ጥለው እየሸሹ መሆናቸውን ተናግሯል።

በአካባቢው የሚገኝ የሲቪል ማህበረሰብ ቡድን በመገናኛ ብዙሃን ለሚዲያ በሰጡት አስተያየት፣ ጦርነቱ ከመባባሱ በፊት አማፅያኑ በሰራዊቱ ቦታዎች ላይ ጥቃት መሰንዘር መጀመራቸውን ገልጿል።

ጥቃቱን ተከትሎ የመንግስት የጸጥታ ኃይሎች በአማፅያኑ ላይ ጥቃት መሰንዘር መጀመራቸውንና በቦታቸው ላይ ጥቃት መፈጸሙን ተናግረዋል። ሰሞኑን ቡድኑን ለማጥፋት በሚደረገው እንቅስቃሴ ለመሳተፍ ኬንያ ወታደሮቿን ወደ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ የላከች ቢሆንም ወታደሮቹ በአሁን ወታደራዊ ኦፕሬሽን ላይ መሳተፋቸውና አለመሳተፋቸውን አስመልክቶ የተባለ ነገር የለም።

ኤም 23 ከሰኔ ወር ጀምሮ የአገሪቱ የድንበር ከተማ የሆነችውን ቡናጋና እና በዙሪያዋ ያሉትን አካባቢዎች መቆጣጠራቸው ይታወሳል። በሌላ በኩል ደግሞ ሩዋንዳ የኤም 23 አማፂያንን ትደግፋለች ስትል ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ስትከስም ሩዋንዳ ግን ወቀሳው ያለማቋረጥ ስታስተባብል ቆይታለች።

## ኢራን የድሮን ባለሙያዎቿን በክሬሚያ ማሰማራቷን አሜሪካ አስታወቀች



ኢራን የሰው አልባ አውሮፕላኖች /ድሮኖች/ ባለሙያዎች በዩክሬን በማሰማራት ጥቃቱን ስትደግፍ ቆይታለች ስትል አሜሪካ ማስታወቋን ቢቢሲ ዘግቧል።

በሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት የአውደ ውጊያ መጧጧፍ የድሮኖች ተሳትፎ በእጅጉ ይነሳል። በዩክሬን መሰረተ ልማቶች ውድመትም ድሮኖች በተለይ የኢራን ሰራሽ መሆናቸው የሚታመን "ካሚካዜ" የሚባሉ ሰው አልባ አውሮፕላኖች የአንበሳ ድርሻ እንደ ነበሩ በተደጋጋሚ ይነገራል።

ሩሲያ የዩክሬን ዋና ከተማ ኪዬቭ ባሳለፍነው ሰኞ "በካሚካዜ" የሰው አልባ አውሮፕላኖች መደብደቧ የሚታወስ ቢሆንም አሜሪካ ከድሮኖቹ ጥቃት ጋር ተያይዞ ሁሌ ኢራንን እንደ ወነጀለች ትደመጣለች።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በክሬሚያ የተፈጸሙ የድሮኖች ጥቃት ጀርባ የኢራናውያኑ አሰልጣኞች እና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች እንዳሉ የዋይት ሃውስ ብሄራዊ ደህንነት ቃል አቀባይ ጆን ኪርቢ አመልክተዋል።

ቃል አቀባዩ ለጋዜጠኞች ሲናገሩ "የኢራን ወታደሮች በክሬሚያ እንዳሉ እና ሩሲያን እንደረዱ ገምግመናል" ካሉ በኋላ "በአንጻራዊነት አነስተኛ" ቁጥር ያላቸው ኢራናውያን የቴክኒክ ድጋፍ እየሰጡ ሲሆን ሰው አልባ አውሮፕላኖቹን የሚያበሩት ደግሞ ሩሲያውያኑ ናቸው ብለዋል።

አክለውም፣ "ቴህራን አሁን በቀጥታ በመሬት ተሳታፊ ሆናለች። ተሳትፎዋም በዩክሬን ውስጥ በሲቪሎች እና በሲቪል መሠረተ ልማቶች ላይ ተፅዕኖ ያላቸውን የጦር መሳሪያዎች ማቅረብ ነው" ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ኢራን ለሩሲያ በመወገን በዩክሬን ሕዝብ ላይ የምታቀርበውን እነዚህን መሣሪያዎች ለማጋለጥ፣ ለመከላከል እና ለመጋፈጥ አሜሪካ ሁሉንም ዘዴዎችን እንደምትከተልም የኢራን ሰው አልባ አውሮፕላኖቹን በማቅረብ ኃላፊነት በወሰዱ የንግድ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ላይ ማዕቀብ መጣሏን ዩናይትድ ኪንግደም አስታውቃለች።

**"ካሚካዜ" የሰው አልባ አውሮፕላን ምንድነው?**

ካሚካዜ ማለት የጃፓን ቃል ሲሆን አጥፍቶ ጠፊ የሚል ትርጉም አለው። ጃፓኖች ቃሉን በስፋት ጥቅም ላይ ያዋሉት በሁለተኛ የዓለም ጦርነት ሲሆን የጃፓን አብራሪዎች አውሮፕላኖችን በመጠቀም ተቀጣጣይ ፈንጂችን ጠላቶቻቸው ላይ በማፈንዳት ጀብዱ ሲፈጽሙ ቆይተዋል።

አሁን ላይ በሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት ጥቅም ላይ እየዋለ ያለው የኢራን ሰራሽ መሆኑ የሚነገረውና 36 ኪሎ ግራም ክብደት መጫን የሚችል የካሚካዜ ድሮን ኢላማው በትክክል እስኪያገኝ በአየር ላይ አድፍጦ የመቆየት ልዩ ችሎታ እንዳለ ይነገራል። ዝቅ ብሎ የመብረር ችሎታውም በጣም ከፍተኛ ነው።

ይሄው ሻሄድ-136 ካሚካዜ ድሮን አየር ላይ አድፍጦ የመቆየት ችሎታ ብቻ ሳይሆን ከራዳር እይታ ለመሰወር የሚያስችል ቴክኖሎጂ የተገጠመለት ከመሆኑም በላይ ክንፎቹ 2 ነጥብ 5 ሜትር ክንፍ ያሉ በመሆኑ በቀላሉ ለጥቃት አይጋለጥም።

ሩሲያውያኑ ጀረኒዬም-2 ብለው የሚጠሩት ይሄው ካሚካዜ ድሮን ሩሲያ ከመስከረም አጋማሽ ጀምራ በዩክሬን ጦርነት መጠቀሟን ምዕራባውያን ቢከሷትም ሩሲያ ግን የኢራን ሳይሆን የራሷን ድሮን ጥቅም ላይ ማዋሏን በተደጋጋሚ ስትገልጽ ቆይታለች።

ይሁን እንጂ በጦርነት ድሮንን ጥቅም ላይ ያዋለች ሩሲያ ብቻ ሳይሆን ዩክሬንም ጭምር ነው። በዩክሬንም ሆነ በሩሲያ ግዛቶች በተለይ በከተሞች አካባቢ በመሰረተ ልማቶች ላይ የደረሱት ውድመቶች በድሮን ጥቃት መሆኑ ታምኖበታል።

ከተዋጊ አውሮፕላኖችና የጦር ድሮኖች ጋር ሲነጻጸርም የካሚካዜ ድሮን ዋጋ በጣም ርካሽ ነው። በዚሁ መሰረት የአንድ የጦር ድሮን ዋጋ በጥቂቱ ሁለት ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሲሆን የካሚካዜ ድሮን ዋጋ ግን 20ሺ የአሜሪካን ዶላር ብቻ ነው።

# መጋቢ አዕምሮ

# ቅንዓት ሲመቸው

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

“በቅናት ውስጥ አትገኝ፤ በሕይወት ጉዞ ውስጥ አንዳንዴ ትቀድማለህ አንዳንዴም ትቀደማለህ” ይህን ያሉት ሜሪ ሽሚች (Mary Schmich) የተባሉ የሃርቫርድ ምሩቅ ጋዜጠኛና ደራሲ ናቸው። መቅደምና መቀደምን አስልቶ የሚነግር አወዳዳሪ በሌለበት ነገር ግን የተቀደምን ወይንም የቀደምን የሚመስለን የራሳችን ስሌት ቅንዓት ከተሰኘው ፎርማታ ላይ አድርሶን ራሳችንን ልናገኘው እንችላለን። ቅንዓት በልባችን ውስጥ ቦታን ሲይዝ የሚፈጥረው አሉታዊ ተጽእኖ ላይ የዘርፉ ባለሙያዎች ጥናቶችን እያጠኑ የሰው ልጅ ከመርዝ ራሱን እንዲጠብቅም ይመክራሉ።

## መንደርደሪያ ታሪካችን ውስጥ እንስፍ፤

በጥቃቅን በሚባል የሱቅ ንግድ ላይ የተሰማሩ ሁለት ጎረቤታም ወጣቶች ናቸው። አንደኛዋ የሞባይል ቻርጀርና የጆሮ ማዳመጫ (ኤርፎን) የምትሸጥ ስትሆን ጎረቤቷ ደግሞ የባልትና ውጤቶችን ትሸጣለች። ሁለቱም በማለዳ ሱቃቸውን የሚከፍቱ አመሻሽተው ወደ ቤታቸው የሚሄዱ አብረው ሳምንታዊ እቁብ የሚጥሉ የሥራ ባልደረባ ናቸው።

አንዳቸው ስሌላቸው ስራ አንስተው የሚያደርጉት ወሬ ቀስ በቀስ በልባቸው ውስጥ የቅንዓት መንፈስን የሚፈጥር እየሆነ ነበር። የባልትና ውጤት አቅራቢዋ የራሷን ስራ ለማዋደድ፤ ባልትና ለሰው የሚሆን ምግብ ነው፤ ያለ ባልትና የሚሰራ ስራ የለም፤ ያለ ባልትና እንዴት ሆኖ የሰው ልጅ የአመጋገብ ሥርዓቱን ሊያስብ ይችላል። ወዘተ በማለት የባልትና ውጤት ላይ መሰማራት ስላለው ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ታብራራለች። ጎረቤቷ ደግሞ ስልክ በዚህ ዘመን ስላለው ቦታ፤ ሁሉም እንቅስቃሴ ከስልክ ጋር የተገናኘ መሆኑን፤ ስልክ ደግሞ ያለ ሞባይል ቻርጀር ምንም መሆኑን ታነሳለች። የኮሌጅ ተማሪዎች የራሳቸውን የትምህርት ዘርፍ አዋደው በማቅረብ እንደሚያደርጉት ፉክክር፤ ህጻናትም በተመሳሳይ ሁኔታ ባላቸው ነገር ሌላኛውን ለማስቀናት የሚሄዱበት የእንቁልልጭ አይነት መንገድ።

ሁለቱ ጓደኛሞች እንደ ቀልድ ሁሌም የሚያነሱትን የባልትና ውጤትና የሞባይል ተጓዳኝ ስራን ፉክክር የሚመለከት አንድ የጋራ ጓደኛቸው አንድ ቀን፤ እናንተ እኮ “ቅንዓት ሲመቸው” ናችሁ አላቸው። ቅንዓት ሲመቸው ማለት ሰው የፈለገውን ሥራ እየሰራ ነገር ግን ሌሎች በሚሰሩት ስራ የሚቀና ሆኖ የሌሎችን ሥራ በማጣጣል በውስጡ የሚሰማውን የቅንዓት ስሜት የሚያስታግስበት ማለት ነው አላቸው። ሁለቱም የጎረቤታቸውን ትርጉም እንደማይቀበሉ ነገሩት። እነርሱ መካከል ቅንዓት እንደሌለም አስረዱት፤ ለጨዋታ ሲባል የሚያቀርቡትን ነገር እንደ ቁምነገር ወስዶ እንዳከረረውም ነገሩት። እርሱ ግን ከልቡ ነበርና በሃሳቡ ጸና።

የመንደርደሪያ ታሪኩን ወደ ቀን ተቀን ውሏችን እናምጣው። በምንሰራበት የሥራ ቦታ እርስ በእርስ ባለን ግንኙነት ውስጥ ቅንዓት ሲመቸው እንዴት እንደሚታይ እንመርምር። በቤተሰብ መካከል ከወንድሞቻችንና እህቶቻችን መካከል ባለን ግንኙነት ውስጥ ቅንዓት ሲመቸው እንዴት ሥጋ ለብሶ እንደሚታይ እንመልከት። ቤተዘመድ ለደስታም ሆነ ለሃዘን በሚገናኝበት ጊዜ የሚኖረው የመገፋፋት ሆነ የመቀራረብ ስሜት ትርጉሙን እናጢነው። የቅንዓት ጉዳይ በሰፊው በቀን ተቀን ሕይወታችን ውስጥ ቦታ እንዳለው የተለያዩ ጥናቶች ያረጋገጡት እውነታ ነውና ወደ ውስጣችን ተንፍሰን በምን ያህል እንደጎዳንም እንመርምር። በባልና ሚስት መካከል ያለው ቅንዓት ደግሞ ትርጉም ከፍ ያለ የግንኙነት ችግር ሆኖ የሚገኝም ነው።

ሁለቱን ባለ ሱቅ የቅንዓት ሲመቸው ማሳያዎችን የጋራ ጓደኛቸው እንዲህ አላቸው “የተመቸንን ስራ በገዛ ፈቃዳችን መርጠን እየሰራን ሌሎች መርጠው በሚሰሩት ስራ ላይ አይናችንን ማድረግ አይገባም” ሲልም መከራቸው።

## ዝርዝሩን አለማወቅ

የሌሎችን ሥራ ተመልክተን ከራሳችን ጋር በማነጻጸር ውስጥ ለስራችን አነስተኛ ግምት እንድንሰጥ በሌሎች እንድንቀና የሚያደርገን አንዱ ነገር ዝርዝሩን አለማወቅ ይሆናል። ከሩቅ ሆኖ አንድን ሥራ ስንመለከተው በቀላሉ የሚሰራ እንደሆነ እናስባለን። ስራውን ጠጋ ብለን ስንመለከት፤ ሥራውን ለመስራት ጥረት ስናደርግ ግን ዝርዝሩ ውስጥ ያለውን ሰይጣን እንጋፈጠዋለን። ሥራን መሰረት ያደረጉ መቀናናቶች የከፋ ጉዳት በግንኙነት ውስጥ በማይፈጥሩበት ደረጃ ውስጥ ሊገኙ ቢችሉም የራስን ስራ አሳንሶ የሚያሳይ ሆኖ ሊገኝ ይችላል።

ሥጋ ቤት ያለው ሰው ስራውን ከጋራዥ ቤት ጋር ሲያወዳድር እኔ ያለሁበት ዘርፍ ይህን ያህል አድክሞኝ ይህን ያህል አውጥቶ አውርዶኝ ሲል፤ ጋራዥ ቤቱ ደግሞ ከትምህርት ቤት ጋር አነጻጽሮ ትምህርት ቤት ቁጭ ብሎ ገንዘብ ማፈስ እንደሆነ ሲረዳ፤ ትምህርት ቤት ከቡና ሻጩ ጋር አወዳድሮ የራሱን ትርጉም ሲሰጥ፤ ቡና ሻጩ ከሪል ስቴት ጋር አወዳድሮ ለራሱ ስራ ተራ ትርጉም ሲሰጥ ወዘተ ዝርዝሩን አለማወቅ የፈጠረው ቅንዓት ይወለዳል።

የቅንዓት ስሜቱ ከውሳኔዎቻችን ጀርባ የሚገኝ፤ ሰዎች በጀመሩት ነገር ላይ አተኩረው እንዳይጸኑ የሚያደርግ ሁሌም ከአንድ ዘርፍ ወደ ሌላ ዘርፍ እየዘለሉ እየሄዱ አተኩረው በአንድ ነገር ላይ ውጤት እንዳያመጡ የሚከለክል ነው።

በመንገድ ላይ ከምናስተውላቸው ነገሮች መካከል አንዱ በመኪና ላይ ተጽፎ የሚገኙ ጽሁፎችን ነው። በመኪና ላይ ተጽፈው የሚገኙ ጽሁፎች አስቂኝ፣ አዝናኝ እንዲሁም በማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ማህበረሰባዊ አስተሳሰብን የሚያሳዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። እንደ ማህበረሰብ ሃዘንንም ሆነ ደስታን በተለያዩ መንገዶች የማስተዋወቅ ልማድ ያለን መሆኑ ይታወቃል። እረኞች በዜማ ሃሳባቸውን ያንጸባርቃሉ። የበዓል ቀናት ላይ የሚቀርቡ ባህላዊ ጭፈራዎች ከፖለቲካዊ እስከ ልዩ ልዩ ማህበረሰባዊ ጉዳዮች ድረስ መልእክት የሚተላለፍባቸው መሆኑ ይታወቃል። ስለ ቅንዓት የሚናገሩ የታክሲ ውስጥ ልጥፎችን እናያለን። አንዳንዱ ከመኪናው ጀርባ ላይ ስለሚቀኑበት ሰዎች ይጽፋል። በማህበራዊ መስተጋብራችን ውስጥ ያሉ ህጸጾች ተጽፈው እናነባለን። ስለ ቅንዓት፤ ስለ ፍቅር፤ ስለ ማሴር፤ ስለ ምቀኝነት ወዘተ።

በሌሎች ሥራ፣ ውበት፣ ትዳር፣ ትምህርት ወዘተ ላይ የሚፈጠር የቅንዓት ስሜት ለምን ሊፈጠርብን እንደሚችል እንጠይቅ። እንዲሁ ለምቀኝነት ወይንስ ራሳችን አንሰን እንዳለን በመመልከት። ቅንዓት በስፋት በሚገኝበት ቦታ ላይ ምቀኝነት ቤቷን ሰርታ ስለመገኘቷ ጥርጥር የለውም።

## ቅንዓት የወለደችው ምቀኝነት

ሸገር 102.1 ከሰሞኑን ከተላለፉት መሰናዶች መካከል አንዱ በአዲስ አበባ ስለሚገኝ የምቀኞች ሰፈር ይመለከታል። የሰፈሩ አባላት ራሳቸውን ምቀኛ እንደሆኑ እየገለጹ ስለሰፈራቸው ያብራራሉ። የሰፈሩ አባላት ምቀኞች መሆናቸውን ለጋዜጠኛው ምላሻቸውን ሲሰጡ ይደመጣል። መመቅኘት አንዱ በአንዱ ላይ መሸረብ የሰፈሩ ሰዎች ባህሪ መሆኑን ይናገራሉ። ወሬው ትኩረት የሚስብ ነው። ጋዜጠኛው እንዴት ይህ ሊሆን እንደቻለ ጥያቄ ሲያቀርብ ያገኘው ምላሽ ወደ ደርግ ጊዜ በምናብ መሄድን ይጠይቃል። በደርግ ዘመን ነዋሪው መሰረታዊ ፍጆታዎቹን በራሽን ከመንግሥት ለመቀበል ይሰለፋል። ሰው ሁሉ ተሰልፎ በሚገኝበት ቦታ ላይ የእዚያ ሰፈር ሰዎች ጣልቃ ለማስገባት ፍቃደኛ ስላልሆኑ እርስ በእርሳቸው የሚመቀኙ አድርገው ራሳቸውን ቆጠሩ። የሌላ ሰፈር ሰዎች ሌላውን ለማስቀደም ፍቃደኝነት የሚታይባቸው መደጋገፍ ያለባቸው ሲሆኑ የምቀኛ ሰፈር ሰዎች ግን ወይ ፍንክች ስለሚሉ ለራሳቸው እኛ ምቀኞች ነን በማለት የሰፈራቸው ስም መጠሪያ አደረጉት። መጠሪያውም እስከ ዛሬ ድረስ ዘልቆ ለራዲዮ ዘገባ በመብቃቱ ሰማነው።

በፕሮግራሙ ላይ የተሳተፉ ሰዎች ምን ቢሆን ይሻላል ትላላችሁ? ተብለው ሲጠየቁ ሁሉም ያስተላለፉት መልእክት አስደሳች ነበር። ሁሉም ምቀኝነት ኮነኑ፤ ሁሉም መተጋገዝ ለሰው ልጆች አስፈላጊ እንደሆነ አስረዱ፤ ሁሉም በዚህ ዘመን በመተጋገዝ እንጂ በመመቀኛኘት መሻገር እንደማይቻል ድምጻቸውን አሰሙ። አንድ እናት ግን ሰፈሩ ሙሉ ለሙሉ መፍረስ አለበት ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጡ። የምቀኞች ሰፈር የሚባለው ከየት እስከየት እንደሆነ አመልክተው የምቀኝነት ታሪክ እንዲዘጋ ሰፈሩ መፍረሱ መፍትሔ እንደሆነ ተናገሩ። እዚህ ጋር ጥያቄ እናንሳ፤ በትውልድ መካከል እየተላለፈው የመጣው የምቀኞች ሰፈር የምቀኝነት ሕይወት እንዴት ተጀመረ? ከሚለው ጥያቄ ጀርባ በምን ያህል ርቀት ቅንዓት እንደምትገኝ እንጠይቅ።

ቅንዓት ያደረብን ነገር እንዲሳካለት ካለመፈለግ የተነሳ የምናደርገው ነገር ምቀኝነትን ያስከትላል። በእያንዳንዱ ውሳኔያችን ውስጥ ምቀኝነት እየተተገበረ እንደሆነ በመጠየቅ ከሰዎች ጋር ያለንን መስተጋብር ማስተካከል ለራሳችን ስንል አስፈላጊ ነው። መፍትሔውም የቅንዓት ገመድ ከልባችን በምን ያህል ርቀት ላይ እንደሚገኝ መመርመር።

## ከልባችን ምን ያህል የራቀ ነው

ብዙ ሰው ከካንሰር በላይ የሚሞተው በቅንዓት እንደሆነ ጥናት ያደረጉ ባለሙያዎች የጠቀሱትን አንብበናል። ቅንዓት ከበሽታዎች ዝርዝር ውስጥ የሚመደብ መሆኑንም ያስረዳል። ሰዎች በእኛ ላይ በቅንዓት ቢነሱ አንፈልግም። በምንሰራው ስራ ላይ በምቀኝነት የሚነሳም እንዲኖር ፈጽሞውኑ መሻታችን አይደለም። በምናደርገው እንቅስቃሴ ውስጥ ተጽእኖው እንዳያድርብን እንፈልጋለን። ቅንዓትም ሆነ ምቀኝነት ሁለቱም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ሆነው በሕይወታችን ውስጥ ቦታ ባይኖራቸው እንፈልጋለን። ወደ መፍትሔው እንሂድ ስንል የምናገኘው ምላሽ ከልብ ጋር የተገናኘ ነው፤ ልብን ማንጻት።

እያንዳንዱ ሰው ልቡን የመጠበቅ ሃላፊነት አለበት። ምቀኝነት ከልባችን በምን ያህል ርቀት ላይ እንደሚገኝ መረዳት አስተዋይነት ነው። የማህበረሰባዊ አኗኗራችን እና ስሪታችን ምን መሆን እንዳለበት በመረዳት ቅንዓትንም ሆነ ምቀኝነትን በአግባቡ ማድረግ ይኖርብናል። የሰዎች እድገት ውስጥ ትምህርት የሚሆነን ከመፈለግ ባሻገር ጠልፎ መጣልን ማሰብ ተገቢነት የለውም። ሰዎች አልሳካላቸው ሲል የሚሰማን ደስታ ይኖር ይሆን? የሰዎች ገመና በአደባባይ ሲወጣ ወሬውን ስንቀባበል በውስጣችን የሚፈጥረው ስሜትስ ምን ይሆን? ልባችንን በታማኝነት በጥንቃቄ ስንጠይቅ ለዚህ ምላሽ ትክክለኛ መልስ እናገኛለን። የሰዎች ውድቀትን ለማውራት የምንፈጥነው ደስ ስለሚለን ይሆን?

እነዚህ ጥያቄዎች ለራስ ግልጸኛ በመሆን ውስጥ ምላሽ የሚፈልጉ ናቸው፤ ከልብ ጋር አብሮ በመምከር ያለንበትን ሁኔታ መረዳት እንድንችል የሚያደርገን። ሰው ከሰው ጋር አብሮ የሚሰራ፤ አብሮ የሚበላ፤ አብሮ የሚኖር፤ አብሮ ችግርንም ሆነ ደስታን የሚያሳልፍ እንደመሆኑ በአብሮነት ውስጥ ዋጋን የሚያሳጡ አላስፈላጊ ባህሪዎችን ማስወገድ አለብን። እርስ በእርስ የሚኖር የኑሮ ውድድር ወዴት የሚያደርሰን እንደሆነ መመርመር ያስፈልጋል። ባለን ነገር እርካታ እንዳይሰማን ሁሌም ሌላው የያዘውን ነገር አድንቀን የምንይዝ ሆነን እንዳንገኝ ልናስብ ይገባናል።

ነገሮች ከልባችን ጋር ባላቸው ርቀት መመልከት አዋጭ የሚሆንበት ዋና ምክንያት ልባችን ውስጥ የሞላውን ለመኖር በብዙ ትኩረት የምናደርግ ስለሆነ ነው። እንደ ማንኛውም ሰው ስኬትን እንፈልጋለን። እንደማንኛውም ሰው ያሰብነውን አሳክተን ማለፍን እንፈልጋለን። እንደ ማንኛውም ሰው ስንወድቅ መነሳትን፤ ስንዝል መበርታትን፤ ተስፋ በመቁረጥ ውስጥ በዚያው አለመቅረትን፤ በፈተና ብዛት ጠንክሮ መውጣትን እንፈልጋለን። ምናልባትም በዙሪያችን ካሉ ሰዎች በተለየ ሁኔታ ለጥረት ቦታ የምንሰጥ በታታሪነታችን ስማችን የሚጠራም ሊሆን ይችላል። ይህ ሁሉ ግን ከልባችን ጋር ባለው ቅርበት እግራችንን የሚያራምድ ነው።

ዛሬ ልብህን የሞላውን አዳምጠው። በልብሽ ውስጥ ቦታ የያዘውን ነገር መርምሪው። በጥያቄው



ውስጥ አድርገን የተግባራ እርምጃችንን እንመልከት። ልባችንን የሞላውን ለማድረግ አብዝተን እንራመድ። አንዳንዴ እያመነታንም ይሁን በልበ ሙሉነት እንቅስቃሴ የምናደርገው ልባችን በሞላው ነገር ልክ ነው። ልባችንን የሞላው ምቀኝነት ከሆነ ቆም ብለን ማስተካከያ ለማድረግ መዘግየት የለብንም።

በተጨባጭ ልባችንን የሞላው በሌሎች ስኬት በመቅናትና አቃቂር በማውጣት ከሆነ ለራሳችን ፈጥነን መገኘት አለብን፤ እየጎዳን ያለነው ያንን ሰው ሳይሆን ራሳችንን ስለሆነ። ከወዳጅ ላይ የማይታየን ጉድፋት ቅናት ባደረብን ሰው ላይ ጎልቶ የሚወጣ ከሆነ እንቅስቃሴያችን የመርህ አይደለም ማለት ነው። አንዳችን በሌላችን ላይ ያለውን ድክመት ነቅሶ በማውጣት ረገድ ጎበዞች እንደሆንን ይታያል። የራሳችንን ድካም ለመመልከት ግን የምናየው ነገር እምብዛም ነው። በተጨባጭ ግን የራስን ድካም እየመረመሩ መመላለስ አስፈላጊነቱ የሚካድ አይደለም። ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ውስጥ ልባችንን እየመረመሩ መንቀሳቀስ መልካሙም ሆነ ክፉ ስሜት ከልባችን ጋር ካለው አንጻር ብንመረምር አትራፊ እንሆናለን። የምርመራውን የመጀመሪያ ተግባር ልክ እንደ እንቅልፍ የእረፍት ምእራፍ ነው። ከራሳችን ጋር ጊዜ በመውሰድ ውስጥ ውስጣችን ያለውን መርዝ የምናጥብበት ሰዓት።

## እንደ እንቅልፍ ስምንት ሰዓት

በቅንዓት ውስጥ ሕይወታቸው ችግር ውስጥ ላሉ ሰዎች ካሉበት ሁኔታ ወጥተው ጥሩ የሕይወት አቅጣጫ ላይ እንዲሆኑ ከራሳቸው ጋር የሚመክሩበት ጊዜ አስፈላጊ ነው። ከሰዎች ጋር ባለመስተጋብር የተጎዳ ሕይወታቸውን ለማስተካከል የሚያስችል ከነገሮች ገለል ብሎ የሚታረፍ የእረፍት ጊዜ። ከውስጥ ሰውነት ውስጥ መርዝን አውጥቶ ለመጣል የሚረዳ እረፍት።

በእንቅልፍ ላይ ጥናት የሚያደርጉ የሳይንስ ሰዎች እንደሚናገሩት አንድ ሰው ለስምንት ሰዓታት እንቅልፍ መውሰዱ ዛሬም የግድ እንደሆነ ይናገራሉ። በስምንት ሰዓታት ውስጥ አእምሮችን ስራውን ለመስራት የሚያመነጨውን መርዝ በማጠብ ስራ እንደሚጠመድ ይናገራሉ። እንቅልፍ የሚያጣ ሰው የተረጋጋ ሕይወትን መምራት የሚቸገረው ለጤና እክልም የሚዳረገው ከእዚህ የተነሳ እንደሆነም ይናገራሉ።

ቅንዓት፤ ምቀኝነት፤ ከሰዎች ጋር ራስን እያገናኙ መብሰክሰክ በቀላሉ የሚፈጠር አይደለም። ጊዜ ወስዶ ራስን መመልከት ያስፈልጋል። አካላዊ ሰውነታችን ተገቢውን እረፍት እንዲያደርግ በአእምሮ ውስጥ የሚቀመጥ መርዝን ለማጠብ ስምንት ሰዓታት የሚፈጅ እንደሆነ ሁሉ፤ ከሰዎች ጋር ያለንን መስተጋብር በመመርመር ሁሌም በራሳችን በመተማመን የራሳችን ነገር ላይ ትኩረት አድርገን ሕይወትን በጤናማ መንገድ ለመምራት የእረፍት መርህን ለመከተል በቂ ጊዜ ያስፈልገናል። የፈውስ እንቅልፍን በመተኛት ከራስ ጋር

በመሆን፤ ነገሮችን በጥሞና በመመርመር፤ አንደበታችን ውስጥ የሚወጡ ቃላትን በማከም ከጥፋት መንገድ የምንመለስበት ጊዜ ምክንያቱም ቅንዓት በሕይወታችን ውስጥ እንዳይመቸው ሊሆን ስለተገባ። አብሮ ከመውደቅ ስለተሻለው።


የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia
የዲጂታል ባንክ አማራጮች
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
ሁሌም የሚተማመኑበት ባንክ!

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የቡራዩ የልዩ ተሰጥኦ ማበልፀጊያ- ክህሎትን የመሻት ግብ

**ዳግም ከበደ**

የአንድ አገር እድገት በብዙ መንገድ ሊለካ ይችላል። ቁሳዊ ሃብት ከሚዛናዊ ምጣኔ ሃብት ጋር ተደምሮ አንዱ የሃያልነት መለኪያ እንደሆነ ባለሙያዎች ይገልፃሉ። ከዚያ ባለፈ የሰው ሃብት ልማት፣ የተፈጥሮ ሃብትና ሌሎች መሰል ጉዳዮች የእድገትና ብልፅግና መስፈርቶች መሆናቸው ይጠቀሳል።

ከሁሉም በላይ ግን በልዩ ልዩ ዘርፎች እውቀቱንና ጉልበቱን አውጥቶ መስራት የሚችል ወጣት ሃይል ሲኖር የአገር ተስፋዋ ይለመልማል። መንግስት እነዚህን ሁሉ በአንድነት ማቀናጀትና በብቃት መምራት ሲችል ሁለንተናዊ ለውጥና እድገት እንደተመዘገበም ይቆጠራል።

በኢትዮጵያ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፤ ከአገሪቱ ህዝብ 70 በመቶ የሚሆነው መስራት የሚችል ወጣት ሀይል ነው። ይህን ሃይል በተለያየ እውቀት በማነፅና ወደ ስራ በማሰማራት አስደማሚ ፈጣን እድገት ማስመዝገብ ይቻላል። አጋጣሚውን ለመጠቀም ደግሞ አገሪቷን እየመራ የሚገኘው መንግስት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይጠበቅበታል። ከዚህ ውስጥ አንዱ ሃላፊነት ወጣቱን ሃይል በብዛት በእውቀትና በተለያዩ ችሎታዎች መቅረፅ ነው። በሚሰማራባቸው ዘርፎች ላይ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ማከናወንንም ይጠይቃል። ቀዳሚው እና አንገብጋቢው ጉዳይ ግን እውቀትን ማስታጠቅና ዝግጁ ማድረግ ነው።

ወጣቶች ብሩህ አእምሯቸውን ተጠቅመው እውቀት እንዲጨብጡ ለማስቻል ጠንካራ የትምህርት ፖሊሲ ቀርፆ ከማስተማር ባሻገር ቁሳዊ በሆነው ጉዳይ ላይም ትኩረት ማድረግ ያሻል። ከዚህ ውስጥ አንዱ ምቹ የመማሪያ ቦታ ማዘጋጀት ነው። ይህ ሲባል የመሰረተ ልማት ዘርፉን ጠንካራ በማድረግ ግንባታዎችን ማከናወንን ይጠይቃል።

የኢትዮጵያ መንግስት ለትምህርትና ሙያዊ ስልጠናዎች በፖሊሲ የተደገፈ ትኩረት በመስጠት ታዳጊዎችና ወጣቶች በክህሎት የዳበረ ችሎታ ኖሯቸው አገር እንዲጠቅሙ ለማድረግ እየሰራ ይገኛል። ለዚህ እንዲረዳ በዘርፉ ልዩ ልዩ መሰረተ ልማቶችን እየገነባ ነው። ለመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው፤ የግሉ ዘርፍ ብቻ ይሰራበት የነበረው የአጸደ ህጻናት ትምህርት ቤቶች ጉዳይ በመንግስት በኩል ይሰራበት ጀምሯል።

የልማት ማህበራት አዳሪ ትምህርት ቤቶችን ከፍተው እያስተማሩ ሲሆን፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሴቶች እንዲሁም የወንዶች አዳሪ ትምህርት ቤቶች ተከፍተው እያስተማሩ ይገኛሉ። በዚህም ተማሪዎች ትምህርታቸውን ብቻ እንዲያስቡ በማድረግ በትምህርቱ ዘርፍ ላይ ለውጥ ለማምጣት ጥረት እየተደረገ ነው።

በርካታ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአገሪቱ ተከፍተው እየሰሩ ሲሆን፣ ሰሞኑን ደግሞ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ወጣቶችና ታዳጊዎችን ተቀብሎ ተሰጥኦዋቸውን የሚያጎለብት የልህቀት ማእከል ተመርቋል።

በአዲስ አበባ ግንባታው ተካሂዶ በቅርቡ ተመርቆ እየተጎበኘ ያለው የሳይንስ ሙዚየም ከዚህ አኳያ ሊጠቀስ የሚችል መሰረተ ልማት ነው። ሙዚየሙ ወጣቶች ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ፣ እውቀትን እንዲቀስሙና ከህልማቸው ጋር በቀጥታ ተገናኝተው ያሰቡትን እንዲያሳኩ የሚያግዝ መሆኑን መመስከር ይቻላል።

ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ወጣቶች ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚያግዝ የትምህርት መሰረተ ልማት ከትናንት በስቲያ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቋል። ዛሬ በዚሁ የመሰረተ ልማት አምድ ላይ ልንዳስሰው የወደድነው ይህ ትምህርት ቤት የቡራዩ የልዩ ተሰጥኦ ማበልፀጊያ ትምህርት ቤት ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ይህን የልዩ ተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት መርቀው ሲከፍቱ "ኢትዮጵያ የብሩህ አቅሞችና ተሰጥኦዎች ባለቤት ምድር ናት። ባለ ተሰጥኦ ታዳጊዎችና ወጣቶች ክህሎታቸውን እያዳበሩ፣ አገራቸውን በቴክኖሎጂ ከበለጸጉ አገራት ተርታ እንዲያሰልፉ፣ እንደ ቡራዩ የተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት ያሉ የተሰጥኦ ማዕከላትን ማብዛት ይገባል" በማለት በትምህርት መሰረተ ልማት ግንባታ ዘርፍ በቀጣይ ሌሎች በርካታ ስራዎች መሰራት እንደሚገባቸውና መንግስትም ለዚያ ዝግጁ እንደሆነ ገልፀዋል።




ትምህርት ቤቱ አንድ ሺ ባለተሰጥኦ ወጣቶችን ተቀብሎ ማስተማር ያስችላል

"ኢትዮጵያ የምትቀየረው ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎችን የሚያበረታቱና የሚደግፉ ማዕከላት ሲስፋፉ ነው" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህ የልዩ ተሰጥኦ ትምህርት ቤት የተለየ የፈጠራ ሃሳብና ክህሎት ያላቸው ወጣቶችና ታዳጊዎች ለአገር ጥቅም ከፍተኛ ሚና እንዲያበረክቱ ያስችላል ብለዋል። አገር የሚቀየረው በወሬ ሳይሆን በፈጠራ መሆኑን ገልጸው፤ እነዚህ ባለ ልዩ ተሰጥኦዎች የፈጠራ ሃሳባቸውን ወደ ተግባር የሚቀይሩበትና የሚያበለጽጉበት አውድ መፍጠር አስፈላጊ ነው። ይህን ማድረግ ሲቻልም እነሱም ይጠቀማሉ፤ እኛም እንደ አገር እናተርፋለን ብለዋል።

"ዓለማችን በቴክኖሎጂ መጥቃለች። አገራችን ኢትዮጵያም ቴክኖሎጂ ከሚያስገኛቸው እንደ ኢኮኖሚ ካሉ ትሩፋቶች ተጠቃሚ ለመሆን፣ በዘርፉ የላቀ ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ማፍራቷ ግድ ነው›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ትምህርት ቤቱ ከየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚመጡ ወጣቶች ተሰጥኦቸውን የሚያጎለብቱበት እንደሚሆንም አስታውቀዋል። የትምህርት ቤቱ ግንባታ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ በልዩ ልዩ መንገድ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የአካባቢው ነዋሪዎችም ምስጋና አቅርበዋል። "የምንተባበር፤ የምንደማመጥ፤ በዘር በሃይማኖት የማንገፋፋ ስንሆን አገራችንን በቀላሉ ማሳደግ እንችላለን›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የሃሳብ ልዩነት ሳይገድበን አገራችንን በትብብር ማሳደግና ማበልጸግ ይኖርብናል ሲሉ አስገንዝበዋል። ‹‹በሰሜን ኢትዮጵያ ያለው ነገር ይቆጫል፤ ትግራይ ሰላም ትሆናለች፣ ከትግራይ ወንድሞቻችን በጋራ የምናለማበት ጊዜ ቅርብ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ››ሲሉም አስታውቀዋል።

### ጥቂት እውነታዎች ስለ ማእከሉ

የልዩ ተሰጥኦ ትምህርት ቤቱን ለመገንባት 708 ሚሊዮን 693 ሺህ ብር ወጪ ተደርጎበታል ። ይህ ትምህርት ቤት እስከ አንድ ሺህ ባለተሰጦዎችን ተቀብሎ የማስተማር አቅም አለው። ፕሮጀክቱ ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ በ 10 ሄክታር መሬት ላይ የሚያርፍ ይሆናል። ከትናንት በስቲያ የተመረቀው በአምስት ነጥብ አራት ሄክታር ላይ ያረፈው ፕሮጀክት ነው።

ትምህርት ቤቱ የባለተሰጥኦዎች ማደሪያ፣ የመመገቢያ አዳራሽ፣ የአስተዳደር ህንጻዎች፣ የህክምና ማዕከል፣ መማሪያ ክፍሎችና ቤተ ሙከራዎችን አካቶ የያዘ ነው። አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉት አስፈላጊ ቁሳቁስ የተሟሉለት ሲሆን፣ መጽሐፍት ፣ ኮምፒውተሮች፣ የቤተ ሙከራ ዕቃዎችንና ሌሎች አስፈላጊ ዕቃዎች አቀናጅቶ የያዘ ነው።

### የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ስለ ማእከሉ

መንግሥት የቴክኖሎጂ ፈጠራን በከፍተኛ ደረጃ ለማበረታታት የተግባር ሥራዎችን በመስራት ላይ እንደሚገኝ የሚያሳዩ በርካታ መረጃዎች አሉ። ከነዚህ ውስጥ አንዱ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ክህሎት ያላቸውን ታዳጊዎችና ወጣቶች መደገፍ የሚያስችል "የክህሎት ማእከል" ወይም የታለንት ልማት ግንባታ ማድረግ ነው። ከዚህ አንፃር ደግሞ በከፊል ተጠናቆ የተመረቀውና በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኘው የቡራዩ የታለንት/ተሰጥኦ ልማት ማእከል ፕሮጀክት ይጠቀሳል። ማእከሉ ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ በሳይንስና ቴክኖሎጂው የፈጠራ ዘርፍ ልዩ ተሰጦ ያላቸው ወጣቶችን በብዛት ለማፍራት አይነተኛ ሚና እንደሚጫወት እሙን ነው።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር አቶ በለጠ ሞላን ጨምሮ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አመራሮች ቀዳሚ አጀንዳቸው በማድረግ የታለንት ልማት ኢንስቲትዩቱ ከፊል ግንባታ ተጠናቆ እስከተመረቀበት ጊዜ ድረስ ያለበትን ደረጃ በተደጋጋሚ ጉብኝተውታል።

የአይሲቲ ልማትና ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ ዓሊ ስለ ግንባታው በተናገሩበት ወቅት "የኛ ሥራ ቴክኖሎጂ ማበልጸግ ብቻም ሳይሆን ተሰጥኦዎችን ማበልጸግም በመሆኑ መሰል ተቋማት መጀመራቸው ሊበረታታ ይገባል" በማለት የመሰረተ ልማት ግንባታውን አስፈላጊነት አስታውቀዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር አቶ በለጠ ሞላ የግንባታ ፕሮጀክቱ ግዙፍነትና ሊያሳካው የታለመለት ዓላማም ትልቅ መሆኑን አንስተዋል። በተጨማሪም ፕሮጀክቱ አገራዊ ፋይዳ ያለው እንደመሆኑና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ዜጎች ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሳይንስ፣ በኢንጂነሪንግና በቴክኖሎጂ ዘርፍ ተወዳዳሪ ለማድረግ ተሰጧቸውን የሚያሳድጉበት መሆኑን ጠቁመዋል። መሰል ተቋማት ዓለምአቀፍ አሰራርን ተከትለው በቀዳሚነት መቋቋምና ከነገም ተበድረን ልናሳካቸው ከሚገቡ ማዕከላት ቅድሚያ የሚሰጣቸውና ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ሁሉም ዜጋ ሊደግፋቸው እንደሚገባም ነው ያስገነዘቡት።

"በዓለም አቀፍ ደረጃ የተረጋገጡ ፋይዳቸው ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ፕሮጀክቶች ውጥናቸው ከማንም ቢሆን በትኩረት ፈጽመን ልናሳካቸው እና ለላቀ አገራዊና ሕዝባዊ ጥቅም ልናውላቸው እንደሚገባ ይታመናል" ያሉት አቶ በለጠ፤ መሰል ተቋማት በየክልሎች እንዲስፋፉ ለማድረግ እንዲቻል ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ እንደሚገባ ተናግረዋል። ከወዲሁ በትብብር አቅዶ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግባትም ከሚመለከታቸው ጋር ተቀናጅቶ ለመስራት ዝግጅት መደረጉንም አመልክተዋል።

### እንደ መውጫ

የሰው ልጅ ስልጣኔ ምድር ላይ በሚያሳርፈው በጎ አሻራ በቀዳሚነት ይገለፃል። ለሺህ ዘመናት የዓለማችንን የመዘመን መንገድ የበየኑና ከቀሪው ፍጥረት የሰውን ልጅ ልዩ አድርገው ያመላከቱ የሰው ልጅ አሻራውን ያሳረፈባቸውን አያሌ ህንጻዎችን መጥቀስ ይቻላል። ከነዚህ ውስጥ የሚጠቀሰው ደግሞ የሰው ልጅ በተሰጠው የማሰላሰልና በህብረት የመስራት አቅሙ ምክንያት እስካሁን ድረስ ለምስክርነት የቆሙ የህንፃ ጥበቦቹን መጥቀስ ብቻ ይበቃል።

የሮማውያንን የህንፃ ጥበብ እና የመንገድ ግንባታ ለማድነቅ የግዴታ በዚያን ዘመን ብቻ መወለድ ላያስፈልግ ይቻላል። ምክንያቱ ደግሞ ግልፅ ነው፤ 2000 ዓመታትን ዘልቀው እንኳን የእነዚያ ጥበበኞች አሻራዎች ያረፉባቸው ስራዎች ዛሬም ምስክር ናቸውና። የንጉስ ላሊበላን ተአምራዊ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ትናንት ስለነበርን ሳይሆን ዛሬም ድረስ ያለምንም እንከን አጠገባችን በመሆናቸው የሰው ልጅ ረቂቅ ክህሎት ምድራችንን በበጎ መልኩ ቀይሮ ለትውልድ የማሻገር ብቃት እንድናስተውል አድርጎናል።

ዛሬ ላይ ዓለማችን ተቀይራለች። መለወጥ ብቻ ሳይሆን የፉክክር መድረክ ሆናለች። መሰረተ ልማቶች ለቁጥር በሚታክት መልኩ ተገንብተዋል። ምድራችን በሰዎች ድንቅ የመፍጠር አቅም አጊጣለች። አገራት በየራሳቸው ቀለም አብበው ምቹ የመኖሪያ አካባቢዎችን ፈጥረዋል።

ትውልድ የራሱን ኖሮ ለመጪው ትውልድ የሚያሻግራቸው አያሌ ቅርሶችም እንደ ምድር አሸዋ የበዙ ሆነዋል። አሁን በምድር ላይ ምን ተሰራ ሳይሆን እኔ ምን አይነት አሻራ አሳረፍኩ የሚለው የበለጠ የሚያፎካክር ጉዳይ ነው። የታፈረና የተከበረ አገር ለመፍጠር አንዱ መንገድ በሉአላዊ ግዛት ውስጥ የሚተገበር የላቀ የመሰረተ ልማት ግንባታ ቀዳሚው መስፈርት ይይዛል።

ሁላችንም ለቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፍ አሻራ ማኖር ያስፈልገናል። መንግስት ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን እያከናወነ ነው። ይህን በጎ ዓላማ መደገፍ፣ ክፍተቶች ሲኖሩም ነቅሶ ማውጣት ወደፊት ለሚሰሩ መሰል ተግባራት ጠቀሜታ ይኖረዋል እያልን የዛሬውን ሃሳባችንን እዚህ ላይ እንቋጭ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢትዮጵያውያን ድምጽ ይደመጥ!

አገር የሕዝቦቿ ናት፤ ሕዝቦችም ስለ አገራቸው የሚናገሩት የእውነት የሆነውንና እንዲሆን የሚፈልጉትን ነው፡፡ ይሄ የአገርና ሕዝብ ትስስር ደግሞ ከባለቤትነት፣ እንዲሁም ከልብ መሻት የሚመነጭ ነው፡፡ ይሄ የሕዝብ የባለቤትነት እውነት፣ የጽኑ መሻት ሂደት ግን ለሕዝቡ የሚገለጥ ሃቅ ቢሆንም፤ ይሄ ሃቅ ከራሳቸው ጥቅምና ፍላጎት አንጻር ሲመዘን እንደ ሬት የሚመራቸው እና ሊወስዱት የሚተናነቃቸው ኃይሎች ከውስጥም ከውጭም የመኖራቸው ጉዳይ በዚህ ዘመን ከፍ ብሎ መታየት ጀምሯል፡፡

ስለ አንድ አገር ከዚያች አገር ሕዝቦች በላይ እናውቃለን የሚሉት እነዚህ የውጭና የውስጥ ኃይሎች፤ የሕዝቦች ንግግር፣ ጥረት፣ ዋጋ መክፈልና ሌላውም ጉዟቸው ከአገር ባለቤቶቹ ሕዝቦች ጥቅም ባሻገር፤ ስለ ራሳቸው አገርና ቡድን ጥቅምና ፍላጎት አንጻር ብቻ እየተመዘነ እውቅና የሚቸሩ ናቸው፡፡ በዚህም ብዙ ሕዝቦችን ዋጋ አስከፍለዋል፤ የፈረሰች አገር ባለቤትም አድርገዋል፡፡ ለዚህም አንዳንድ የምዕራቡ ዓለም አገራት፣ ሚዲያዎቻቸው እና በሰብዓዊም ሆነ ዴሞክራሲ ድርጅትነት ስም ያቋቋሟቸው ተቋሞቻቸው የተመጋገበና የተናበበ ስራን በመከወን የሚያስተጋቡት የፈጠራ ድርሰት ላይ የተመሰረተ ድራማ አብይ ማሳያ ነው፡፡

ይሄን በተጠና መልኩ የሚተውኑት የልቦለድ ድርሰት ታዲያ፣ እንደ ሊቢያ፣ ሶሪያ፣ የመን፣ አፍጋኒስታን፣... የመሳሰሉ አገራትን ወደ ፍርስራሽነት የቀየረ፤ ሕዝቦቹንም ለከፋ ስቃይና እልቂት የዳረገ ሆኗል፡፡ የዚህ እኩይ ድርጊት ባለቤት የሆኑት አገራት፣ ሚዲያዎቻቸውና ተቋማት ታዲያ፤ ዛሬም ድረስ እንደ ፍላጎትና መሻታቸው ታግለው ሊጥሏት ያልቻሏት ኢትዮጵያ የምትባል አገር መኖሯ አልተዋጠላቸውም፡፡ እናም ኢትዮጵያን የማዳከም፣ ሕዝቦቿን የማንበርከክ አቅም ይሰጠናል ያሉትን መንገድ ሁሉ ተከትለው መስራት፤ ከውስጥም ከውጭም ካሉ ኢትዮጵያን ጠል እና የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር ተቀናጅተው ለማዳከም በጦርም፣ በዲፕሎማሲም፣ የኢኮኖሚም፣ በሚዲያና ኮሙኒኬሽን ፕሮፖጋንዳም፣ በማዕቀብና ሌላም መንገድ የሚችሉትን ሁሉ ለማድረግ እየጣሩ ይገኛሉ፡፡

ለዚህ እኩይ ዓላማቸው መሳካት እንደ ትልቅ መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግላቸው ፈጥረው ያሳደጉትና እስከ ሽበት እድሜው የሚንከባከቡት ደግሞ አሸባሪው ትህነግን ነው፡፡ ይህ ቡድን በሕዝብ ስም ጫካ እንዲገባ ሲያደርጉትም ሆነ ለመንግሥትነት ሲያበቁት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስበው አልነበረም፡፡ ይልቁንም ሕዝብን እንደ መያዣ ተጠቅሞ በትግራይ ሕዝብ ጫንቃና መስዋዕትነት የእነሱ ጥቅምና ፍላጎት እንዲያሳካ እንጂ፡፡ ለዚህም ነው የትግራይ ሕዝብ ትናንትም ሆነ ዛሬ ከጦርነት እና ልጆቹን የጥይት ራት ከማድረግ ለአፍታም እንዳያርፍ አድርገውት ያሉት፡፡

እነዚህ ኃይሎች መሳሪያ ጭነው ለሽብር ቡድኑ ይልካሉ፤ ቡድኑም የድሃውን ልጅ ከጉያው እየነጠቀ አስታጥቆ ወደ በረሃ ነድቶ ለእሳት ይዳርገዋል፡፡ የትግራይ ሕዝብ ተራበ ሰብዓዊ ድጋፍ ያሻዋል እናም ድጋፍ ይግባ ብሎ ይጮኽና ሰብዓዊ ድጋፉ ይላካል። ነገር ግን ሕዝቡ በርሃብ እየተሰቃየ የሕጻናት የነፍስ አድን ምግቡ ሳይቀር ለታጣቂ ቡድኑ ይከፋፈላል፤ የተቀረውም በመጋዘን ተከዝኖ ይከማቻል፡፡ ይሄን የሽብር ቡድኑን ገመና ለመሸፈን ሲሉ ደግሞ እነ ቢቢሲን ዓይነት ሚዲያዎች በትግራይ ረሃብ ተከስቷል የሚል ዶክመንተሪ እየሰሩ ሃጥያቱን ለፌዴራሉ መንግሥት ለመስጠት እና ሌላ እጅ መጠምዘዣ ስልት እንዲነደፍ ለጌቶቻቸው ሲያሳስቡ ይታያሉ፡፡

ይሄን መሰል የውጭና የውስጥ ጠላቶች ትብብርና ትስስር ያልበገረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ አገሩን ከብተና ለመታደግ፤ የራሱንም ሕልውና ለማስጠበቅ እና የጠላቶች መጠቀሚያ እንዲሆን በአፈና የተያዘውን የትግራይን ሕዝብ ከእስራቱ ነጻ ለማውጣት በሁሉም ዘርፍ ድጋፍ እያደረገና ዋጋ እየከፈለ ይገኛል፡፡ መንግሥትም የሀገር ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ጥቃትን እየተከላከለ ለሰላም አማራጮች ደግሞ ሁሌም በሩን ክፍት አድርጓል፡፡ ይሄ የሕዝብና የመንግሥት ጥምረት ለእኩይ ፍላጎታቸው ግብ መምታት እንደ ቋጥኝ ከብዶ አላንቀሳቅስ ያላቸው እነዚህ ኃይሎች ደግሞ በኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ላይ ዘርፈ ብዙ ዘመቻቸውን ቀጥለዋል፡፡

ዲፕሎማሲያዊ ጫና፣ የኢኮኖሚ አሻጥር፣ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ፕሮፖጋንዳና ሌሎችም ዘመቻዎችን ለማቀጣጠል ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት እስከ አውሮፓ ህብረት፤ ከዓለም ጤና ድርጅት ኃላፊ እስከ ተቀጣሪ አክቲቪስቶች፤ ከአንዳንድ ምዕራባዊ ሚዲያዎች እስከ ተቋማት ቃል አቀባዮች የውሸቱን ድርሰት ቃለ ተውኔትን እየተቀባበሉ ናቸው፡፡ ታላቁን ተቋም የመከላከያ ሠራዊትን ስም ለማጠልሸት እንጥፍጣፊ እውነት ቀርቶ ለማስመሰል የሚያስችል ነገር ሳይኖራቸው እየማሰኑም ነው፡፡ በዚህም ኢትዮጵያን፣ ኢትዮጵያውያንንና መንግሥታቸውን ለማንበርከክ ያስችለናል ያሉትን ሁሉ በተጠናከረ መንገድ ማራመድ ሥራቸው ሆኗል፡፡

ይሄን የተገነዘቡ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆችም ከአገር ውስጥ እስከ ዓለምአቀፍ አደባባዮች "እጃችሁን ከኢትዮጵያ ላይ አንሱ" ወይም "ኖ ሞር" እያሉ ይገኛሉ፡፡ ስለ ኢትዮጵያ መናገር የሚያስችል የመብትም፣ የሞራልም ልዕልና ያላቸው ናቸውና መልዕክታቸው በሚገባ ሊደመጥ ይገባል፡፡ እንዲደመጥላቸው የሚሹትም እውነት ነው፡፡ ንግግራቸውም ጥረትና ዋጋ መክፈላቸውም ለራሳቸው ልዕልና፤ ለአገራቸው ሕልውና ነው፡፡ ድምጻቸው የጠላቶቻቸውን የጥፋት ጉዞ ማስቆምን ታላሚ ያደረገ ነው፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያ ላይ ፍላጎታቸውን ለመጫንና በውስጥ ጉዳይዋ ታልቃ ለመግባት የሚሰሩ አገራት፣ ተቋማት እና ሚዲያዎቻቸው ይሄን የኢትዮጵያውያን ድምጽ ቆም ብለው ሊያደምጡና ካልተገባ ጫናና ይሄን ለማሳካት ከሚያደርጉት እኩይ ጉዞ ሊታቀቡ ይገባል፡፡ በኢትዮጵያ ጉዳይም የራሳቸውን ፍላጎትና ጥቅም ሳይሆን፤ የኢትዮጵያንና የሕዝቦቿን ባለቤቶች ድምጽ ማዳመጥ ይገባል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

## አይናችን ሰራዊታችን ላይ

**አቤል ገ/ኪዳን**

ሰሞኑን በማህበራዊ ሚዲያ አንድ ቪዲዮ ሲዘዋወር አየሁና ልቤ ክፉኛ አዘነ። ቪዲዮው በሶስተኛው ዙር ጦርነት ወቅት በአሸባሪው ሕወሓት የተማረኩ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላት ሲንገላቱ የሚያሳይ ሲሆን የተገኘውም ከተማረከ የሕወሓት ወታደር ስልክ ላይ ነበር። ቪዲዮው ላይ እነዚህ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላት በሰደፍ ሲደበደቡ፤ በድንጋይ ሲወገሩ፤ ጫማቸውን አስወልቀው በባዶ እግር ሲያስኬዷቸው፤ ሲሰድቧቸው፤ ሲረግሟቸው ያሳያል።

በቪዲዮው ላይ የሚታየው ሁለት ነገር ነው። አንደኛ የአሸባሪው ሕወሓት ወታደሮች በመከላከያ ሰራዊቱ ላይ ብሎም በኢትዮጵያ ላይ ያላቸው ጥላቻ ጽናት ይታያል። ይህ አስገራሚም ሆነ አዲስ ባይሆንም ነገር ግን በዚህ ቪዲዮ ላይ በማይደበቅ መልኩ ጎልቶ ይታያል።

የጥቅምት 24ቱ የጥላቻ ጥቃት በዚህ ቪዲዮ ላይ ተደግሞ ይታያል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ያኔ በዚያ እለት በጥቃቱ ሰለባ የሆኑት ወታደሮች የደረሰባቸው ነገር ሲናገሩ ለማመን የሚከብድ ይመስል ነበር። ይህ ቪዲዮ ግን በእርግጥም የቡድኑ ሰዎች የተባለውን በደል ሁሉ የመፈጸም አቅም እንዳላቸው በግልጽ የሚያሳይ ነው።

ሌላኛው በዚህ ቪዲዮ የሚታየው የሰራዊቱን የመስዋእትነት ከፍታ ነው። ሰራዊቱ አጥንቱን ከስክሶ፤ ስጋውን ቆርሶ፤ ደሙን አፍስሶ አገራችንን ጠብቆልናል የሚለው ንግግር ከመደጋገሙ የተነሳ ዘልማዳዊ አባባል ቢመስልም በዚህ ቪዲዮ ግን በተግባር ታይቷል። በዚህ ቪዲዮ ላይ እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ወታደር ሲደበደብ እና ሲሰደብ የሚታየው ኢትዮጵያዊ ወታደር ስለሆነ እና አገራዊ ግዴታውን ስለፈጸመ ብቻ እንደሆነ በግልጽ ይታያል።

የሚሆንባቸው ነገር በሙሉ የሚሆነው ለግል ጉዳያቸው አይደለም። ለአገር ነው። የዛሬ ጽሁፋችን ማጠንጠኛም የታወቀውን የአሸባሪ ሕወሓት ለኢትዮጵያውያን ያለ ጥላቻ መዘከር ሳይሆን ለዚህ ሰራዊት የምንሰጠው እውቅና እና ክብር ያለ ቅደመ ሁኔታ መሆን እንዳለበት፤ ብሎም በቀጣይ ሰራዊቱ በትግራይ ክልል በሚያካሂዳቸው ዘመቻዎች በሙሉ አብረነው ልንቆም እንደሚገባ በድጋሚ ለማስታወስ ነው።

ዛሬ ላይ በወልቃይት በሚሊየን የሚቆጠር ሰው ተሰልፎ ምርት ሊሰበስብ ማሳ ላይ ውሏል። ባህር ዳር የጣና ፎረምን አዘጋጅታ የቀጠናው መሪዎችን አስተናግዳለች። ጎንደር የመንግስት የካቢኔ አባላት ግምገማን አካሂዳለች። ደሴ ወደ ቀድሞ ቅኝቷ ተመልሳለች። ደብረ ብርሀን የኢንዱስትሪ ከተማነቷን የሚያጠናክር ድግስ እያሰናዳች ነው። አዲስ አበባ አሁንም ሰላማዊ ኑሮዋን እየገፋች ነው። ይህ ሁሉ የሆነው ግን እንዲሁ በመላ አይደለም። ከላይ የጠቀስነውን መስዋእትነት የሚከፍሉ ጀግኖች ስላሉ ነው።

እኛ አንድ ቀን መንፈሳዊ ጉዞ ወይም ሀይኪንግ ተጉዘን በእግር የሁለት ሰዓት መንገድ ብንጓዝ በማግስቱ ስራ አንገባም። ወገቤን፤ እግሬን፤ ጀርባዬን አመመኝ እንላለን። ለኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ግን ይህ የእለት ተእለት ኑሮው ነው። እንደሚታወቀው ሰሜኑ የአገራችን ክፍል ተራራ ይበዛዋል። ሊያውም ረዣዥም እና ሰንሰለታማ።

ወታደር ደግሞ እንደ ሲቪል አስፋልት ተከትሎ አይሄድምና እነዚህን ተራሮች መሳሪያ ተሸክሞ መውጣት አለበት። ሊያውም ዝም ብሎ መውጣት አይደለም እየተዋጋ ከሰውም ከተፈጥሮም እየታገለ። ይህን የሚያደርገው ለግል ጉዳዩ አይደለም ለእኛው ነው...።

አንዳንዶቻችን የተለመደ የአመጋገብ ሂደት አለን። ምን ብንበላ እንጀራ ካልበላን እህል የበላን አይመስለንም። ሊያውም አይነቱን መርጠን። ወጡንም እንደዛው። ቁርጥ እና ቅቅል ካልበላ እህል የበላ የማይመስለውም አለ። በቀን አራቴ ካልበላ የከሳ የሚመስለውም ብዙ ነው።

ሰራዊቱ ግን ለቀናት ያለ ምግብ እና ያለ ውሀ ነፍስ ለማቆየት ያህል እየቀመሰ ነው የሚቆየው። ሱባኤ ይዞ አይደለም። ክብደት የመቀነስ ልምምድ ላይም ሆኖ አይደለም። ሌላው በልቶ እንዲያድር መስዋእትነት መክፈል ያለበት ኃይል ስለሚያስፈልግ ነው። ይህን የሚያደርገው ለግል ጉዳዩ አይደለም፤ ለእኛው ነው....።

ብዙዎቻችን ልብስ የምንለብሰው ለጥቂት ቀናት ነው። በቀን በቀን ልብስ የሚቀይርም አለ። ማታ ቤታችን ስንገባ ከሚያስደስቱን ነገሮች አንዱ ቀን አድርገነው የዋልነውን ጫማ ማውለቅ ነው። ይሄ ጫማ አልተመቸኝም፤ ያቃጥላል። ይሄ ልብስ አልተመቸኝም እንዲህ ወይም እንዲያ ሆኗል እንላለን።

የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ለወራት ዩኒፎርም ሳያወልቅ ጫማውን በእግሩ እንዳለ ምሽግ ውስጥ ተቀምጦ አገር ይጠብቃል። ይህን የሚያደርገው እንደኛ የጤናው ጉዳይ ስለማያሳስበው ወይም ዘንጦ መታየት ስለሚጠላ አይደለም። ይህ የሚሆነው ሌሎች አምረው እንዲታዩ የተወሰነ ኃይል እየተጎሳቆለም ቢሆን መጠበቅ ስላለበት ነው። ይህም ለእኛው የተደረገ ነው..።

እንዲህ እንዲህ እያልን ብዙ ልንጽፍ እንችላለን። ዋናው ፍሬ ጉዳይ ግን ሰራዊቱ አሁንም በእያንዳንዱ ቀን እየከፈለ ያለው መስዋእትነት መረሳት የለበትም ነው። በተለይም በዚህ ወቅት ከምንጊዜውም በላይ ሰራዊቱን ማስታወስ እና ያለቅድመ ሁኔታ መደገፍ ግዴታ ነው። ሁላችንም አይናችንን በሰራዊቱ ላይ ልናደርግ ይገባል። ሁላችንም ከያለንበት ሆነን ለሰራዊቱ ማንኛውንም አይነት ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆን አለብን።

ሕወሓት ሰሞኑን ሞቱ መቃረቡን ሲያውቅ የመሞቻውን ቀን ለማስረዘም ሌት ተቀን እየተጋ ነው። እነ ቴዎድሮስ አድሀኖም ጄኖሳይድ ሊፈጸምብን ነው እያሉ እየተፈራገጡ ነው። ለአይቀሬው ሽንፈት ሽፋን እያዘጋጁ ደግሞም ከተሳካ ዓለም ተረባርቦ ሽንፈታቸውን እንዲያስቀርላቸው እየሰሩ ነው። በዚህ ሁንታ መሀል ግን ያለመዘናጋት አይኖቻችን ሰራዊቱ ላይ ሊሆኑ ይገባል።

ሰራዊቱ እንደሚያሸንፍ እርግጥ ነው። ነገር ግን ድሉ ድላችን እንዲሆን በእያንዳንዱ የትግራይ ከተማም ሆነ የገጠር ቀበሌ ለሚኖረው ነጻ የማውጣት ዘመቻ ልንደግፈው አብረነው ልንቆም ብቻውን እንዳልሆነም ልናሳይ ይገባል። ከሁሉም በላይ ደግሞ የትግራይ ህዝብ ነጻ ሊያወጣው ብዙ ዋጋ እየከፈለ ላለው የመከላከያ ሰራዊቱ ያለውን አጋርነት በተጨባጭ ማሳየት ይጠበቅበታል።

# ስኬት

# ዓለም አቀፍ ድርጅት ለመሆን እየተጋ ያለው ዳዬ በንሳ ቡና ላኪ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ሆኖ የኖረው የግብርናው ዘርፍ አሁንም ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑ ቀጥሏል። ከአገሪቱ ህዝብ አብዛኛው የሚተዳደረው በግብርና ስራ መሆኑ እንዳለ ሆኖ የአገሪቱን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እየተደረገ ባለው ጥረት ዘርፉ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

ዘርፉ የአገር ውስጥ የግብርና ምርቶች ፍላጎትን በማሟላት ከፍተኛ ሚና ከመጫወት በተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ መሆኑን ቀጥሏል። በተጠናቀቀው 2014 በጀት ዓመት አገሪቱ ለውጭ ገበያ በማቅረብ ካገኘችው የውጭ ምንዛሬ ከፍተኛ መጠን ያለው ገቢ ያስገኘው ይሄው የግብርናው ዘርፍ ነው።

ለውጭ ገበያ ከተላኩ የግብርና ምርቶች መካከልም ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት እየታወቀ ያለው ቡና ነው። ቡና ባለፉት ዓመታት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ጉልህ ስፍራ ይዞ የቆየ ሲሆን፣ ባለፈው በጀት ዓመት ከቡና የወጪ ንግድ ከአንድ ነጥብ አራት ቢሊየን ዶላር በላይ ተገኝቷል። ይህም በቡና የወጪ ንግድ ታሪክ የመጀመሪያው ስኬት ለመባል በቅቷል።

በቡናው ዘርፍ እየተመዘገበ ላለው ውጤት መንግስት፣ በዘርፉ የተሰማሩ አርሶ አደሮች፣ አቅራቢዎች፣ ቡናውን አዘጋጅተው ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ላኪዎች ጉልህ ድርሻ አላቸው። በተለይ የኢትዮጵያ ቡና በመጠንና በጥራት ተወዳዳሪ መሆን እንዲችል ብሎም በዓለም ገበያ ከፍ ያለ ዋጋ እንዲያወጣ እየተከናወነ ባለው ተግባር፤ ከአርሶ አደሩ ጋር በመሆን ሌት ተቀን ከሚተጉ በርካታ አካላት መካከል ዳዬ በንሳ ቡና ላኪ ድርጅት አንዱ ነው።

ድርጅቱ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ በቡና ንግድ ላይ ቆይቷል፤ ካለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ወዲህ ደግሞ የቡና የንግድ ስራው በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ መጥቷል። በአሁኑ ወቅትም በቡና ልማትና ግብይት እንዲሁም እሴት በመጨመር ዘርፉን ለማሳደግ የረጅምና የአጭር ጊዜ ራዕይ ሰንቆ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል።

ቡናን በብዛትና በጥራት አዘጋጅቶ ወደ ውጭ ገበያ በመላክ ቀዳሚ ከሆኑት ተርታ በመሰለፍ ተሸላሚ የሆነው ዳዬ በንሳ ቡና ላኪ ድርጅት፣ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ቡና በብዛት አምርቶ ወደ ውጭ ገበያ በመላክ እና በጥራት ተሸላሚ መሆን ችሏል። በአገሪቱ በቅርቡ በተጀመረው የካፕ ኦፍ ኤክሰለንስ ወድድር ባለፉት ሁለት ዓመታት ቶፕ ቴን ውስጥ ገብቶ የነበረው የዳዬ በንሳ ቡና ድርጅት፤ በ2014 ዓ.ም ለሶስተኛ ጊዜ በተደረገው ውድድር ሁለተኛ ደረጃ በመያዝ ተሸላሚ ሆኗል።

የድርጅቱ መሥራችና ባለቤት አቶ አሰፋ ዱካም ከሃያ ዓመታት በፊት ወደ ቡና ልማትና ለወጪ ገበያ መላክ ንግድ ከመግባታቸው በፊት ጫማ በማሳመር /የሊስትሮ ሥራ/ ተሰማርተው ሰርተዋል፤ በዱቄትና ሌሎች የንግድ ሥራዎችም ተሰማርተው ሰርተዋል። ከተሰማሩባቸው የንግድ ሥራዎች የቡና ንግድ አዋጭ ሆኖላቸው ቡናን ከማምረት ጀምሮ ለውጭ ገበያ እስከ ማቅረብ ደርሰዋል። አቶ አሰፋ ወንድማቸውን አቶ ሙሉጌታ ዱካሞን እና ሁለተኛ ትውልድ የሆነው ልጃቸው ወጣት ከንአን አሰፋን ወደ ዘርፉ እንዲቀላቀሉ በማድረግ ሥራቸውን ውጤታማ ማድረግ ችለዋል።

በለጋ ዕድሜው የቡና ንግድን የተቀላቀለውና ሁለተኛ ትውልድ የሆነው ከንአን አሰፋም ድርጅቱ እያስመዘገበ ላለው ውጤት የጎላ ድርሻ እያበረከተ እንደሆነ አጫውቶናል። ማንኛውም ሥራ በዕውቀት ሲመራ አመርቂ ውጤት ማምጣት እንደሚችል የሚያምነው ከንአን፤ በዕውቀት ተመስርቶና ቴክኖሎጂን በመጠቀም የምርት፣ የጥራት፣ የኤክስፖርትና አጠቃላይ የውጭ ገበያውን ዘርፍ በመምራት የድርሻውን እየተወጣ ይገኛል። ወላጅ አባቱ አቶ አሰፋ ዱካሞና ወንድማቸው አቶ ሙሉጌታ ዱካሞ ደግሞ ቡና በማምረት ስራ ተሰማርተዋል።




ቡናን አምርቶ ከመሸጥ ባለፈ ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጠቀሜታ በመረዳት ሰፊ ሥራ መሥራት እንደሚቻል የሚናገረው ከንአን፣ በቡናው ዘርፍ እሳተፋለሁ የሚል ሃሳብ አልነበረውም፤ ወላጅ አባቱ በቡና ልማትና ግብይት ውስጥ የነበራቸውን ትጋትና ለውጥ ሲመለከት ግን ዘርፉን ለመቀላቀል አላመነታም። በተለይም የኮምፒዩተር ሳይንስ ትምህርቱን ለመከታተል አሜሪካ በሄደበት አጋጣሚ የኢትዮጵያ ቡና ያለውን ተቀባይነትና ዋጋ ይረዳል። በመሆኑም በውጭው ዓለም የቤተሰቡን የቡና ድርጅት ቡና በመሸጥ ድርጅቱን ሲያግዝ ቆይቷል።

ትምህርቱን አጠናቅቆ ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላም ድርጅቱን በሙሉ ጊዜው በማገልገል ውጤታማ እንዲሆን ሲሰራ ቆይቷል። የገበያ ልማቱን በቴክኖሎጂ በማዘመን፤ አዳዲስና ቀልጣፋ አሰራሮችን በመዘርጋትና ወጣቶችን አሰልጥኖ ወደ ሥራ በማምጣት ለውጥ ማስመዝገብ ጀመረ። ይህ ጥረቱም ድርጅቱ ካለፉት ሶስት ዓመታት ወዲህ በአራትና አምስት እጥፍ እንዲያድግ ምክንያት መሆኑን ይናገራል። የዛሬ ሶስት ዓመት ድርጅቱ ለውጭ ገበያ ከሚያቀርበው ቡና በዓመት ስምንት ሚሊዮን ዶላር ገቢ ያገኝ ነበር። በአሁኑ ወቅት ድርጅቱ በዓመት 37 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት ችሏል።

ድርጅቱ በሲዳማ ክልልና በከፋ አካባቢ ባለው የቡና እርሻ ቡና ያለማል፤ በሲዳማ ክልል ከሚገኙ በርካታ ገበሬዎችም ከፍተኛ መጠን ያለው የቡና ምርት ይሰበሰባል። ከ45 እስከ 50 ሺ ከሚደርሱ የአካባቢው ገበሬዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ቡና የሚሰበሰብ ይሆናል።

በሲዳማ ክልል በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎችም 71 የሚደርሱ የቡና መፈልፈያ ጣቢያዎች ያሉት ሲሆን፣ በእነዚህ ጣቢያዎችም ቡናው ተሰብስቦ፣ ተፈልፍሎና ደርቆ ወደ አዲስ አበባ ይላካል። አዲስ አበባ የደረሰው ቡናም አስፈላጊው ዝግጅት ተደርጎለት ለውጭ ገበያ የሚላክ ይሆናል።

ከድርጅቱ ጋር ትስስር ፈጥረው ያመረቱትን ቡና ለድርጅቱ እያቀረቡ ከሚገኙ 50 ሺ ገበሬዎች በተጨማሪ 2500 የሚደርሱ ገበሬዎች ደግሞ የድርጅቱ አባላት ሆነው ቡና አምርተው እንደሚያቀርቡ ያጫወተን ከንአን፤ እነዚህን አርሶ አደሮች ድርጅቱ እያንዳንዳቸውን በስም ከማወቅ ባለፈ ምን ያህል ቡና እንደሚያመርቱ ጭምር እንደሚያውቅና ጥብቅ ግንኙነት እንዳለውም ያብራራል። ድርጅቱ ከእነዚህ አርሶ አደሮች ቡና የሚገዛው ከገበያው ዋጋ ከፍ ባለ እንደሆነም አጫውቶናል። ድርጅቱ የእነዚህ አርሶ አደሮች በቡና ልማቱ ምርታማ እንዲሆኑ ችግኝ በመስጠት፣ የግብርና ባለሙያዎችን በመመደብ ሙያዊ ድጋፍ እንዲያገኙ ያደርጋል።

ድርጅቱ ቡና አምርቶ ወደ ውጭ ገበያ ከመላክ ባለፈ ዘርፉን ለማጎልበት የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑንም ወጣት ከንአን ይጠቁማል፤ በዓለም ዙሪያ ያሉ ቡና ገዢዎች በየጊዜው የተለያየ አይነት አመራረት እንደሚፈልጉ ጠቅሶ፣ ይህን ታሳቢ ያደረገ ከጊዜው ጋር



ሊሄድ የሚችል ሥራ በመሥራት የደንበኞችን ፍላጎት ማርካት የግድ ነው ይላል። ለዚህም ከዛሬ ሶስት ዓመት ጀምሮ ድርጅቱ በየዓመቱ 10 ልጆችን በማሰልጠን የተሻለ ውጤት ያመጡትን እየቀጠራቸው መሆኑን ይገልጻል። በዚህ በጀት አመት ደግሞ 20 ወጣቶችን ለማሰልጠን አቅዷል፤ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ደግሞ 100 ለሚደርሱ ወጣቶች ስልጠናውን በመስጠት ቡና በዕውቀት እንዲመረትና ለውጭ ገበያ እንዲዘጋጅ እንደሚሰራም አስረድቷል።

ቡና በማምረትና በኤክስፖርት ሥራ የተሰማራው ዳዬ በንሳ ቡና ላኪ ድርጅት፣ በኤክስፖርት ሂደት ውስጥ 110 ለሚደርሱ፣ እንዲሁም በማምረት ሂደት ውስጥ ለ250 በድምሩ ለ360 ሠራተኞች ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለ ነው። ቡና በሚደርስበት ጊዜ ደግሞ 150 የሚደርሱ ጊዜያዊ ሠራተኞችን ወደ ሥራ ያስገባል። እነዚህ ሠራተኞችም በሲዳማ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በሚገኙ 71 የቡና መፈልፈያ ጣቢያዎች ቡና ተዘጋጅቶ ወደ አዲስ አበባ እንዲጓጓዝ የሚያደርጉ ናቸው። ተጓጉዞ አዲስ አበባ የደረሰው ቡናም ተበጥሮ፣ ተለቅሞና ታሽጎ ለውጭ ገበያ የሚላክ ይሆናል።

በሲዳማ ክልል ሰፋፊ የቡና እርሻዎች አለመኖራቸውን የጠቀሰው ከንአን፤ በትናንሽና በተበጣጠሰ የአርሶ አደር መሬት ቡና እንደሚለማ ይናገራል፤ በዚህ ሂደት ውስጥ እየሰራ ድርጅቱ በየጊዜው የሚያመርተውን የቡና መጠንና ጥራት በማሻሻል ተሸላሚ መሆን እንደቻለ ይናገራል። ባለፉት ዓመታት በዓመት ከስድስት ሺ አምስት መቶ እስከ ሰባት ሺ ቶን ቡና ወደ ውጭ ገበያ ይልክ እንደነበር በማስታወስ፤ በ2015 ዓ.ም 50 ሚሊዮን ኪሎ ግራም እሸት ቡና ለመሰብሰብ እንዲሁም 10 ሺ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ ለመላክ አቅዶ እየሰራ መሆኑን አጫውቶናል።

የድርጅቱ የገበያ መዳረሻ አሜሪካ፣ ጀርመንና ኮሪያን ጨምሮ 25 የሚደርሱ የዓለም አገራት መሆናቸውን የተጠቀሰ ሲሆን፣ በቀጣይም ምርትና ምርታማነቱን በማሳደግና ጥራት በመጨመር የገበያ መዳረሻቸውን ለማስፋት አቅዷል። ዓለም ላይ ትላልቅ ስም ካላቸው እንደ ስታር ባክስና ንስሌም ከሚባሉ ድርጅቶች ጋር በቀጥታ የገበያ ትስስር መፍጠርም ችሏል። ገበያውን በማስፋት የኢትዮጵያን ቡና ለዓለም ገበያ በማቅረብ ከሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ገቢ በበለጠ አገርን በማስተዋወቅ ረገድ ቡና የጎላ ድርሻ እንዳለውም ከንአን ይናገራል።

‹‹ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ሆና ቡና በተፈጥሮ የተሰጣት ስጦታ ቢሆንም፣ በሚገባን ልክ ግን አልተጠቀምንበትም›› የሚለው ከንአን፣ ቡና በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ የመቶ ቢሊዮን ዶላር ኢንዱስትሪ እንደሆነና በቀጣይ ጥቂት ዓመታትም እስከ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ሊደርስ የሚችል ኢንዱስትሪ እንደሆነ መረጃዎችን ጠቅሶ ያስረዳል። ከዚህ ውስጥ የቡና ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ያላት ድርሻ አንድ በመቶ ያህል እንደሆነም ጠቅሶ፣ የኢኮኖሚ ድርሻዋም በዛው ልክ እጅግ ዝቅተኛ መሆኑን በቁጭት አስረድቷል።

ለቡና ሥራ ቅርብ ከሆነ ቤተሰብ የተገኘው ከንአን፤ በተለይም በውጭ አገር ቆይታው ለቡና ያለውን እውቀት በማስፋት ዓለም ምን እንደሚፈልግ መረዳት ችሏል። በመሆኑም ኢትዮጵያ ቡና አብቃይ አገር እንደመሆኗ በዘርፉ ብዙ ልትጠቀምበት እንደሚገባ በማመን አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን በተለይም ዘርፉን በእውቀት መምራት ላይ አበክሮ እየሠራ ይገኛል። ለዚህም ድርጅቱ በቀጣይ ትምህርት ቤት በመክፈት ስለ ቡና የማስተማር ዕቅድ እንዳለው አስረድቷል። በዚህም ቀጣዩ ትውልድ ቡናን አምርቶ ከመላክ ባለፈ በቡና ዙሪያ ያለውን ዕውቀት በመሸጥ ጭምር ገቢ ማግኘት እንደሚችል ነው ያመለከተው።

ቡና ከእርሻ ጀምሮ እስከ ካፌ ድረስ ያለውን ሂደት ለማስፋት ትምህርትና ስልጠና ለመስጠትና ዘርፉን በእውቀት ለመምራት የተዘጋጀው ዳዬ በንሳ ቡና ላኪ ድርጅት፣ በአሁኑ ወቅት እሴት በመጨመር ቡና ቆልቶ ለአገር ውስጥ ገበያ እያቀረበም ይገኛል። በቀጣይም ዘርፉን በማስፋት ለውጭ ገበያ የማቅረብና በአገር ውስጥም ካፌ የመክፈትና በውጭው ዓለም የሚቀርበውን አይነት የካፌ ቡና የማቅረብ ዕቅድ ይዞ እየሠራ ነው። በቅርቡም ሀዋሳ ላይ የመጀመሪያውንና ደረጃውን የጠበቀ ካፌ ለመክፈት ዝግጅቱን አጠናቅቋል።

ድርጅቱ ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድ የሲዳማ ክልል በንሳና አርቤጎናን ጨምሮ በአራት ወረዳዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ትምህርት ቤቶችን ገንብቶ እያጠናቀቀ ነው። የትምህርት ቤቶቹንም ግንባታ በዚህ ዓመት በማጠናቀቅ ለመንግሥት እንደሚያስረክብም ከንአን ይጠቁማል። ድርጅቱ የመንገድ፣ የውሃና ሌሎች መሰረተ ልማቶችን በመገንባት ለማህበረሰቡ እያበረከተ መሆኑን ተናግሯል። በቀጣይም ዘላቂነት ባለው መንገድ አርሶ አደሩን በማገዝ፣ በማበረታታትና አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ምርትና ምርታማነት በማሳደግ ራሱን እንዲለውጥ ለማድረግ ይሠራል ብሏል።

በቂ የሆነ የገበያ ተደራሽነት ያለው ዳዬ በንሳ ቡና ላኪ ድርጅት፤ በረጅም ጊዜ ዕቅዱ ከኢትዮጵያ ቡና በተጨማሪ በሌሎች አገራትም ቡናን አምርቶ ለገበያ በማቅረብ ዓለም አቀፍ ድርጅት የመሆን ራእይ አለው። ይህን ሃሳቡን እውን ለማድረግም ድርጅቱ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን የጠቀሰው ከንአን፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዓለም አቀፍ በመሆን የአፍሪካ ኩራት እንደሆነ ሁሉ በቡናው ዘርፍ ደግሞ ዳዬ በንሳ ቡና ላኪ ድርጅት ዓለም አቀፍ ድርጅት በመሆን ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን እየተጋ እንደሆነም አጫውቶናል።

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ^አስተውሳችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# በእሾህ የተከበበችው አበባ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

አንዳንዴ ሰው ሆና መፈጠሯን እስትረግም ራሷን ትጠላለች። ያሳለፈችውን መከራ መለስ ብላ ስትቃኝ ሆድ ይብሳታል ። እሷ የልጅነቷን ደስታና ፈገግታ አታስታውስም። ብሶት ለቅሶና መከራ ደጋግመው ፈትነዋታል። ያለፈችበት መንገድ እሾህማ ነው። በየደረሰችበት እየወጋ አድምቷታል። አንዳንዴ ደግሞ ልክ እንደ ሳማ ነበር። አብዝቶ የሚያቃጥል፣ በቶሎ የማይተው ስቃይ አለው።

ከህይወቷ ስንክሳሮች ሁሉን ላስታውስ ካለች ዕንባዋ በዋዛ አይቆምም። ያለፈው ታሪኳ ተመላልሶ ይረብሻታል። ዛሬም ድረስ ያላለፈው ችግሯ ከኋላ እየተከተለ ያስጨንቃታል። ሁሌም አንገቷን ደፍታ በሀሳብ ትቆዝማለች። አሁን ደግሞ ገና በማለዳ ዕንቅልፍ እየነሳ ሆድ የሚያስብሳትን አላጣችም።

እንደልማዷ ውስጧን ካዳመጠች እንደሁሌው ይከፋታል፣ ዝም እንዳትል አትችልም፣ ውሰጧ የሚላትን እታደርግ ነገር እጅ አጥሯታል። ወፍ ሳይንጫጫ ከራሷ ትግል የምትገጥመው ሴት በውስጧ ለሚገላበጠው የርሀብ ጥያቄ ፈጽሞ መልስ የላትም። በሆዷ ነፍስ ዘርቶ በየአፍታው ለሚረግጣት ፍጡር የፍላጎቱን አትሞላም። ዕንባዋን ውጣ ርሀቧን ለማስታገስ ያላት ምርጫ አንድ ብቻ ነው። እጆቿን ለልመና መዘርጋት።

የዕለት ርሀቧን ለማስታገስ የምግብ ትርፍራፊ አታጣም። አንዳንዴ ደርሶ ውል ለሚላት አምሮት ግን መፍትሄ የላትም። ነፍሰጡር ናትና የማያምራት፣ የማይሸታት የለም። አንዳንዴ ልታገኘው ቀርቶ ፈጽሞ ልታየው የማይቻላት በዓይኗ እየዞረ፣ ሽታው በአፍንጫዋ ያውዳል። ይህኔ አይኖቿ በስስት እየቃበዙ እጆቿ ያማራትን ሊያጎርሷት ይሻሉ።

በበዛ ፍላጎት የሚቃብዘው ውስጠቷ ግን ሁሌም ‹‹ሲያምርሽ ይቅር ›› ሲል ያሳቅቃታል። አዎ ! ሁሉንም ሲያምራት ከመተው ውጭ ምርጫ የላትም። ሁሌም የሆዷን በሆዷ ይዛ ለቀን ውሎዋ ትባዝናለች። አጋጣሚው ከቀናት ለርሀቧ ታክል አታጣም። አንዳንዴ ግን ከልመናዋ ጋር የምትቀበለው ስድብና መመናጨቅ ሰው መሆኗን ያስረሳታል። የአንዳንዶች ክፉ ልማድ ራሷን ጠልታ፣ ማንነቷን እንድትንቅ ጭምር ያስገድዳታል።

ለልመና እጆች በተዘረጉ ጊዜ ከበስተጀርባ የሚከተል ችግር መልከ ብዙ ነው። አንዳንዱ ሲያመናጭቅ፤ አንዳንዱ ይራገማል፣ አንዱ ፍርድ ሲሰጥ ሌላው ለዓይን ይጠላል። ደርሰው ‹‹እንምከር ›› ባዮች ሲቀርቡ ደግሞ ኩነኔያቸው በዝቶ፣ ቃላቸው አጥንት ይበሳል።

እነሱ ከራሳቸው ሀሳብ በላይ ስሌላው ስሜት አይጨነቃቸውም። እንዳመጣላቸው እየተናገሩ ብሶትን ያግማሉ፣ ቁስልን ያደማሉ። እንዲያም ሆኖ መፍትሄ የላቸውም። ሳይላቸው ነካክተው ዕንባን ሳያብሱ፣ ህመምን ሳያክሙ እብስ ይላሉ። እንዲህ አይነቶቹ ልመናን ስለምን ሲሉ ለቀጣዩ ህይወት መላ የላቸውም። ሰውዬውን ኮንነው፣ ድርጊቱን ተቃውመው ብቻ ያልፋሉ።

አንዳንዶች ሌሎችን ጎዳና ላይ ስላዩ ብቻ በጎነቱ የላቸውም። በዚህ ህይወት ያሉ ሁሉ ሌባና ዱርዬ ይመስሏቸዋል። የጎዳና ላይ ነፍሶች ከእነሱ አቻ እንዳልሆኑ እያሰቡም የአንደበታቸውን ቃል በክፉ ሀሳብ ይመነዝራሉ። ይህ አይነቱ አጋጣሚ ጠኔ እጃቸውን አዘርግቶ፣ የሰው ፊትን ላሳያቸው ብሶተኞች መኖርን ያስጠላል፣ ከከፋ ሀዘን ይጥላል።

### ቅድመ- ታሪክ

አበባ አርአያ የልጅነት ህይወቷ እንደ እኩዮቿ ሆኖ አላለፈም። ወላጆቿ ገና ጡት ሳትጥል መሞታቸውን ስትሰማ አድጋለች። ከእናት አባቷ ማለፍ በኋላ ዕጣ ፈንታዋ በዘመድ እጅ ቢወሰን ቀጣይ ህይወቷ በሰው ቤት ሆነ። በማደጎ የተቀበሏት ዘመዶቿ ነፍስ እስከታውቅ በእንክብካቤ ያዟት። ዕድሜዋ ሲጨምር ግን አልተመቻትም። በደሏ በዛ፣ ሰላሟን አጣች። ጠዋት ማታ የዘመድ ቤት ኑሮ ሆድ አስባሳት። ስታለቅስ፣ ስተክዝ መዋል ማደር ልምዷ ሆነ።

የአበባ ዘመዶች ኑሮ ከእጅ ወደአፍ የሚባል ነው። በእጅጉ ድህነት ያጠቃው ቤተሰብ ሰርቶ ማግኘትን፣ ሸምቶ መብላትን አያውቅም። ሁሉም ጠዋት ማታ የሰው እጅ አይተው፣ ለምነው ያድራሉ። የልመናው ውሎ ካልቀና ደግሞ ቀምሶም ማደር ይቸግራል።



አበባ በዘመድ ቤት ስትኖር እንደ እኩዮቿ መማር አልቻለችም። ይህን ማድረግ ብትሞክር እንኳን የአሳዳጊዎቿ አቅም ርቆ አይወስዳትም። ከሁሉም ግን ከቤቱ ልጆች አንደኛው እየደበደበ የሚያሰቃያትን ልማድ መቋቋም አልቻለችም። ልጁ ሰበብ እየፈለገ ይሰድባታል፣ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ በጭካኔ ይመታታል።

አንዳንዴ ልጅቷን ጎረቤቶች ደርሰው ያስጥሏታል። እንዲህ ካልሆነ በስቃይ የምትውለው አበባ እውነቱን የሚያውቅላት አላገኘችም። ይባስ ብሎ የልጁ ችግር በእሷ ተሳቦ ጥፋተኛ መሆኗ ይነገርባት ያዘ። እየተደበደበች ደብድባለች፣ እየተሰደበች ተሳድባለች የምትባለው ልጅ ሰሚ ጆሮን አጣች። የነገሮች እንዳይሆን መለዋወጥ ባይተዋር ያደረጋት አበባ ክፉኛ አንገቷን ደፋች።

አሁን አበባና የዘመድ ቤት ህይወት እንደቀድሞው አልሆኑም። በየምክንያቱ የሚመጣው ግጭት ለእሷ ትርጉም ይኖረው ያዘ ። በየሰበቡ የሚነሱ ችግሮችን ‹‹ይሁነኝ›› ማለት አልቻለችም። ቁዘማዋ ጨመረ። ሲቆጧት እያዘነች፣ ሲቀጧት ቂም ያዘች። የኑሮዋ አለመመቸት በኩርፊያና ቅያሜ ብቻ አልቀረም። ብዙ ያሰበው ውስጧ እግሯን ለመንገድ አነሳሳቶ ልቧን ውጭ አሳደረ።

ከቤት መውጣት ያሰበችው አበባ የዕቅዷን ልትፈጽም ዕንቅልፍ ይሉት አጣች። በኋላም ካለችበት ቤት ኑሮ ይሻለኛል ያለችውን የጎዳና ህይወት መረጠች። ከቤት ወጥታ ከጎዳና ጓደኞቿ ስታድር ማንም የፈለጋት የለም። ለጊዜው የጎዳናው ዓለም ሰላም ነጻነቷን ሰጣት። በዚህ ቦታ የሚጨቀጭቅ፣ የሚያስከፋት የለም። ይህ ሲገባት ፊቷ በደስታ በራ፣ ‹‹እፎይ›› ስትል አረፍ አለች።

### ጎዳናው - ውሎ አድሮ

አበባና የጎዳና ህይወት ከተዋወቁ ጊዜያት ተቆጥረዋል። አሁን በውስጧ የትናንቱ እፎይታ የለም። በጎዳና የከፋ ብርድና ቅዝቃዜ አለ። በጎዳና ዝናብና ጸሀይ ይፈራረቃሉ፣ በጎዳና ርሀብና ችግር ያብራሉ። ጎዳና እንደቤት አይደለም። ይህን ህይወት በብዙ ጭንቅና ስጋት፣ በበርካታ ጉስቁልናና መከራ ሊኖሩት ግድ ነው። በጎዳና የብዙ ሴት ልጆች ልብ ተሰብሯል፣ የህጻናት ህይወት ተፈትኗል። የወጣቶች ተስፋ በሱስ በመጠጡ መክኗል።

አበባ ከቤት እንደወጣች ማረፊያዋ ብሄራዊ አካባቢ ከነበረ ጎዳና ሆነ። በስፍራው ካገኘቻቸው ባልንጀሮች ብዙዎቹ ሲጋራና ጫት ይጠቀማሉ። ማስቲሽ ከቤንዚን ይስባሉ። ተጠግታ ልትመስላቸው ሞከረች። አቀራረቧ ከእነሱ አልሄድ ቢላቸው እንግድነቷን አልፈለጉም። ደርሳ ጨዋ ልምሰል ማለቷን አልወደዱትም።

እነሱ የቀረባቸውን ይመስላሉ። የመሰላቸውን ይወዳሉ። የመጀመሪያ ቀን አበባ በመሀላቸው ተገኝታ ከአንዱ ጥግ አረፍ አለች። በመምጣቷ ያልተከፉት ልጆች ከለበሱት አጋርተው፣ ከቀመሱት አጉርሰው አሳደሯት። ውሎ አድሮ ከብዘዎች ተግባባች፣ የበሉትን በልታ የሆኑትን መሆን ግድ አላት። ከሱስ ከጫቱ ዓለም ለመ ቀላቀል አልዘገየችም። የጎዳና ልጅ ከሆነች ይህን ልታደርግ ያስፈልጋል። አልያ ከመንጋው ትለያለች፣ ከሁሉ ትነጠላለች።

### ከአንድ- ሁለት

አበባ በጎዳና ያሉ መሰሎቿን አስተዋለች። አብዛኞቹ በፍቅር ጥንድ ሆነው ያድራሉ። በዚህ ህይወት ጋብቻና መተሳሳብ ይሏቸው እውነቶች እንዳሉ ነው። በጎዳና ሴት ልጅ ባልና ጓደኛ ከሌላት የብዙዎች ዓይን ያርፍባታል፣ በማንም መነተት መደፈሯ አይቀርም። ይህ እንዳይሆን አበባ ከአንዱ መጠጋት አለባት። ‹‹ባሌ›› የምትለው ‹‹ሚስቴ›› ሲል የሚጠራት አጋር ያሻታል።

በጎዳናው አበባና አንድ ሰው ለፍቅር ተፈቃቀዱ። ሁለቱም ልባቸው ለመውደድ ተገዛ፣ መተሳሰባቸው ከአንድ ውሎ እያሳደረ አብሮነታቸውን አጎላው። አሁን አበባ በዚህ ሰው ዓይን ገብታ ከክንዶቹ አርፋለች። ማንም በተለየ አስቦ ሊያጠቃት፣ ሊመኛት አይሞክርም። ብቸኝነቷ በፍቅር አጋሯ ተቀርፏል። አሁን የሚያሳስባት ቢኖር ድንገት የገባችበት የሱስ ልማድ ብቻ ነው።

አበባ በምታጨሰው ሲጋራና በምትቅመው ጫት ሳቢያ ለህመም እየተዳረገች ነው። ይህን ችግሯን ከመቻል ውጭ ግን ደፍራ መናገር አልተቻላትም። እንዲህ ልሞክር ብትል የሚቃወማት ይበዛል። የሚያነውራት ይበረክታል። ሱስ ማለት ለጎዳና ልጆች የመደበቂያ ዋሻቸው ነው። ይህን ዋሻ ያናናቀ፣ በሰበቡ ታመምኩ፣ ተቸገርኩ የሚል ቢኖር እንደ ነውረኛ ይቆጠራል። አበባ ይህን እውነት አሳምራ ታውቃለች። እናም በሱሱ ምክንያት መታመሟን ለመናገር አትደፍርም። ሁሌም ልቧን እያመማት ትቅማለች፣ ከነስቃይዋ ታጨሳለች። ለመኖር፣ ሌሎችን ለመምሰል ደግሞ እንዲህ መሆን የግድ ይላል።

የአበባ ጓደኛ ተሸከሞ፣ ለፍቶ አዳሪ ነው። ቀኑን ጉልበቱን ገብሮ ላቡን አንጠፍጥፎ ይውላል። ምሽት የሰራበትን ቋጥሮ ካገኘው አካፍሎ ከአነስተኛ ቤርጎ ቢጤ ያሳድራታል። ሌቱ ሲነጋ ሁሉም እንደልምዱ ይሰየማል። እሷ በምታመጣው ብር ጓደኞቿ እየቃሙ ያጨሳሉ፣ እያጨሱ ከቡሌው፣ ከትራፊው ይበላሉ። አንዳንዴ አበባ ያሰበችው አይሞላም። የምታመጣው ገንዘብ ለባልንጀሮቿ የማይበቃ ሲሆን ትሳቀቃለች። ሳይቀናት ቀርቶ ከእጅ በጠፋ ግዜ ውጤቱ የከፋ ነው። ከእሷ የሚጠብቁት የጎዳና ልጆች ሊያዩዋት አይፈልጉም። እየሰደቡ ያርቋታል፣ እያመናጨቁ ያባርሯታል።

ይህ አይነቱ አጋጣሚ ለአበባ በእጅጉ ፈታኝ ነበር። ከጓዳዋ ያጣችውን ሰላም ከጎዳና አላገኘችም። ከቤት ወጥታ ያረፈችበት ጥግ ከችግር አላዳናትም። አበባ በእጅጉ እየከፋት ነው። የውስጧን ያወቀ የለምና ቸግሯታል። አንዳንዴ ደርሶ ራስሽን አጥፊ ከሚል ስሜት ትገባለች። መልሳ ደግሞ የነገውን ተስፋ እያሰበች ትጽናናለች።

አንድ ቀን አበባ በህመም ከወደቀችበት ጎዳና የአንድ መልካም ሰው ዓይኖች አስተዋሏት። ይህ በጎ ሰዉ አይቷት ብቻ አላለፈም። ቀረብ ብሎ ችግሯን ተረዳ። ከሆስፒታል አድርሶም በወጉ አሳከማት። ችግሯ የልብ ህመም መሆኑን ያረጋገጠው ሀኪም በክትትል እንድትቆይ አደረገ። ሰውዬው የመድሀኒቱን ሙሉ ወጪ ከፍሎ ከህመሟ አዳናት። ከስቃይዋ መለስ ስትል ራሷን ባሏ ጉያ አገኘችው። ዳግመኛ ፍቅራቸው ደራ ትዳራቸው ጀመረ።

አበባ የመጀመሪያ ልጇን ጎዳና ላይ ወልዳ አሳደገች። ሁለተኛ ልጇም ከዚህ ዕጣ አላለፈም። በጎዳና ተወልዶ በጎዳና አደገ። ህይወት ከቀድሞው በባሰ የከፋባት እናት አበባ ልጇቿን ለማሳደግ ባዘነች። ትናንት አብሯት የነበረው የልጆቿ አባት በድንገት የደረሰበት ቢጠፋት ችግሮችን ለብቻዋ ተጋፈጠች። ከራሷ አልፎ ለልጆቿ ጉሮሮ ለመድረስም ሌት ተቀን ለፋች፣ ሮጠች።

ከጥቂት ጊዚያት በኋላ አበባ ሶስተኛ ልጇን ታቀፈች። ‹‹በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ›› እንዲሉ ሆኖ የዚህኛውም ወላጅ አባት በሞት ተለያት። ለአበባ ሶስት ልጆችን ያለ አባት ማሳደጉ በእጅጉ ይከብዳል። እንዲያም ሆኖ ችግሯን ለመቋቋም ትከሻዋ ሰፊ ሆኖ የመከራ ቀናትን ተሻግራለች። አሁንም አልፎ ያላለፈው ችግሯ ከእሷው ተጣብቆ አብሯት ቀጥሏል።

### ዛሬን- ስለነገ

ጠዋት ማታ በተስፋ የምትኖረው አበባ ከጎዳና የምትወጣበት ቀን እስኪመጣ የእሷ መከራ በልጆቿም ጭምር ሲያልፍ ቆይቷል። አበባን ብዙዎች በማንነቷ ያውቋታል። በተለይ ተወልዳ ባደገችበት አካባቢ ችግሯን አውቀው የሚያዝኑላት ጥቂቶች አይደሉም። እንዲህ መሆኑ ስምንት ዓመታትን በስቃይ ከኖረችበት የጎዳና ህይወት ለመውጣት ምክንያት ሆኗል።

አበባን ከልጅነቷ አንስተው የሚያውቋት የአካባቢው ሰዎች ወደቀድሞ መኖሪያ ቤት እንድትገባ አግዘዋታል። አሳዳጊ አክስቷ መሞታቸውን ተከትሎ የቀበሌ ቤቱን ትኖርበት ዘንድም የብዙ ሰዎች እጅ ተባብሯታል።

ዛሬ የትናንቷ አበባ ልጅነቷን ካሳለፈችበት ቤት ተመልሳ ልጇቿን በጣራ ስር ማሳደር ችላለች። ቀድሞ ተገፍትራ ከተባረረችበት ጎጆ ተመልሳም አዲስ ህይወትን ጀምራለች። አሁንም ግን በወጉ ልጇቿን አብልቶ ለማሳደር አቅሟ ደካማ ነው።

በልደታ አካባቢ በተገነባው የተስፋ ብርሀን የምገባ ማዕከል በቀን አንዴ ብቅ እያለች የተሰጣትን ለልጆቿ ታቀምሳለች። አበባ እስከዛሬ ህይወትን ከእነሾሁ ተቀብላው ኖራለች። ረጅሙንና ፈታኙን መንገድ በድል እየተወጣች ዛሬ ላይ ስትቆም ደግሞ ስለነገው ድካምን አታውቅም። ህይወትን ለማሸነፍ፣ ኑሮን ታግሎ ለመጣል በሩጫ ላይ ነች። በፈጣን የሩጫ ሜዳ ላይ።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ቅዳሜ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር ታላቁን ሰው ዘከረ

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያን በስፖርቱ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካስጠሩ ሰዎች መካከል አንዱ አንጋፋው የስፖርት ጋዜጠኛ ፍቅሩ ኪዳኔ ናቸው። እኚህ ታላቅ ሰው ከጋዜጠኝነት ሙያ ባለፈ በስፖርቱ ዘርፍ የተለያዩ አገልግሎቶችን በማበርከት የኢትዮጵያን ስፖርት ከምስረታው አንስቶ የደገፉ ናቸው። አቶ ፍቅሩ በዓለም አቀፍ የስፖርት ማህበራትም በአማካሪነትና ሌሎች ስራዎች ያገለገሉ ሰው ናቸው። የስፖርት ትምህርት ቤትና ማህደር የነበሩት አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ ባሳለፍነው ሳምንት በ88 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸው ይታወቃል። የቀብር ስነስርዓታቸውም ረጅም ዓመታትን በኖሩበት ፈረንሳይ የተፈጸመ ሲሆን፤ በአገራቸው ኢትዮጵያም ስራዎቻቸውን የሚዘክሩ መርሃ ግብሮች ተከናውነዋል።

ከእነዚህ መካከል አንዱ በኢትዮጵያ የስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር ከትናንት በስቲያ ምሽት የተዘጋጀው ዝክረ ፍቅሩ ኪዳኔ ዋነኛው ነው። አቶ ፍቅሩ በተለይ የሚታወቁት በስፖርት ጋዜጠኝነት ሲሆን፤ በጋዜጣ እና በሬዲዮ ስፖርትን በመዘገብም ቀዳሚው ሰው ናቸው። በአማርኛ፣ እንግሊዝኛ እና ፈረንሳይኛ ቋንቋዎችም ከኢትዮጵያው የዛሬይቱ ኢትዮጵያ እስከ ትልልቆቹ የፈረንሳይ ጋዜጦችና መጽሄቶችም ስፖርታዊ ዘገባዎቻቸውን አስነብበዋል። ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም የኢትዮጵያ ስፖርት ጋዜጠኞች ማህበርን በመመስረትና በመምራት የማይዘነጋ ሚና አላቸው። ይህንን የሚዘክር መድረክም በሙያ ልጆቻቸው ማህበር የተካሄደ ሲሆን፤ እርሳቸውን የሚያውቁ እንግዶችም በቦታው ተገኝተዋል።



የኢትዮጵያ ስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር ታላቁን የስፖርት ሰው ፍቅሩ ኪዳኔን ጧፍ በማብራት ዘክሯል፣

በዝክር መርሃ ግብሩ ላይ ተገኝተው ንግግር ካደረጉ ሰዎች መካከል አንዱ የሆነው ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ ትውውቃቸውን በማስታወስ ነበር ንግግሩን የጀመረው። ኃይሌ በሲድኒ ኦሊምፒክ ሲያሸንፍ፤ አቶ ፍቅሩ ከዓለም አቀፉ የኦሊምፒክ ኮሚቴ አመራሮች ጋር በመሆን በስታዲየም የተገኙ ሲሆን ደስታቸውንም አጠገቡ ሄደው ነበር የገለጹለት። ከዚያን በኋላም ትውውቃቸው ጠንክሮ በተለያዩ ውድድሮች ላይ በቅድሚያ የሚያገኛቸው ሰው ናቸው። እንደ ቤተሰብም ይጠያየቁ ነበር። በቅርቡ የተሰማው ህልፈታቸው አሳዛኝ ቢሆንም በሕይወት ሳሉ ሃውልታቸውን ሰርተው ካለፉ ሰዎች መካከል መሆናቸውን ጀግናው አትሌት ተናግሯል። አቶ ፍቅሩ አፍሪካዊ ሆነው በዓለም አቀፍ የስፖርት ተቋማት ውስጥ ነጮችን ማማከራቸውም ምን ያህል ተጽዕኖ ፈጣሪ እንደሆኑ የሚያሳይ መሆኑንም አብራርቷል።

ሌላኛው በመድረኩ ላይ ትዝታቸውን ያጋሩት የአቶ ፍቅሩ የረጅም ጊዜ ወዳጅ የሆኑትና የቅዱስ ጊዮርጊስ ስፖርት ክለብ ፕሬዚዳንት አቶ አብነት ገብረመስቀል ናቸው። በንግግራቸውም አቶ ፍቅሩ ኪዳኔ ለኢትዮጵያ፣ አፍሪካ እና ዓለም ስፖርት የተፈጠሩ ሰው መሆናቸውን አንስተዋል። ‹‹በዓለም አቀፍ የስፖርት ተቋማት ስማቸው የተከበረ የስፖርት ማህደር›› መሆናቸውንና በየትኛውም ዘርፍ የኢትዮጵያ ጠበቃ እንደነበሩም በሃዘን ስሜት ውስጥ ሆነው ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ስፖርት ታሪክ አቶ ፍቅሩ ፈር ቀዳጅ ከሆኑባቸው ጉዳዮች መካል አንዱ የስፖርት ጋዜጠኝነት ሲሆን፤ የስፖርት ጋዜጠኞች ማህበርንም በ1960ዓ.ም በመመስረትና በአመራርነትም አገልግለዋል። ኑሯቸውን በፈረንሳይ ካደረጉም በኋላም ማህበሩ በተለያየ ጊዜ አዳዲስ አመራሮችን ቢቀያይርም ከጎኑ በመሆንና፤ ሕይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ ለአባላቱ የትኛውንም ሙያዊና ሌሎች ጉዳዮች ላይ በማማከርና ልምዳቸውን በማካፈል ቆይተዋል። በመሆኑም ማህበሩ ታላቅ ሰው ማጣቱን የማህበሩ ፕሬዚዳንት ጋዜጠኛ ነዋይ ይመር ገልጿል። ላበረከቱት አስተዋጽኦም ማህበሩ ከአራት ዓመታት በፊት የሕይወት ዘመን ልዩ ተሸላሚ አድርጓቸው ነበር። በጊዜውም ለጀማሪ የስፖርት ጋዜጠኞች መታሰቢያ ይሆንላቸው ዘንድ መጠየቃቸውንና የትኛውም ባለሙያ ሲፈልጋቸው በቅርበት የሚገኙ ሰው እንደነበሩም አስታውሷል።

አቶ ፍቅሩ የኢትዮጵያውን የስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር ብቻም ሳይሆን የአፍሪካ እና የዓለም የስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር ምስረታ ላይም ቀዳሚው ሰው ነበሩ። ይህንን ተከትሎም የማህበራቱ አመራሮች በተንቀሳቃሽ ምስል ሃዘናቸውን ገልጸዋል። አቶ ፍቅሩ የክብር አባል የሆኑበት የዓለም የስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ጂያኒ ሜርሎ፤ ማህበሩ አማካሪው የነበሩ ትልቅ ሰውን አጥቷል ብሏል። የአፍሪካ ስፖርት ጋዜጠኞች ማህበር ፕሬዚዳንት ሚሼል አቢ በበኩሉ፤ በማህበሩ ምስረታ እንዲሁም አቅጣጫዎችን በመስጠት ሚናቸው ከፍተኛ እንደነበር አውስቷል። የጋዜጠኝነትን ፍልስፍና በተግባር ያሳዩ መሆናቸውንም ከስራቸው መረዳት እንደሚቻልም ነው የገለጹት።

የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፤ በመድረኩ ላይ ተገኝተው ሃዘናቸውን ገልጸዋል። በዚህም አቶ ፍቅሩ በኢትዮጵያ ፋና ወጊ ጋዜጠኛ ከመሆናቸው ባሻገር ኢትዮጵያን ያስቀደሙ የስፖርት ዲፕሎማት መሆናቸውንም ነው ያመላከቱት።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም
ጋር በመተባበር በየሣምንቱ የሚታተም

## ለ7502 ነፃ የስልክ መስመር አቤቱታ አቅራቢዎች በሙሉ!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም የዜጎችን ጊዜ፣ ገንዘብና ጉልበት ብክነት ከማስቀረት አኳያ አቤቱታ አቅራቢዎች 7502 ነፃ ስልክ መስመርን በመጠቀም አቤቱታቸውን ባሉበት ቦታ ሆነው እንዲያቀርቡ በማድረግ እየተሰራ መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ሰሞኑን የነጻ ስልክ ቁጥሩ በSMS በመተዋወቁ ብዙ ሰዎች እየደወሉበት በመሆኑ በርካታ አቤቱታ አቅራቢዎች በዚህ የስልክ መስመር በአግባቡ እየተስተናገዱ አለመሆናቸውን በተለያዩ መንገዶች መረጃዎች እየደረሱን ይገኛሉ። በመሆኑም 7502 በመደበኛነት በሦስት ቋንቋዎች (አማርኛ፣ ኦሮምኛና ትግርኛ) ሁልጊዜ የሚሰራ የአቤቱታ መቀበያ የስልክ መስመር እንጂ ጊዜያዊ አለመሆኑንና በቀጣይም አገልግሎት የሚሰጥ እንደሆነ፤ ያጋጠመው የመስመር መጨናነቅም ጊዜያዊ መሆኑን እንድትረዱልን እንጠይቃለን። አሁን ላይ አቤቱታ አቅራቢዎችን እያጋጠመ ያለውን የመስመር መጨናነቅ ችግር ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ችግሩን ለማቃለል ይቻል ዘንድ ሊቀርቧችሁ በሚችሉ በዋናው መ/ቤት ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚከተሉትን መደበኛ የስልክ መስመሮች በተጨማሪነት በመጠቀም አቤቱታችሁን ማቅረብ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን።

| | |
|---|---|
| ለዋናው መስሪያ ቤት<br>0115580147/ 126/ 094/ 021 | ለጋምቤላ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት<br>0475510548 |
| ለባህር ዳር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት<br>0582205369 | ለኦሮሚያ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት<br>0114703341 |
| ለአፋር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት<br>0333663604 | ለድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት<br>0251110859 |
| ለአሶሳ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት<br>0572752876 | ለሐዋሳ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት<br>0462206005 |

ማሳሰቢያ፡-

ተቋሙ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ጉዳዮችን የማይመለከት መሆኑንን ለማስታወስ እንወዳለን።

1. በሕዝብ ምርጫ የተቋቋሙ ምክር ቤቶች በሕግ አውጭነታቸው የሚሰጧቸው ውሳኔዎችን፤
2. በፍርድ ቤቶች ወይም በህግ የመዳኘት ስልጣን በተሰጣቸው አካላት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች ወይም የታዩና ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮችን፤
3. በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም በክልል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በመታየት ላይ ያሉ እና የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮችን፤ እንዲሁም
4. በመከላከያ ሠራዊትና በፖሊስ ክፍሎች የሚሰጡ የፀጥታ ወይም የሀገር መከላከል ጉዳዮችን በሚመለከት የሚሰጡ ውሳኔዎችን የመመርመር ሥልጣን የለውም።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ